# የትግራይ ህዝብና የትምክህተኞች ሴራ

# ከትናንት እስከ ዛሬ

ከመምህር ገብረኪዳን ደስታ

1998 ዓ/ም

© መምህር ገብረኪዳን ደስታ

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው::

All Rights Reserved

አንደኛ እትም 1998 ዓ/ም

## ምስጋና

ለሕትመት የሚያስፈልገውን ገንዘብ፣ ልዩ የመንፈስ ደስታ እየተሰማቸው ሙሉ በሙሉ ለሸፈኑልኝ ክቡራን ወዳጆቼ፣ የተለየ አክብሮትና ምስጋና ሳቀርብላቸው የመንፈስ ኩራት ይሰማኛል:: አቶ ብርሃነ ኪዳነማርያም ይህን መፅሐፍ ለመፃፍ ከተነሳሳሁበት ቀን ጀምሮ ከፍተኛ የሞራል ድጋፍ ስላደረገልኝ ምስጋናዬ የላቀ ነው:: አቶ ብርሃኑ አባዲም፣ ገንቢ ሐሳብ በመስጠት ትብብሩ ስላልተለየኝ ከልብ አመሰግነዋለሁ::

እንደዚሁም፣ መፅሐፉን አንብበው ሐሳብ በመለገስና ደጋግመው በኮምፒዩተር በመፃፍ ለተባበሩኝ ሁሉ ከልብ የመነጨ ምስጋና አቀርብላቸዋለሁ:: መፅሐፉን ባጭር ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ የቻልኩትም የባለቤቴ ልዩ ድጋፍና ትብብር ስላልተለየኝ በመሆኑ፣ ለባለቤቴ ለወ/ሮ ለተብርሃን ገብረሀይወት ያለኝ ልባዊ ፍቅርና አክብሮት በቃላት ለመግለፅ ያዳግተኛል::

1998 ዓ/ም

# ይህ መፅሐፍ መታሰቢያነቱ

ትግራይን ህዝብ ብሄራዊና ሃገራዊ እኩልነት ለማረጋገጥ ሲሉ፣ ካቲት ወር 1967 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ፣ ከህወሐት ጐን ሰልፈው፣ ከተለያዩ የትግራይ ህዝብ ደመኛ ጠላቶች ጋር ተፋለሙ፣ ዳግም የማትገኝ ውድ ህይወታቸውን፣ አካላቸውንና ጣትነት ዕድሜያቸውን ቤዛ ላደረጉ የህዝብ ልጆች በሙሉ ሁንልኝ::

መምህር ገብረኪዳን ደስታ

# ሳሰቢያ

ህ መፅሐፍ ውስጥ ያለው የዘመን አቆጣጠር እስከ ዳግማዊ ልክ ዘመነ መንግስት ፍፃሜ ድረስ፣ በአውሮፓ አቆጣጠር ነው ፃፈው:: ከዚያ በኋላ ያሉት ዓመታት ግን፣ ከሞላ ጎደል ትዮጵያ ዘመን አቆጣጠርን የተከተሉ ናቸው::

ንኛውም አስተያየት
ፓ.ሳ.ቁ. 7406 አ.አ ኢትዮጵያ

ሊያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1

ምዕራፍ አንድ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 11

ተክለጊዮርጊስ ዛቻና ውጤቱ . . . . . . . . . . . . . 11

ምዕራፍ ሁለት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 21

ሐንስና የግብፅ ወራሪ ሐይል . . . . . . . . . . . . .21

ምዕራፍ ሶስት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .28

ሊ ጦርነትና ውጤቱ . . . . . . . . . . . . . . . . . 28

ምዕራፍ አራት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 42

ምኒልክ ሃገራዊ ሴራና የአፄ ዮሐንስ ዘመነ
ነት ፍፃሜ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 42

ምዕራፍ አምስት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .74

ከጠገበና አንድ ከሆነ አይገዛም» . . . . . . . . . . .74

ምዕራፍ ስድስት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .106

የና የትግራይ ህዝብ የህልውና ተጋድሎ . . . . . . . . 106

ምዕራፍ ሰባት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .156

ምኒልክ ደቀመዝሙሮች ምን እያሉ ነው? . . . . . 156

ምዕራፍ ስምንት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .194

ካገራችን ይውጣ!» . . . . . . . . . . . . . . . . . . 194

አፄ ዮሐንስ በአውሮጳ ዘመን አቆጣጠር በ1872 ዓ/ም ላይ
በአኩሱም ፅዮን ቤተክርስቲያን የነገሱት። ይሁን እንጂ
ፁ እንደ ግብፅና እንደ ኢጣልያ የመሳሰሉ ወራሪዎች ሰሜን
ዮጵያን ለመቆጣጠር ያሰፈሰፉበት ወቅት ነበርና፣ ዘመኑ ለአፄ
ነስም ሆነ ለትግራይ ህዝብ ፈታኝ ነበር። በሌላ አነጋገር አፄ
ነስ እንደ እምዬ ምኒልክ በተድላና በደስታ ኢትዮጵያን
ገዛት የታደሉ ንጉሰ ነገስት አልነበሩም።

በመጀመርያ ደረጃ ሰሜን ኢትዮጵያን ለመቆጣጠር
ነጋሚ ሙከራ ያደረገው የግብፅ ወራሪ ሐይል እንደነበር
ነጋም። ነገር ግን፣ በአፄ ዮሐንስ እና በአሉላ አባ ነጋ
ራው የሰሜን ኢትዮጵያ ሰራዊት፣ ጉዳጉዲ፣ ጉራዕና ሰሐጢ
ኑ ዓውደ ውጊያዎች ላይ የግብፅን ጦር በተከታታይ
ጣት የሐፍረት ካባ አከናንቦ ወደ መጣበት መልሶታል።

ምኒልክም እንዲሁ፣ የሰሜን ኢትዮጵያን ህዝቦች
ፋትና ለመበታተን በነበራቸው ሰፊ እቅድ መሰረት ከውጭ
ሐይሎች ጋር መመሳጠርና ማሴር የጀመሩት፣ በዚሁ
እንደነበር ይታወቃል።

ከዚሁም የተነሳ የትግራይ ህዝብ አገሩንና ዳር ድንበሩን
ነከል ከግብፅ ወራሪ ሐይል ጋር በሚዋደቅበት ወቅት፣ ንጉስ
ካ ግን ከወራሪው የግብፅ ሰራዊት ጐን ነበር የተሰለፉት።
ኣያ መንግስት ግብፅን ተክቶ፣ ወረራውን በሚቀጥልበት
ም እንዲሁ፣ ንጉስ ምኒልክ፣ አሁንም ከወራሪው የኢጣልያ

አይደለም። ከደርቡሾች ጋርም እንዲሁ፣ በትግራይ ህዝብ ላይ ያነጣጠረ ልዩ ሴራና ምስጢራዊ ግንኙነት ነበራቸው። ሌላ ይቅርና የአፄ ዮሐንስ ሞትም ቢሆን፣ በአፄ ምኒልክ ሴራ እንጂ፣ በወራሪው የድርቡሽ ሐይል ጥበብና ችሎታ እንዳልሆነ፣ አቶ አፈወርቅ ገብረኢየሱስም ይመሰክራሉ። «ዳግማዊ ምኒልክ» /ገፅ 56/

በመሆኑም ግብፅም ሆነች ኢጣሊያ፣ «የፖለቲካ ስልጣን ከአፄ ዮሐንስ እጅ ወጥቶ ወደ ንጉስ ምኒልክ ካልተዛወረ በስተቀር፣ በሰሜን ኢትዮጵያ ቅንጣት መሬት መቆጣጠር አይቻልም» የሚል እምነት ነበራቸው። /ኤርሊክ ገፅ 14/ ይህ አመለካከት ግን ከባዶ ነገር የመጣ አይደለም። ባንድ ወቅት ኢጣሊያኖች፣ ሰሐጢ አካባቢ ላይ ትንሽ መሬት እንዲሰጣቸው፣ ራስ አሉላ አባ ነጋን ጠይቀው ነበር። ለዚህ ጥያቄ ከራስ አሉላ የተሰጣቸው መልስ ግን፣ «እናንተ ወደ ሰሐጢ የምትመጡት፣ እኔ የሮም ገዥ ስሆን ብቻ ነው» የሚል ሆነ። ኤርሊክ/ገፅ 153/ አንድ ታዛቢም ከዚህ በመነሳት ይመስላል ለራስ አሉላ አባ ነጋ።

«አሉላ አባ ነጋ ውረድ ናብቲ ባፅዕ፣
ሰብ ክርኢ አይደልን አብ ባሕሪ ዝሕባእ፣
አብቲ ቆላ ባፅዕ ፃህያይ በቆሎ አሎ።
ወሪድካ ንቐሎ ብጋንኡ እንተሎ» ብሎ የገጠመላቸው።

የግጥሙ መልእክትም ባጭሩ፣

«ባሕር ውስጥ የሚደበቅ ሰው አልፈልግምና፣ አሉላ አባ ነጋ እባክህን ወደ ምዕዋ ውረድ። ምዕዋ ቆላ ላይ የበቀለ አረምም አለ። ስለሆነም ሂድና ስር ሳይሰድ ነቅለህ ጣለው» የሚል ነው።

ኢጣልያኖች በአሉላ አባ ነጋ መልስ ተስፋ ቆርጠው አልተኙም። ለአፄ ዮሐንስም ተመሳሳይ ጥያቄ ነበር ያቀረቡላቸው። የአፄ ዮሐንስ መልስም በመሰረቱ ከአሉላ አባ ነጋ መልስ የተለየ አልነበረም። «እኔስ ካገሬ ጥርኝ አፈርም አልሰጥም። እናንተም ባገራችሁ ኑሩ፡ ተነሱልኝ» የሚል መልስ ነው የተሰጣቸው። «ዐሐፌ ትእዛዝ ገብረስላሰ» /ገፅ 221/

ስለዚህ የግብፅና የኢጣልያ ወራሪዎች፣ ፖለቲካዊ ስልጣን ከአፄ ዮሐንስ እጅ ወጥቶ ወደ ንጉስ ምኒልክ ካልተዛወረ በስተቀር፣ በሰሜን ኢትዮጵያ ቅንጣት መሬት መቆጣጠር አይቻልም፤ ማለታቸው ያለ ምክንያት አይደለም።

እዚህ ላይ ነገሩ ግልፅ ለማድረግ የሃጋይ ኤርሊክን አባባል እጠቅሳለሁ። «የዶግዓሊ ጦርነት፣ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ወሳኝ ምዕራፍ ነው። ይህ በአጼ ዮሐንስና በኢጣልያ መሃከል የተደረገው ጦርነት የሸዋን የበላይነት ለማረጋገጥ ማገዙ አልቀረም» ይላል። የዶግዓሊ ጦርነት ብቻ ግን አይደለም፡ የትምክሕተኞችን የበላይነት ለማረጋገጥ ያገዘው። የመተማው ጦርነትም እንዲሁ ለከሐዲዎችና ለወራሪዎች ምቹ ሁኔታ ፈጥሮላቸዋል። ይህን በተመለከተም፣ ራስ አሉላ አባ ነጋ ሲናገሩ፣ «እኛ በምኒልክ ቀንበር ስር የወደቅነው፣ ከመተማ ጦርነት በኋላ ሐይላችን ስለተዳከመና በሁለት እሳት መሃከል ስለተጠበስን ነው» ብለው ነበር። «ኤርሊክ» /ገፅ 215/

አንዳንድ የታሪክ ባለሞያዎች ግን፣ ታሪክን በማዛባት ለመተንተን ይሞክራሉ፡፡ «አፄ ዮሐንስ፣ ከፍተኛ ውድቀት ላይ የደረሱት ጥበብ የተሞላበት ዲፕሎማሲያዊ አገባብ ባለመከተላቸው ነው፡፡ ስለሆነም፣ ኤርትራን አጡ፡ ትግራይም እንዳልነበረች ሆና ወደመች፡፡ ዲፕሎማሲያዊ ጥበብ የነበራቸው ዳግማዊ ምኒልክ ግን፣ ስልጣን ለመጨበጥ ቻሉ» ይሉናል፡፡ ይህ አባባል ግን እራሱን የቻለ የታሪክ ክሕደት ነው፡፡

አፄ ዮሐንስ፣ ከ1875-1889 ዓ/ም ድረስ ከውጭ ወራሪዎች የተሰነዘሩ ስምንት ጦርነቶችን ለመጋፈጥ ተገደዋል፡፡ ከነዚህ ዓውደ ውጊያዎች ውስጥ ግን፣ ንጉስ ምኒልክ ባንዱም የጦር ሜዳ አልተሳተፉም፡፡ በአንፃሩ ግን ንጉስ ምኒልክ የእነዚህ ወራሪዎች ተባባሪና አማካሪ ነበሩ፡፡ ስለዚህ እንደዚህ ያለ ሃገራዊ ክሕደት እንደ ዲፕሎማሲያዊ ጥበብ የሚታይ ከሆነ ፍርዱን ለታሪክ እተወዋለሁ፡፡

ባጭሩ ለማስቀመጥ ግን፣ የትግራይ ህዝብ፣ ነፃነቱንና ዳር ድንበሩን ለማስከበር ሲል፣ ከኢጣልያ ወራሪዎች ጋር ባደረገው የሞት የሽረት ተጋድሎ ምክንያት፣ በትግራይ ህዝብና በወራሪው የኢጣልያ ሰራዊት መሃከል ከፍተኛ ቅራኔ ተፈጥሮ ነበር፡፡ ለዚህም ነው የኢጣልያ ወራሪዎች «ከሰው ሁሉ እንደ አበሻ፣ ከአውሬ ሁሉ እንደ አንበሳ ጨካኝ ፍጥረት አላየንም» ብለው ለመናገር የተገደዱት፡፡ «ትቤ አኩሱም መኑ አንተ?» /ገፅ 21/

ስለሆነም አፄ ምኒልክ፣ ዲፕሎማሲያዊ ጥበብ ስለነበራቸው ሳይሆን፣ ሃገራዊ ወኔ አልነበራቸውምና፣ በትግራይ ህዝብና በኢጣልያ ወራሪዎች መሃከል የነበረውን ከፍተኛ የማይታረቅ

ቅራኔ በመበዝበዝ፣ የወራሪዎችን ፍላጎት ሳያቅማሙ ሙሉ በሙሉ ለማስተናገድ በመቻላቸው ብቻ ነው ስልጣን ላይ ለመውጣት የቻሉት።

በዚያን ጊዜ የኢጣልያ ወራሪዎች፥ «ቁጥር አንድ ጠላታችን ነው» ብለው የፈረጁት፣ የትግራይን ህዝብ ብቻ ነበር። ትምክሕተኞች ግን፣ ከስልጣን በላይ የሚያዩት ነገር የላቸውምና፥ ስልጣን ለመጨበጥ ብቻ ሲሉ፥ የትግራይን ህዝብ ለመበታተን፥ ለማዳከምና ለማጥፋት ከኢትዮጵያ ህዝብ ደመኛ ጠላቶች ጐን ተሰለፉ። ለዚህም አንድ አብነት ብቻ እንመልከት።

ልዑል ራስ መኰንን ከአፄ ምኒልክ የተላከ ደብዳቤ ይዘው ወደ ሮም እንደሄዱ፣ ከንጉስ ኡምቤርቶ ፊት ቀርበው ሲናገሩ «የኢጣልያ ጠላቶች፣ የኛም ጠላቶች እንደሆኑ ለልዑል ግርማዊነትዎ አረጋግጥልዎታለሁ» በማለት ነበር የትግራይን ህዝብ ለማጥፋት ከወራሪው የኢጣልያ መንግስት ጐን የተሰለፉ መሆናቸውን ያረጋገጡለት። «ትቤ አኩስም መኑ አንተ?» /ገፅ 29/

የትግራይ ህዝብም፣ ራስ አሉላ አባ ነጋ እንዳሉት «በሁለት እሳት መሃከል እየተጠበሰ» ካዲሱ ምኒልካዊ የስቃይ ዘመን ጋር መጓዝ ጀመረ። ለዚህም ነው ሃጋይ ኢርሊክም፣ በትግራይ ህዝብ ላይ ስለደረሰው መከራ ሲፅፍ፣ «ከአፄ ዮሐንስ ድንገተኛ ሞት በኋላ፣ እነዚያን ኩሩ የትግራይ መሳፍንት፣ የሚያስተባብራቸው አካል አላገኙም። ከዚሁ ጋር ተያይዞም ያቺ፣ በሸዋ፣ በደርቡሾችና በኢጣልያኖች ምክንያት አደጋ ላይ የወደቀችው፣ የወደመችውና

የተበታተነችው ትግራይም፣ ተፃራሪ የሌለው መሪ ለማግኘት አልታደለችም» በማለት ታሪኩን በሚያሳዝን መልኩ የሚገልፀው፡፡

እንግዲህ ከላይ እንዳየነው፣ የትግራይ ህዝብ የሚያስተባብረው አካል በማጣቱ፣ የእነዚህን ትምክሕተኞች የግፍ ቀንበር ተሸክሞ ነው፣ ከሰብአዊ ፍጡር በታች ሆኖ፣ ፍዳውን እያየ ዘመናትን ያስቆጠረው፡፡ ይህ አሰቃቂ የሕይወት ጉዞ ግን፣ መከፈል ያለበት ዋጋ ተከፍሎ መገታት ነበረበት፡፡ ይህነን የግፍ ቀንበር በማይደግም መልኩ አሽቀንጥሮ ለመጣል ግን፣ በቀላሉ የሚታይ አልነበረም፡፡ በመሆኑም የትግራይ ህዝብ፣ እንዳንድ ሰው ሆኖ ባደረገው እልህ አስጨራሽ ተጋድሎ፣ የደርግን መንግስት በ14 ዓመት ውስጥ ነበር ከትግራይ ምድር ጠራርጎ ያባረረው፡፡

በመቀጠልም ከኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰብ ሐይሎች ጋር ግንባር በመፍጠር፣ የደርግን መንግስት በአገር ደረጃ ለመገርሰስ ቻለ፡፡ ሁሉም ብሄር ብሄረሰቦች፣ በመቻቻል፣ በመከባበር እና በእኩልነት በጋራ የሚኖሩባት ኢትዮጵያም እንደገና ተወለደች፡፡ በፌዴራላዊ ስርዓት የተዋቀረ ሃገራዊ መንግስትም በትምክሕተኞች፡ በዘረኞችና በነፍጠኞች መቃብር ላይ ተመሰረተ፡፡

ጉዞው በዚህ መልክ እየቀጠለ ባለበት ወቅት ነበር፣ ሶስተኛው ሃገራዊ ምርጫም በግንቦት ወር 1997 ዓ/ም ላይ የተካሄደው፡፡ ይህ ምርጫ የተለያየ ዓላማና አመለካከት ያላቸው ፓርቲዎችና ግለሰቦች የተሳተፉበት ስለነበር፣ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ልዩ ምዕራፍ ይዞ ይኖራል ተብሎ ነው የሚታመነው፡፡

ይሁን እንጂ ምርጫው፣ የራሱ የሆኑ ጠንካራና ደካማ ጎድኖች ቢኖሩትም፣ ቀደም ብለው ከተካሄዱት ሁለት ምርጫዎች ጋር ሲነፃፀር ግን፣ በመሰረቱ የተሻለና ብዙ ህዝብ በመራጭነት የተሳተፈበት በመሆኑ፣ በአገር ውስጥም ይሁን በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ምስጋናም ሆነ ሂስ አልተነፈገውም።

በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ሽፋን ለውድድር የቀረቡት እንደ ቅንጅት የመሳሰሉ የትምክሕት ሐይሎች ግን፣ «ሰይፍ ዘክልኤ አፉሁ» /ሁለት ስለት ያለው ሰይፍ/ ሆነው ነበር የተወዳደሩት። ይኸውም፣ የመጀመርያው ስልታቸው በዴሞክራሲያዊ መንገድ በመወዳደር ስልጣን መጨበጥ የሚል ሲሆን፣ ምርጫው እነሱ በሚፈልጉት መንገድ ፍፃሜ ካላገኘ ግን፣ «ምድር አንቀጥቅጥ» ብለው በሰየሙት የከተማ ላይ ነውጥ ተጠቅመው፣ «ወያኔ ኢህአዴግን፣ ወደ አገሩ በመሸኘት» የትምክሕተኞችን መለኮታዊ በትረ መንግስት መጨበጥ የሚል ነበር።

የአፄ ምኒልክን ቤተመንግስት ማን ተቆጣጠረ? እያለ በስደት ዓለም ውስጥ ሆኖ፣ «የወያኔ ኢህአዴግን ሕልፈት አሳየኝ» ብሎ ነጋ ጠባ ከመፀለይና በወያኔ ኢህአዴግ ላይ ከማሴር በስተቀር፣ ለኢትዮጵያ ህዝቦች የጋራ ህልውናም ሆነ፣ ለሃገራዊ እድገትና ልማት ባዕድ የሆነው ዳያስፖራም፣ በጭፍን የዘርና የጥላቻ ፖለቲካ ታውሮ፣ «እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል» በሚለው የአህያ ፍልስፍና እየተነዳ፣ ገንዘቡን፣ እውቀቱንና ጉልበቱን አስተባብሮ ከአያቶቹ የወረሰው፣ የጥላቻና የዘረኝነት መርዙን በትግራይ ህዝብ ላይ ብቻ እየረጨ ከረመ።

እንደ መኢሶን፣ ኢህአፓና ኢሰፓ ወዘተ ያሉት የስያሜ እንጂ፣ የዓላማና የተግባር ልዩነት የሌላቸው የባሕር ማዶ ተስፈኛ ቡድኖችም እንዲሁ፣ የትምክሕተኛው ሐይል ቀንደኛ ጠላት የሆነውን፣ «ወያኔ ኢህአዴግን» ደምስሰው፣ ያባቶቻቸውን በትረ መንግስት ዳግም ለመጨበጥ፣ በውክልና ከሚያንቀሳቅሱት፣ ያገር ውስጡ ቅንጅት ጋር ተሰልፈናል ብለው አወጁ።

በአዲስ አበባ ከተማ በየቀኑ የሚታተሙት፣ አብዛኞዎቹ የግል ጋዜጦችም እንዲሁ፣ የትምክሕተኞችንና የዘረኞችን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ፣ በትግራይ ህዝብ ላይ ብቻ በማነጣጠር፣ የእልቂት መርዛቸውን በመርጨት ላይ ነበሩ። እነዚህ የትምክሕት ሐይሎች፣ በጀግኖች የዓመታት ተጋድሎና የህይወት መስዋእትነት የተገኘውን ዴሞክራሲያዊ መድረክ፣ ህዝቦችን እርስበርስ ለማናቆርና ለማተራመስ ተጠቀሙበት። እንደ ፕሮፌሰር መስፍንና ፕሮፌሰር ጌታቸው ሐይሌ የመሳሰሉ የትምክሕቱ ጉራ ልሂቃንም፣ ከአያቶቻቸው የተካኑትን የጥላቻና የዘረኝነት መርዛቸውን በትግራይ ህዝብ ላይ በመርጨት፣ ሂትለራዊ ግዴታቸውን ተወጡ።

እኔም እነዚህ ኢህገራውያን ትምክሕተኞች፣ በትግራይ ህዝብ ላይ የሚነዙት የጥላቻና የእልቂት መርዝ ከዕለት ወደ ዕለት እየከፋ በመሄዱ ነው፣ በመጠኑም ቢሆን ማንነታቸውን ለማጋለጥ፣ በትግርኛ ቋንቋ የጀመርኩትን ስራ ትቼ ይህን መፅሐፍ በአማርኛ ቋንቋ ለመፃፍ የተገደድኩት። «የያዘውን ከወረወረ ፈሪ አይባልም» እንደሚባለው ነውና፣ እኔም የትግራይን

ህዝብ ደመኛ ጠላቶች ማንነት በማጋለጥ በኩል ማድረግ የምችለውን ነገር በማድረጌ የመንፈስ እርካታ ይሰማኛል።

ከዚህ በኋላ ግን፣ የትግራይ ምድር ያበቀለቻቸው ምሁራን፣ የታሪክ ተወቃሽ ላለመሆን፣ የትምክሕተኞችንና የዘረኞችን የውሸት ብዕር በማሻመድመድ፣ የትግራይን ህዝብ ሐቀኛ ታሪክና ማንነት በአግባቡ እየመዘገቡ ለቀጣዩ ትውልድ የማስተላለፍ ህዝባዊ ግዴታ አለባቸው። በሌላ አነጋገር «ትግሬ ታሪክ ይሰራል እንጂ፣ ታሪክ አይፅፍም» የሚለው የትምክሕተኞች የትናንቱ ፌዝ፣ ነገና ከነገ ወዲያም በትግራይ ምሁራን ላይ የሚሰነዘር ተሳልቆ ሆኖ መቀጠል አይኖርበትም።

በመጨረሻ ላይ ግን፣ አንድ ነገር ለማሳሰብ እፈልጋለሁ። ትምክሕተኞች፣ የትግራይን ህዝብ «ድሃ፣ ለማኝ፣ ስደተኛ፣ ደንቆሮ፣ ቋንቋው ጉረሮ የሚፍቅ፣ ለፍቅር የማይሆን፣ አገሩ ድንጋይ፣ እህል የማይበቅልበት» ወዘተ እያሉ ነው የሚሳለቁበት። የሌላውን ነገር እንተወውና፣ ለድህነቱና ለኋላቀርነቱ ግን፣ በታሪክ ውስጥ ካነሱ ወዲያ ተጠያቂ የለም። ቢሆንም ግን፣ የትግራይ ህዝብ፣ ነገና ከነገ ወዲያ ሳይል፣ ድህነትንና ትምክሕትን ለዘለዓለሙ ለመቅበር ገንዘቡን፣ እውቀቱንና ጉልበቱን አስተባብሮ እንዳንድ ሰው ሆኖ መንቀሳቀስ አለበት። ብሄረ ትግራይም፣ የባህል፣ የታሪክ፣ የአንድነት፣ የጀግንነት፣ የመቻቻል፣ የእኩልነት፣ የአልበገር ባይነትና የኢትዮጵያ ህዝብ የስልጣኔ እምብርት እንደሆነች ሁሉ፣ «ካብያ ነበረኒስ እኒህኒ» ነውና፣ ዛሬም ያለፈውን ታሪክ ለመድገም፣ የስራ፣ የባህል፣ የእውቀት፣ የምርምር፣ የአንድነት፣ የእድገትና የብልፅግና ማእከል ሆና

መቀጠል ይኖርባታል። እነዚህ ነገሮች ተግባራዊ ሳይሆኑ ከቀሩ ግን፣ በትግራይ ህዝብ የዓመታት ተጋድሎና፣ ጀግኖች በከፈሉት ክቡር የሕይወት መስዋእትነት የተጐናፀፍነው፣ ብሄራዊ እኩልነትና ሃገራዊ አንድነት፣ ለትግራይ ህዝብ ደመኛ ጠላቶች መጋለጡ አይቀርም። ይህ እንዳይሆን ግን፣ የትግራይ ህዝብ አንድነቱ በላላ ቁጥር ምን እንደሚሰነዘርበት ካለፈው ታሪኩ በመማር፣ ለትምክሕተኞች ከፋፋይ ሴራ ሳይጋለጥ፣ ብሄራዊና ሃገራዊ አንድነቱን ጠብቆ የደመኛ ጠላቶቹን ሰይጣናዊ እንቅስቃሴ ምን ጊዜም ቢሆን በጥበብና በንቃት መከታተልና ማክሸፍ ይኖርበታል።

# ምዕራፍ አንድ

# የአፄ ተክለጊዮርጊስ ዛቻና ውጤቱ

ኢትዮጵያ እንደ አውሮጳ ዘመን አቆጣጠር ከ1769-1855 ዓ.ም ድረስ አንድ ማእከላዊ መንግስት አልነበራትም። ይህንን ክፍተት ለማስተካከልና አንድ ጠንካራ ማእከላዊ መንግስት ለመመስረት በከፍተኛ ደረጃ የታገሉት ግን፣ ንጉሰ ነገስት አፄ ቴዎድሮስ ናቸው።

ይሁን እንጂ እሳቸውም ቢሆኑ፣ ዓላማቸው ቀስ በቀስ ተግባራዊ መሆኑ ባይቀርም በህይወት እያሉ ግን ይህንን ለማየት አልታደሉም። አፄ ቴዎድሮስ፣ በልባቸው ያደረው ብሩህ ራእይ ስላልተሳካላቸው ይመስላል፣ ከህዝባቸው ጋር የነበራቸው ግንኙነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየላላ ሄደ። በመጨረሻ ላይም ከውስጥም ከውጭም ችግሮች ተደራረቡባቸው።

ስለዚህ ጉዳይም ፀሓፌ ትእዛዝ ገብረስላሴ «ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ» በተባለው መፅሐፋቸው እንዲህ ይላሉ።

«አፄ ቴዎድሮስ፣ የወረሂመኖ ሰው መጥቶ ምኒልክን የተቀበለ መስሏቸው፣ በዚህ ነገር ተበሳጭተው፣ መቅደላ ታስረው የነበሩትን የወሎንና የወረሂመኖን ይማማውን፣ መኳንንቱንም እጃቸውን፣ እግራቸውን እየቆረጡ ገደል ሰደድዋቸው። በዚህም ሃይለ እግዚኣብሄር ከአፄ ቴዎድሮስ ተለየ። አብያተ ክርስቲያናትን ማቃጠል ጀመሩ። ሴቱንም፣ ወንዱንም፣

ህዝናቱንም እቤት እያገቡ አቃጠሉት። ላሙንም፣ በሬውንም፣ እየማረኩ በጦር በጐራዴ ያስደበድቡት ጀመር። ሰራዊቱም ይህንን እያየ በየስፍራው ተበተነ። አገሩም ሁሉ ሽፍታ ሆነ፣» በማለት ይገልፁታል። /ገፅ 55-6/

አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስም፣ «ዳግማዊ ምኒልክ» በተባለ መፅሐፋቸው፣ እንዲህ ይላሉ።

«አፄ ቴዎድሮስ ግን፣ አጤ ምኒልክ በከዱ በማግስቱ ተናደዱና ታስረው ከተቀመጡበት እያስጐተቱ፣ እያስወጡ፣ ብዙ ሰው በገደል አስጣሉ። የወይዘሮ ወርቂቱን ልጅም እናቱ ለምኒልክ አግዛ ለምን ሸሽጋ ሰደደችው ብለው በንዴት ገደል አስጣሉት» ይሉናል። /ገፅ 19/

ይህም ሆኖ ግን አፄ ቴዎድሮስ፣ ኩሩና ጀግና ኢትዮጵያዊ ንጉሰ ነገስት እንደነበሩ እናያለን። በመጀመርያ ደረጃ ቱርኮችን ቢያንስ በሐሳብ ደረጃ፣ ከቀይ ባሕር ዳርቻ አካባቢ ለማባረር ዓላማ ነበራቸው። ይህ ብቻ አይደለም፣ ግዛታቸው እስከ ኢየሩሳሌም ድረስ መስፋት እንዳለበትም ይመኙ ነበርና እንዲህ እየተባለ ይዘመርላቸው ነበር።

> «ታጠቅ ብሎ ፈረስ ካሳ ብሎ ስም፣
> ዓርብ ዓርብ ይሸበራል ኢየሩሳሌም፣
> አንተም ጌታ አይደለህ እኔም ሎሌ፣
> የኢየሩሴላም ሰው ካልጫነ በርሞሌ» የሚል

ይገኝበታል።

መቅደላ ላይ በጠላት በተከበቡበት ጊዜም፣ «የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት በጠላት እጅ ወደቀ መባል የለበትም» ብለው

ለኢትዮጵያ ህዝብና ለራሳቸው ዘለዓለማዊ ክብር ሲሉ ሸጉጣቸውን ጠጥተው በክብር አልፈዋል።

የአፄ ተክለጊዮርጊስ የሶስት ዓመት ዘመነ መንግስት እንዳለ ሆኖ፥ ከአፄ ቴዎድሮስ ቀጥሎ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ልዩ ስፍራ ይዞ የሚገኘው የአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግስት ነው።

አፄ ተክለጊዮርጊስ፣ ወዲያው እንደ ነገሱ፣ ለደጃዝማች በዝብዝ ካሳ «ከኔ ጋር መዋጋት አያዋጣህም። በሰላም ብትገባ ይሻልሃል» በማለት የሰራዊታቸውን ብዛት ለመግለፅ ብለው አንድ ስልቻ ጤፍ ሙሉ ላኩባቸው። ደጃዝማች በዝብዝ ካሳም፣ ያንን ጤፍ አሳርረው አስቆሉና፣ የኔ ነፍጥም ሰራዊትህን እንዲህ አድርጎ ያሳርረዋል፣ ለማለት ያረረውን ጤፍ እንደገና መለሱላቸው። የደጃዝማች በዝብዝ ካሳ እህት የሆኑት እቴጌ ድንቅነሽም ለባለቤታቸው ለአፄ ተክለጊዮርጊስ አንድ ትንቢት አዘል ግጥም በትግርኛ ቋንቋ አቅርበውላቸው ነበር። የእቴጌ ድንቅነሽ ትንቢታዊ ግጥምም፣

«ናይቲ ሸዋ ገፊሕ ኢዩ መንገዱ፣
ናይቲ ጐጃም ውን ገፊሕ ኢዩ መንገዱ፣
ናይቲ ጐንደር ገፊሕ ኢዩ መንገዱ፣
ናይቲ ወሎውን ገፊሕ ኢዩ መንገዱ፣
አንታ ንትግራይ አቢልኩም ግና ክይትኸዱ፣
ኣይከም ኩሉን ሀቢብ ኢዩ መንገዱ፣
ኣብቲ ማእኸል ዓድዋ እንድሕር ዓሪዱ፣
ብእሳተ ገሞራ ክይትነዱ፣

አባ በዝብዝ ካሳ ቀራዕ ኢዩ ክብዱ» የሚል ነበር።

ግጥሙ ወደ አማርኛ ሲመለስ፣

«ወደ ሸዋ፣ ጐጃም፣ ወደ ጐንደር፣ እንዲሁም ወደ ወሎ የሚወስደው መንገድ ሰፊ ነው። ወደ ትግራይ የሚወስደው መንገድ ግን፣ እንደሌሎቹ ሳይሆን ጠባብ ነውና፣ ወደዚያ መሄድ የለባችሁም። አባ በዝብዝ ካሳም ቀራጥ ነው። ዓድዋ እምብርቱ ላይ የመሸገ እንደሆነ፣ በእሳተ ገሞራ ትቃጠላላችሁ» የሚል መልእክት አለው።

ይሁን እንጂ ፉከራውም ዛቻውም ስላልሰራ፣ ጦርነት መደረጉ የማይቀር ሆነ። ስለሆነም ደጃዝማች በዝብዝ ካሳ ተንቤን አካባቢ «ዛልቃባ» በሚባለው ቦታ በመቆየት ነበር አፄ ተክለጊዮርጊስን ሊገጥሙዋቸው አስበው የነበረ። ነገር ግን በዝብዝ ካሳ «ጐርዞ ጊላ» (ወጣቶች) ምን ይላሉ? ብለው መረጃ ጠየቁ። ለዚሁ ጉዳይ የተላኩ ሰዎችም

«እንታይ ወሰደካ ንዛልቃባ፣
ዓድዋ'ዶ አይንሄካን እንካ ሃባ፣»

እየተባለ ይዘፈናል ብለው ሲነግሩዋቸው፣ «እንግዲያውስ ፈረሴን ወደ ዓድዋ መልስ» አሉና ጉዞዋቸውን ወደ ዓድዋ አቀኑ። በዚሁ ወቅት ከአፄ ተክለጊዮርጊስ ጋር የተሰለፈው ሰራዊት 60 ሺሕ ሲሆን የደጃዝማች በዝብዝ ካሳ ሰራዊት ደግሞ 12 ሺህ ብቻ ነበር። በዚሁም መሰረት ጦርነቱ ዓድዋ ከተማ ላይ ተደረገና በደጃዝማች በዝብዝ ካሳ ድል አድራጊነት ተገባደደ።

በወቅቱ ጦርነቱን በተመለከተ ቀርቦ የነበረው ግጥም ደግሞ፣

«ላባ በዝብዝ ግብር በቶሎ እንዲደርስ፣
ጥሬውን ጤፍ ቢልክ ተክለጊዮርጊስ፣
ስልቻው ተፈቶ ትግሬ ላይ ቢፈስ፣
አባ በዝብዝ ካሳ ቆላው እንደገብስ።

«የወንዱ አባ ታጠቅ ተቀባይ ሆነህ፣
ምነው በሶስት ዓመት ደከመ ሐይልህ፣
ባባ በዝብዝ ካሳ ታጥፎ ግንባርህ፣
ተሸከመህ ወርደህ አልጋህን ሰጠህ።

«በሙሉ ሶስት ዓመት የተሰራው አልጋ፣
ከሰቈጣ ወርዶ ትግሬ ተዘረጋ።
ለምን ትለኛለህ ሰቈጣ ሰቈጣ፣
ጥንቱን አይደለም ወይ ለአኩሱም የመጣ፣
ዛሬ ጊዜ አግኝቶ ከላስታ ቢወጣ»

የሚል ነበር። /ተክለፃድቅ መኩሪያ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ሃይለስላሴ ገፅ 51/

ቀደም ሲልም እንዲሁ፣ ደጃዝማች ሐይሉ የተባሉ የሐማሴን ገዥ ደጃዝማች በዝብዝ ካሳን ለመግጠም አስበው ነበር። ነገር ግን አቶ ዓንደዕዮን የተባለ ገጣሚ፣

«አንታ እዛ ዓድዋ ዓድዋ እትብልዋ፣
ክትመፀኩም ድያ ክትከድዋ፣
ሓንቲ ዓቕብ ኢያ ሓንቲ ሩባ፣
ሓደ ረፋድ ስግር ዘይትብልዋ።
አንታ እንዳድሙዶ ትኣቱ አንጭዋ፣

እንዳ ኣንበሳ'ኸ ይኣቱዶ ባዕዋ?» ብሎ ሲገጥምላቸው፣ ወደ ዓድዋ መጥተው እጃቸውን ለበዝብዝ ካሳ በሰላም ሰጡ:: ግጥሙ ወደ አማርኛ ሲመለስ፣

«ይህች ዓድዋ ዓድዋ የምትሉዋት፣ እናንተ ናችሁ ወደ እሷ የምትሄዱት ወይስ እስዋ ወደ እናንተ ትመጣለች? አንድ ወንዝና አንድ ዳገት እኮ ነው ያላት:: ለምን ተሻግራችሁ አትሄዱም::

ለመሆኑ ወደ ድመት ቤት አይጥ ትገባለች እንዴ? ወደ አንበሳ ቤትስ ጥጃ ይገባልን?» የሚል መልእክት አለው::

አፄ ዮሐንስም እንደ አውሮጳ ዘመን አቆጣጠር በ1872 ዓ.ም አክሱም ከተማ ላይ ነገሱ:: ነገር ግን ይህ ዘመን ለአፄ ዮሐንስ ጥሩ አልነበረም:: ኢትዮጵያ በየአቅጣጫው በጠላቶች የተከበበችበት ዘመን ነው የነበረ:: አፄ ዮሐንስም፣ አንድም ቀን ሳይደላቸው ነው፣ የኢትዮጵያን ዳርድንበር ለማስከበር፣ ከነዚህ ወራሪ ሃይሎች ጋር እየተፋለሙ ዘመነ መንግስታቸውን ያገባደዱት:: አፄ ዮሐንስ ወደ ስልጣን የመጡት፣ ኢትዮጵያ በተለያዩ ወራሪ ሃይሎች ተከባ በነበረችበት ወቅት ነበር ብለናል:: እነዚህ ወራሪ ሃይሎችም ዓላማቸውን ተግባራዊ የሚያደርጉት በሃይማኖት ሽፋን በሚላኩ ሚሲዮናውያን በኩል እንደ ነበር አይዘነጋም:: ይህም ከጐንደር ዘመነ መንግስት ጀምሮ ይጠቀሙበት የነበረ ስልት ነው:: በዘመነ አፄ ዮሐንስም እንዲሁ ብዙ ሚሲዮናውያን ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ነበር::

ከአፄ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግስት ጀምሮ ሚሲዮናውያን በሚፈጥሩት ሰበብ፡ በኢትዮጵያ የደረሰው አለመረጋጋትና ጦርነት ለአፄ ዮሐንስ የተሰወረ አልነበረም:: ስለሆነም ንጉሰ ነገስት

ዮሐንስ፣ በሚሲዮናውያን ላይ ከፍተኛ ጥርጣሬ ነበራቸው። ከዚህም የተነሳ ሚሲዮናውያኑን በሙሉ ከምድረ ኢትዮጵያ ለማስወጣት ወሰኑ።

ስለዚሁ ጉዳይም አቶ አስረስ የኔ ሰው «ትቤ አክሱም መኑ አንተ?» በተባለ መፅሐፋቸው እንዲህ ይሉናል።

«አፄ ዮሐንስ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩትን ሚሲዮናውያን፣ ከሸዋም አባ ማስያስን እና ተከታዮቹን ሁሉ አንድ ላይ እንዲሰበሰቡ አደረጉ። ከዚያም ወደሃገሬ ምን ልታደርጉ መጣችሁ?» ብለው እንደ ጠየቅዋቸው ያብራራሉ። ሚሲዮናውያኑም በበኩላቸው ወንጌልን ለማስተማር እንደመጡ መግለፃቸው አልቀረም። አፄ ዮሐንስም «እኔ ለሃገሬ ህዝብ የእጅ ስራና ጥበብ የሚያስተምሩ ሰዎችን እቀበላለሁ እንጂ እናንተን አልፈልጋችሁምና አገሬን ልቀቁልኝ» አሉዋቸው። /ገፅ 15-16/

«በዚሁም መሰረት ሚሲዮናውያኑ ከፊሎቹ በምፅዋ፣ ከፊሎቹ ደግሞ በመተማ በኩል ወደየሃገራቸው እንዲሔዱ ተደረገ። የተወሰኑት ደግሞ፣ በአሰብ በኩል አድርገው በሚስጢር ወደ አንኮበር መጥተው ተቀመጡ። ከዚህ በኋላም ሚሲዮናውያኑ፣ የንጉስ ምኒልክ ልብ ከአፄ ዮሐንስ ልብ የተለየ መሆኑን ተገንዘቡ» ይሉናል አቶ አስረስ የኔሰው። /ገፅ 16/

የሚሲዮናውያኑ አባባል ትክክል ነው። የንጉስ ምኒልክና የአፄ ዮሃንስ ልብ በፍፁም አይገናኝም። የአፄ ዮሃንስ ልብ ስለ ኢትዮጵያ ያስባል። ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና ዳርድንበር ይዋደቃል፣ ህይወቱንም አሳልፎ ይሰጣል። የንጉስ ምኒልክ ልብ ግን፣ ከአንኮበራዊ ብሄረተኝነትና ትምክሕት ውጭ አያስብም።

በአንኮበራዊ ስልጣንና ልዕልና ላይ ብቻ የታጠረ ነው። ሸዋዊ ብሄርተኝነት፣ በጥንታዊት ኢትዮጵያ ሃገራዊነት፣ ሉዓላዊነትና አንድነት አያምንም። አንኮበራውያን ትምክሕተኞች፣ ሸዋዊ ልዕልና የተረጋገጠበት ሰፊ ግዛት ቢኖራቸው ባይጠሉም፣ የነሱ ስልጣንና የበላይነት ያልተረጋገጠባት ኢትዮጵያን ከሚያዩ ግን፣ ውድቀትዋንና ጥፋትዋን ይመኛሉ። አንኮበር ላይ የመነጨው ትምክህሕታዊ ስርዓታቸውን ለማስጠበቅና ህልውናቸውን በዘላቂነት ለማረጋገጥም፣ ከማንም የኢትዮጵያ ጠላትና ወራሪ ሃይል ጋር ግንባር ፈጥረው አገርን ለማስማማት ወደ ኋላ አይሉም። ይህም ካሁን በፊትም በታሪክ የተረጋገጠ ነው። በሌላ አነጋገር ትምክሕተኞች፣ ስልጣንና የበላይነትን ማእከል ያደረገ ኢትዮጵያዊነትና ሃገራዊ ስሜት ብቻ ነው ያላቸው።

ኢትዮጵያዊ ሃገራዊነትንና ሸዋዊ ብሄረተኝነትን በተመለከተ ግን፣ አንድ ተጨማሪ አብነት እንይ። አቶ አታክልቲ እምባዬና አቶ ግርማይ ወልደጊዮርጊስ ወደ ትግርኛ ቋንቋ ለተረጐሙት «ኢትዮጵያን ኤርትራን አብ እዋን ምቅርማት አፍሪካ» ስለሚባለው የሃጋይ ኤርሊክ መፅሐፍ ዶ/ር አድሃና ሃይለ ሞያዊ አስተያየቱን ሲያስቀምጥ፣ እንዲህ ይላል።

«ከ1529-1632 ዓ.ም ባለው ጊዜ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ትከስቶ በነበረው ችግር ምክንያት የኢትዮጵያ ሃገራዊነትና መንግስትነት በሰሜን ኢትዮጵያና በኤርትራ አካባቢ ተወስኖ ነበር። በተለይ ከ1696 ዓ.ም በኋላ ግን፣ ሸዋ እራስዋን የቻለች ሃገር ሆና ብቅ አለች። ኢትዮጵያ ደግሞ መረብ ምላሽ /ደጋው ኤርትራ/፣

ትግራይ፣ ቤጌምድር /ጐንደር/፣ ጐጃም፣ ወሎ በከፊል በተለይ ዋግ፣ የጁንና ላስታን የሚያጠቃልል መንግስትና ሃገር ሆነች።

«የሸዋ ነገስታት፣ ከኢትየጵያ መንግስት ውጭ የሆነ መንግስትና አገር ማለትም /የሸዋ አገር መንግስት/ የመሰረቱና የሚመሩ ስለነበሩ፣ ፖለቲካዊ አመለካከታቸውም በሽዋነት የታጠረ እንደነበር ግልፅ ሆኖ መቀመጥ አለበት። ስለሆነም፣ የኢትዮጵያ ነገስታት የሆኑት አፄ ቴዎድሮስና አፄ ዮሐንስ፣ ኢትዮጵያን ማእከል አድርገው ሲንቀሳቀሱ፣ ሸዋንም በውዝፍ እንደቀረች የኢትዮጵያ አካል አድርገው ያዩዋታል። የሸዋ መሪዎችም በበኩላቸው፣ ሸዋን ማእከል አድርገው ይንቀሳቀሳሉ። ውሎ አድሮ ደግሞ፣ ኢትዮጵያ የሸዋን ጥቅም እንደምትሻማ አገርና መንግስት አድርገው ይመለከትዋታል» በማለት ነው፤ ዶ/ር አድሃና ታሪኩን የሚያስቀምጠው።

ስለሆነም ይህ አንኮበር ላይ የፈለቀው ምኒልካዊ ትምክህተኛ ሃይል፣ በአሁኑ ወቅትም ቢሆን ፀረ አንድነትና ፀረ እኩልነት ስርዓቱን በኢትዮጵያ ህዝቦች ጫንቃ ላይ ዳግም ለመጫን ሌትና ቀን እየተንገታገተ ነው። ነገር ግን ይህ ፀረ ሰላም፣ ዐረ እድገትና ፀረ እኩልነት ሃይል፣ በወቅቱ ካልከሰመ፣ የኢትዮጵያ ህዝቦች ህልውና አደጋ ላይ መውደቁ አይቀርም። ይህ ትምክሕተኛ ሃይል፣ በኢትዮጵያ ህዝቦች ሰላማዊ ህይወትና እድገት አይጠቀምም። ስለሆነም ከተለያዩ የኢትዮጵያ ጠላቶችና ወራሪ ሃይሎች ጋር በመመሳጠር የኢትዮጵያን ህዝብ ላለፉት አንድ መቶ ዓመታት ለእርስበርስ ጦርነት እና እልቂት፣ ለረሃብና

ለቸነፈር እንዲሁም ለውጭ ወረራና ለኋላ ቀርነት በመዳረግ የዓለም ህዝብ መሳቅያና መሳለቅያ እንዲሆን አድርጎት ቆይቷል።

## ምዕራፍ ሁለት

# አፄ ዮሐንስና የግብፅ ወራሪ ሐይል

አፄ ዮሐንስ፣ ኢትዮጵያ የምትባለውን ጥንታዊት አገር አፈራርሰው፣ ለመቀራመት ያሰፈሰፉ አራት ጠላቶች ነበርዋቸው። እነሱም

የግብፅ መንግስት፣

ኢጣልያ፣

ድርቡሽ እና

ንጉስ ምኒልክ ናቸው።

በመጀመርያ ደረጃ ኢትዮጵያን ለመውረር የተንቀሳቀሰው ግን፣ የግብፅ መንግስት ነበር። ግብፃውያን፣ ስልጣን ለመጨበጥ ከፍተኛ ፍላጎትና ጉጉት ከነበራቸው ከንጉስ ምኒልክ ጋር ልዩ ምስጢራዊ ግንኙነት መስርተው ነበር። የግብፅ መንግስት ዋና ዓላማ ግን ከመረብ ወንዝ በስተሰሜን ያሉትን አካባቢዎችንና የቀይ ባሕርን ጳርቻ መቆጣጠር እንጂ፣ ኢትዮጵያን በመላ ለመያዝ አልነበረም። ይህ ግን አፄ ዮሃንስን የመሰለ በሃገራዊ ፍቅር የተነደፈ ኢትዮጵያዊ ንጉሰ ነገስት በስልጣን ላይ እያለ ሊሳካ እንደማይችል ለግብፃውያን የተሰወረ አልነበረም። በመሆኑም ከዲቭ እስማኤል፣ «የግብፅ ዓላማ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ስልጣን ከአፄ ዮሐንስ እጅ ወጥቶ ደቡብ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙት በንጉስ ምኒልክ እጅ

ሲገባ ብቻ ነው» የሚል ፅኑ እምነት ነበረው። /ሃጋይ ኤርሊክ ገፅ 14/

ስለሆነም አፄ ዮሐንስን ከስልጣን አስወግዶ ዓላማውን ለማሳካት በ1875 ዓ.ም በሰሜን ኢትዮጵያ ጦርነት ከፈተ። አፄ ዮሐንስም ወራሪውን የግብፅ ጦር ለመመከት ክተት ሰራዊት ምታ ነጋሪት ብለው አወጁ። የግብፅ ጦርም ወደፊት እየገፋ መጣ። በዚህ ወቅት በአሉላ አባ ነጋ የሚመራው የሰሜን ኢትዮጵያ ሰራዊት፣ ሕዳር 14 ቀን 1875 ዓ.ም መረብን ተሻግሮ ወደ ፊት ገሰገሰ። ሕዳር 16 ቀን 1875 ዓ.ም ደግሞ ጉንዳጉንዲ ላይ ውጊያ ተጀመረ። ጀግናው የሰሜን ኢትዮጵያ ሰራዊትም ከወራሪው የግብፅ ጦር ጋር አንገት ላንገት ተያይዞ ተፋፋመ። ድሉም የአፄ ዮሐንስ ሰራዊት ሆነ። በዚሁ ወቅት ሶስት ሺሕ ከሚሆን የግብፅ ጦር ውስጥ በህይወት ያመለጡት ጥቂቶች ናቸው። በዚህ ጦርነት ላይ የሐማሴኑ ባላባት ደጃዝማች ወልደሚካኤል ሰሎሞንም ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። ከጉንዳጉንዲ ጦርነት በኋላ ደግሞ «ሻግያ ሻግያ፣ ዓመት ዝበልካያስ ረፋድ ኢያ» እየተባለ ይዘፈን ነበር።

ሃጋይ ኤርሊክ የተባለ እስራኤላዊ የታሪክ ባለ ሞያ፣ አቶ አታክልቲ እምባየና አቶ ግርማይ ወልደጊዮርጊስ ወደ ትግርኛ ቋንቋ በተረጎሙት «ኢትዮጵያን ኤርትራን አብ እዋን ምቅርማት አፍሪካ» በተባለ መፅሐፉ፣ ይህን አስመልክቶ ሲፅፍ፣ «አፄ ዮሐንስ የግብፅን ወረራ ለመመከት በሚዘጋጁበት ወቅት ታላላቆቹ የኢትዮጵያ መሪዎች ከነዚሁ መሃከልም የሸዋው ንጉስ ምኒልክና

የጐጃሙ ራስ አዳል አደጋውን ለመመከት አልተባበርዋቸውም» ይላል። /ገፅ 14/

አቶ አፈወርቅ ገብረኢየሱስም «ዳግማዊ ምኒልክ» በተባለ መፅሐፋቸው እንዲህ ይሉናል።

«መቸም የምኒልክ ልማድ ለመስጠት አይገመግምምና ለፍቅር ብለው ብዙ ፈረስና በቅሎ ላጤ ዮሐንስ ላኩ። አጤ ዮሐንስ ግን ያጤ ምኒልክን ለጋስነት ማድነቅ ትተው የፍርሃት መስላቸውና ተደፋፈሩ። በላይ እኔ ነኝ አሉ።

«አጤ ምኒልክ በዚህ ተናደዱና ዋና ዋና መኳንንቶቻቸውን ሰብስበው ነገሩን አማከሩ። የሸዋ መኳንንት ሁሉም፣ ተሁሉ ሁሉ ራስ ዳርጌ፣ ራስ ጉበና፣ እነደጃች ገርማሜ፥ እንዋጋ፥ ይዋጣልን፥ እናስገብራለን እንጂ፣ ለትግሬ አንገብርም አሉ። ነገሩ በዚህ ተቆረጠ። አጤ ምኒልክ ከዚህ ወዲያ ከምስር ንጉስ ጋር ተላላኩ። የምስር ንጉስም አጤ ዮሃንስን ለመውጋት ብዙ ጦር ላከ። ባንድ ወገንም ባውሳ በኩል ብዙም አይባልም በመጠኑ ጦር ላጤ ምኒልክ ኢጋዥ ብሎ ካለቃ ብሩ ጋር ወደ ሸዋ ሰደደ። አጤ ዮሐንስም በቱርክ መምጣት ደንግጠው የድፍን ኢትዮጵያን ጦር ባዋጅ ክተት አሉ። ወደ አጤ ምኒልክም ነገሩን ሳያውቁ እባክዎ ይገዙኝ ብለው ላኩ። የምስር ጦርም ጉንዳጉንዲ ደረሰና ምሽጉን አበጀ። አፄ ዮሐንስ ግን ከሸዋ በቀር የድፍን አበሻን ጦር አስከትለው ተዋጉና ለወሬ አንድም ሳይ ቀር ቱርክን እንደካንቻ መቱት። ካለቃ ብሩ ጋር ባውሳ የመጣውም የምስር ጦር ያውሳው ንጉስ መሐመድ አንፋሪ ወዳጅ መስሎ፣ ፍሪዳውን ወተቱን ሰጥቶ፣ እንግድነት ተቀብሎ ኣሳድሮ ሲአቆም፣ ሌሊት ምንም የለብን

ብሎ ከተኛበት ለዘር ሳይቀር አርዶ አርዶ ጣለው» በማለት በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ ይገልፁታል:: /ገፅ 23/

እዚህ ላይ መገንዘብ የሚያስፈልገው፣ የሸዋው ንጉስ፣ ገና ከጧቱ ጀምረው፣ ከኢትዮጵያ ደመኛ ጠላቶች ጋር ግንባር በመፍጠር ኢትዮጵያን ለማፈራረስና አንድነቷን ለማናጋት ሲያሴሩ መቆየታቸውን ነው::

ይህ በእንዲህ እያለ የግብፅ መንግስትም ጉንዳጉንዲ ላይ የደረሰበትን ሽንፈት ለመበቀል ከፍተኛ ዝግጅት ሲያደርግ ቀይቶ፣ ካንድ ዓመት በኋላ በ1876 ዓ.ም መጋቢት ወር ላይ ጦሩን ወደ ጉራዕ አዘመተ:: አፄ ዮሐንስም የሸዋው ንጉስ ምኒልክና የጐጃሙ ራስ አዳል እንደከድዋቸው ቢገነዘቡም፣ ምንም ዓይነት የመንፈስ መረበሽ ሳይሰማቸው፣ በሰሜን ኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ብቻ ተማምነው ወራሪውን የግብፅ ጦር ለመመከት ወሰኑ::

በዚህም መሰረት በአሉላ አባነጋ የሚመራው የአፄ ዮሐንስ ሰራዊት ከመጋቢት 7-9፣1876 ዓ.ም በተደረጉ ተከታታይ ጦርነቶች ወራሪውን የግብፅ ጦር እንዳልነበረ አደረገው:: 5200 ከሚሆነው የግብፅ ሰራዊት ውስጥም 1900 ብቻ ነው ከሞት ያመለጠው:: ደጃዝማች ወልደ ሚካኤል ሰሎሞን ግን፣ በዚሁ ጦርነት ከወራሪው የግብፅ ጦር ጐን ነበር የተሰለፉት::

ከዚህ በኋላ አሉላ አባነጋ፣ የኢትዮጵያን ህዝብ አይበገሬነት ስላስመሰከሩ «የጉራዕ አንበሳ» እየተባሉ ይጠሩ ጀመር ይላል ሃጋይ ኤርሊክ ቀደም ብዬ በጠቀስኩት መፅሐፉ:: /ገፅ 16-17/

በዚህ ወቅትም፣ «ማፋሽ ማፋሽ ዝብል ንሱ፣ ብጉራደ በሎ ርእስ ርእሱ» እየተባለ ይዘፈን ነበር። ከጉንዳጉንዲና ከጉራዕ ጦርነት በኋላ ቀርቦ የነበረው መወደስ ቅኔም ይህ ነበር።

# መወድስ ቅኔ

«ቱርክ ለጉራዕ ምስለ ጒዳጉዲ፣
ኲዓትካያ ቅድመ
ከመትኩን መቃብርካ፣
አኮኑ መፃእካ
እንዘትሐድግ ሃገርካ፣
ወንጉስ አመበኲናት
ገቦከ ወግአካ፣
ለዝብእ ወሃበካ፡፡

ማየሂ ፀዊረከ
በዘገቦከ ታኒካ፣
ለልቁማ አክሊለ ወርቅ
በርእስከ ተቀፀልካ
ወለሰናዲር ሐይልከ
አመበጥይት ለጐምካ፣
ትግራይ ሓሸከር ወሬሳ፣
በይእቲ አቅመሰካ፡፡»

ወደ አማርኛ ሲመለስም

«ሰማህ ወይ ቱርክ፣ አገርህን ትተህ ስለመጣህ እኮ ነው ጉራዕንና ጒዳጉድን /ጉንዳጉንድን/ መቃብርህ ይሆኑ ዘንድ አስቀድመህ የቆፈርካቸው፡፡ ንጉሰ ነገስት ዮሐንስም፣ ወገብህን በጦር ወግቶ ለጅብ ዳረገህ፡፡

ወገብህ ላይ ባለችው ታኒካ ወሃ ከተሸከምክ በኋላ ደግሞ፣ የወርቅ አክሊል የሆነችው ልቁማህን/መለዮ/ በራስህ ላይ አደረግሃት። የሐይልህ ምንጭ የሆነችው ሰናዲርህን ጥይት ባጐረስካት ጊዜም፣ የወሬሳው ካሳ ተከታይ የሆነው የትግራይ ህዝብ በዚያቺው አድርጎ ደቆሰህ» የሚል መልእክት ነው ያለው።

# ምዕራፍ ሶስት

# የዶግዓሊ ጦርነትና ውጤቱ

እስቲ በቅድሚያ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም፣ ምን እንዳሚሉን እንስማ::

«አፄ ምኒልክ፣ ቢያንስ ትግራይን ከኢጣልያ ቅኝ ተገዥነት አዳኑ፤ ኤርትራን ለምንና እንዴት ለኢጣልያ ተውት? የሚለውን ጥያቄ ውስብስብና አከራካሪ ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን አንድ ሌላ ጥያቄም በግድ መቅረብ አለበት:: አንድ ሺህ ኪሎ ሜትር ተጉዘው የተዋጉትን ከመውቀስ የአካባቢው ሰዎች ኢጣልያን ከትግራይም ሆነ ከኤርትራ ለማስወጣት ምን እንቅስቃሴ አድርገው ነበር? ብሎ መጠየቅና መልሱንም ማግኘት ተገቢ በሆነ ነበር» በማለት ይጠይቃሉ:: /የከሕደት ቁልቁለት ገፅ 45/

የፕሮፌሰር መስፍንን ፅሑፍ ስመለከት አንድ ነገር ትዝ አለኝ:: የነጋድራስ ገብረህይወት ባይከዳኝ አባባል::

«ታሪክን መማር ለሁሉም ሰው ይበጃል:: የታሪክ ትምህርት ግን የሚጠቅም የእውነተኛ ታሪክ ትምህርት ሲሆን ነው:: እውነተኛውን ታሪክ ለመፃፍም ቀላል ነገር አይደለም:: የአገራችን ታሪክ ፀሐፊዎች ግን፣ በነዚህ ላይ ሐጢአት ይሰራሉ:: በትልቁ ነገር ፈንታ ትንሹን ይመለከታሉ:: በእውነት መፍረድንም ትተው በአድልዎ ልባቸውን ያጠባሉ» ይሉናል፣ «አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ» በተባለ መፅሐፋቸው:: ይህም በቀጥታ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያምን ይመለከታል::

ፕሮፌሰር መስፍን እውነትን አይወዱም። ከእውነት የራቀና የተሳሳተ መልእክት ነው የሚያስተላልፉት። አፄ ምኒልክ የትግራይ ትግርኚ ህዝብ፣ ዳርድንበሩን ለማስከበር ለዓመታት የከፈለውን መስዋእትነት ደመከልብ ሆኖ እንዲቀር ያደረጉ የኢጣልያ ወራሪ ሃይሎች አጋር መሆናቸው ለማንም ግልፅ ነው። እንደ ፕሮፌሰር መስፍን አባባል ከሆነ ግን፣ የትግራይ ህዝብ ከቅኝ ተገዥነት የዳነው በአጤ ምኒልክ ጀግንነት መሆኑ ነው። ይህም ሊሆን የቻለው የትግራይና የኤርትራ ህዝቦች የኢጣልያን ወራሪ ሃይል ለመመከትና ካገራቸው ለማባረር ሙከራ ባለማድረጋቸው፣ አፄ ምኒልክ ይህን ህዝብ ለመታደግ ሲሉ የአንድ ሺህ ኪሎሜትር መንገድ ተጉዘው ቢያንስ የትግራይን ህዝብ ከቅኝ ገዥዎች ቀንበር ስር አድነውታል ነው፤ የሚሉን የኛው ፕሮፌሰር።

እስቲ ለማንኛውም ግን፣ የትግራይ ትግርኚ ህዝብ፣ ዳርድንበሩንና ሀልውናውን ለማስከበር ከወራሪው የኢጣልያ ጦር ጋር ሲፋለም ለዓመታት የከፈለውን መስዋእትነትና፣ ዓለምን ያስገረሙ ድሎቹን እንመልከት።

ንጉስ ምኒልክ የትግራይ ትግርኚን ህዝብ በሃይል አንበርክከው ስልጣን ለመጨበጥ እንደማይችሉ እርግጠኛ ነበሩ። የግብፅ መንግስትም እንዲሁ፣ ቀደም ብለን እንዳየነው አፄ ዮሐንስ ስልጣን ላይ እስካሉ ድረስ ከሰሜን ኢትዮጵያ መሬት ቁርሶ ለመያዝ አይቻልም፣ የሚል ፅኑ እምነት እንደነበረው አይተናል። ለዚህም ነው፣ ንጉስ ምኒልክና የግብፅ መንግስት አፄ ዮሐንስን በሃይል ለማስወገድ ግንባር ፈጥረው የተንቀሳቀሱት።

ነገር ግን የንጉስ ምኒልክና የግብፅ ሴራ ጉንጳጉንዲና ጉራዕ ላይ በተደረጉ ጦርነቶች ምክንያት ግቡን ሳይመታ ከሸፈ። የግብፅ መንግስትም፣ ምፅዋንና አካባቢዋን ለኢጣልያ ወራሪ ሃይሎች ለቀቀላቸው። ንጉስ ምኒልክም፣ የትግራይ ትግርኚን ህዝብ በማዳከም ስልጣን ለመጨበጥ የሚያስችላቸው ሌላ የውጭ ጌታ ማፈላለጋቸውን ቀጠሉ።

አቶ አስረስ የኔሰው፣ ከላይ በጠቀስኩት መፅሓፋቸው ስለዚሁ ጉዳይ የሚሉት አላቸው። «ንጉስ ምኒልክ በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ጥር 14 ቀን 1875 ዓ.ም ከአፄ ዮሐንስ ተደብቀው የአሰብን በር እንዲሁም ንግድንና ወዳጅነትን የሚመለከት ውል፣ የሸዋ፣ የከፋ፣ የጋላ ሁሉ ንጉስ ምንሊክ፣ በሚል ከኢጣልያ መንግስት ጋር አንኮበር ላይ ተፈራረሙ» ይላሉ። /ገፅ 19/ እንግዲህ ከላይ እንዳየነው፣ ንጉስ ምኒልክ ከግብፅ መንግስት ብቻ ሳይሆን ከኢጣልያ ወራሪ ሃይል ጋርም ቢሆን ቀደም ብለው የመሰረቱት ምስጢራዊ ግንኙነት ነበራቸው። የኢጣልያ ጦርም ከምፅዋ ተነስቶ ሰሐጢ ላይ መመሸጉ ተሰማ። የአሉላ አባ ነጋ ሰራዊትም በዚሁ ወቅት ነበር የደርቡሽን ወራሪ ሃይል ኩፊት ላይ ድባቅ የመታው። ሰሓጢም ለአሉላ አባ ነጋ አዲስ አልነበረችም። የግብፅ ጦር ለሶስተኛ ጊዜ በአሉላ ሰራዊት የተመታውም ሰሐጢ ላይ ነው የነበረው። የኢጣልያ ወራሪ ሰራዊትም ተመሳሳይ ቅጣት ለመቀበል ነው እየተክለፈለፈ ወደ ሰሐጢ የመጣው። ጦርነቱን በሰለማዊ መንገድ ለመፍታት የተደረጉ ሙከራዎችም ነበሩ። ነገር ግን አልተሳኩም። ምክንያቱም የአፄ ዮሐንስና የኢጣልያኖች ልብ አይገናኙም።

ኢጣልያኖች አፄ ዮሐንስን በማግባባት መሬት ለመያዝ ነው ፍላጎታቸው:: አፄ ዮሐንስ ግን ለስልጣንና ለጥቅም ሲባል አገርን አሳልፎ የመስጠት ባህሪ አልነበራቸውም:: ስለሆነም ሊስማሙ አልቻሉም::

ሃጋይ ኤርሊክ የተባለ የታሪክ ባለሞያ ቀደም ብዬ በጠቀስኩት መፅሐፉ እንደሚለው፣ አፄ ዮሐንስ ከኢጣልያኖች ጋር ስለሚያደርጉት ውይይት ሲናገሩ «እነሱ ጥሩ እምነት ያላቸው አይደሉም:: አታላዮች ናቸው:: ኢጣልያኖች፣ ወደዚህ የመጡት ሃገራቸው ውስጥ መናፈሻና ጮማ ስላጡ አይደለም:: ነገር ግን እራሳቸውን ለማሻሻል ብለው ነው የመጡት:: ምክንያቱም ከመሃከላቸው ብዙ ድሆች አሉዋቸው:: ስለሆነም በእግዚአብሄር ሃይል በዓለም ፊት ተዋርደውና አፍረው ወደ አገራቸው ይመለሳሉ» ብለዋል ይለናል:: /ገፅ 122/

አፄ ዮሐንስ ይህን ያሉበት ዋናው ምክንያት ኢጣልያኖች የምፅዋ ዳርቻ ቃጠሎ ስለሆነብን ከደጋው አካባቢ ትንሽ ቦታ ይስጡን ብለው ስለጠየቅዋቸው ነው:: የአፄ ዮሐንስ መልስ ግን አጭር ነበር:: ቀልዳችሁን ተዉት የሚል ነው:: ኢትዮጵያዊ ሃገራዊነት ማለትም ይህ ነው:: በሃገሩና በህልውናው ላይ አይደራደርም:: ለውጭ ወራሪዎችም አያጐበድድም:: እስቲ ቀጥለን ደግሞ ሌላ የኢትዮጵያዊ ሃገራዊነት መገለጫ እንይ:: ፀሐፊ ትእዛዝ ገብረስላሴ «ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ንጉሰ ነገስት ዘኢትዮጵያ» በተባለው መፅሐፋቸው ሲተርኩ፣

«ኢጣልያኖች ሰሐጢ ከሚባል አገር ወጥተው እርድ አበጅተው ቆይተው ነበር:: አፄ ዮሐንስም አገሬን ለቃችሁ ሂዱ

አልዋቸው:: ከአውሬማ ሰው አይሻልምን? ውድማችሁን አቅንተን እንኑር ይፍቀዱልን ቢሉ አፄ ዮሐንስም እኔስ ካገሬ ጥርኝ አፈርም አለሰጥም፣ እናንተም ባገራችሁ ኑሩ ተነሱልኝ» አሉዋቸው ይላሉ:: /ገፅ 221/

ይህ ነው እንግዲህ ኢትዮጵያዊ ሃገራዊነት ማለት:: ኢትዮጵያዊ ሃገራዊነት በተግባር እንጂ በፉከራ፣ በቀረርቶ፣ በሽለላና በማስመሰል አይገለፅም:: ኢትዮጵያዊ ሃገራዊነት የትግራይ ህዝብ የማንነት መገለጫ ነው:: የትግራይ ህዝብ፣ ታሪክ እንደሚያረጋግጠው ለኢትዮጵያዊነቱ፣ ለርስቱ፣ ለዳርድንበሩ፣ እና ለሃገራዊ ክብሩ ሲል ህይወቱን ሳሳልፎ ይሰጣል:: እንደ ትምክሕተኞች ስልጣን ለመጨበጥ ሲባል አንድ ክፍለ ሃገር ሙሉ ሸንሽኖ ለወራሪ ሐይሎች ገፀበረከት አያቀርብም:: ለዚህም ነው አንከበራውያን ትምክሕተኞች፣ የኢትዮጵያዊ ሃገራዊነት እና አንድነት ፀር ናቸው የምንለው:: አንከበራውያን ትምክሕተኞች፣ የኢትዮጵያ ሃገራዊነት ፀር ብቻም አይደሉም፤ የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰብ ፀርም ናቸው:: ባጭሩ አንከበራውያን ትምክሕተኞች፣ አስመሳዮች ናቸው:: አንከበራውያን ትምክሕተኞች ጉረኞች ናቸው:: አንከበራውያን ትምክሕተኞች ፈሪዎች ናቸው:: አንከበራውያን ትምክሕተኞች አስመሳዮችና ተመፃዳቂዎች ናቸው:: ስለኢትዮጵያ አንድነት፣ ስለኢትዮጵያ ዳርድንበር፣ ስለኢትዮጵያ ባንዴራ፣ ስለ ኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ ሲመፃደቁ ግን፣ ከነሱ ወዲያ ጀግና፣ ከነሱ ወዲያ ሳገር ተቆርቋሪ፣ ከነሱ ወዲያ ታሪክ ሰሪ፣ ከነሱ ወዲያ ጥሩ ኢትዮጵያዊ ያለ አይመስላቸውም::

ወደ ሰሐጢ ታሪክ እንመለስ:: ኢጣልያኖች፣ ከአፄ ዮሐንስ በቀረበላቸው ማስጠንቀቂያ መሰረት ሰሐጢን ለመልቀቅ ፈቃደኞች አልሆኑም:: ስለዚህ የሐይል እርምጃ መወሰድ ነበረበት::

በዚሁም መሰረት ሃጋይ ኤርሊክ እንደሚለው፣ አፄ ዮሃንስ ታሕሳስ 23 ቀን 1887 ዓ.ም ለንግስት ቪክቶርያ አንድ ደብዳቤ ልከው ነበር:: መልእክቱም «በመሃከላችን ሰላም ለማውረድ ፍላጎት ቢኖርዎት፣ እነሱ በሃገራቸው፣ እኔም በሃገሬ እያለን ማድረግ ይቻል ነበር:: አሁን ግን በሁለቱም በኩል ፈረሶቹ ተጭነዋል:: ጉራዴዎቹም ካፎታቸው ተመዘዋል:: እንደ አሸን የበዙት ወታደሮቼም ጦራቸውን ይዘው ተዘጋጅተዋል:: የጣልያኖች ፍላጎትም ጦርነት ነው:: ፍላጎታቸውን ይፈፅሙ:: በህይወት እስካለሁ ድረስ ከነሱ ተደብቄ ወደ ጉድጓድ አልገባም» ይላል:: /ገፅ 156/

ከአፄ ዮሐንስ ደብዳቤ ብዙ የምንማረው ነገር አለ:: ይሄውም፣ የትግራይ ህዝብ በሃገሩና በሉዓላዊነቱ አይደራደርም:: በወራሪዎች ዛቻም ልቡ አይፈታም:: ለሃገርና ለወገን የሚተርፍ የታሪክ ጠባሳን ትቶ ከሚያልፍ፣ ዘለዓለማዊ ክብር የሚያጐናፅፍ የህይወት መስዋእትነት መክፈልን ይመርጣል::

የራስ አሉላና የኢጣልያ ወራሪ ሃይል ፍጥጫ አሁንም እንደቀጠለ ነው:: በመሆኑም ራስ አሉላ፣ ለጄኔራል ጄኔ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ሲፅፉ «ዊዓ ላይ የመሸገውን ሰራዊትህ እስከ ጥር 21 ቀን 1887 ዓ.ም ከዚያ ቦታ እንዲወጣ:: ዙላ ውስጥ ያለው ሰራዊትህም በአንድ ወር ውስጥ ማለትም እስከ የካቲት 26

ቀን 1887 ዓ/ም ድረስ ቦታውን ለቆ ይውጣ። ግንኙነት ለመቀጠል ይህ መደረግ አለበት። ይህ ሳይፈፀም ግን ግንኙነት የሚሉት ነገር አይኖርም» በማለት ነበር ያስጠነቀቁት። ይህም ሃጋይ ኤርሊክ የተባለ የታሪክ ባለሞያ እንደሚገልፀው መሆኑ ነው። /ገፅ 138/

ሃጋይ ኤርሊክ እንደሚለን ኢጣልያኖች ከአሉላ አባ ነጋ ብቻ አይደለም ማስጠንቀቂያ የተፃፈላቸው። አፄ ዮሐንስም ጥር 26 ቀን 1887 ዓ.ም ለጄኔራል ጄኔ አንድ ደብዳቤ ፅፈውለት ነበር። የደብዳቤው ዋና ቁምነገርም፣

«መጀመርያ ዊዓን ተቆጣጠርክ። አሁን ደግሞ ምሽግ ለማነፅ ወደ ሰሐጢ መጣህ። ያአካባቢ የኔ መሬት አይደለም እንዴ? ስለሆነም ካገሬ መውጣት አለብህ» የሚል ነው። «ኤርሊክ» /ገፅ 141/

የኢጣልያ ወራሪ ሃይል ግን በትዕቢት ስለተወጠረ፣ የተላኩለትን ማስጠንቀቂዎች ለመቀበል ዝግጁ አልሆነም። በመሆኑም የአሉላ አባ ነጋ ሰራዊት፣ ጥር 25 እና 26 ቀን 1887 ዓ.ም ሰሐጢና ዶግዓሊ በሚባሉ ቦታዎች ላይ መሽጎ የነበረውን የኢጣልያ ጦር ለወሬ ነጋሪ ሳያስቀር ደመሰሰው። በሁለት ቀን ውስጥም ከ 500 የማያነስ የኢጣልያ ጦር ነው ያለቀው።

አቶ አስረስ የኔሰው «ትቤ አክሱም መኑ አንተ?» በተባለ መፅሐፋቸው ጦርነቱን አስመልክተው የሚሉት አላቸው።

«ራስ አሉላ አባነጋ ሰሓጢ ላይ የመሸገውን የኢጣልያ ጦር፣ ጥር 25 1887 ዓ.ም ነው የከበቡት። ከዚያም ለረዳትነት ይመጣ የነበረውን 500 የኢጣልያ ጦር፣ ጥር 26 ቀን 1887 ዓ.ም ተደዓሊ ላይ አድፍጠው ቆይተው መቱት። የጦርነቱ ወሬ ሮማ

ከተማ በተሰማ ጊዜም ከፍተኛ ሐዘንና ድንጋጤ ሆነ። ኢጣልያኖችም፣

«ከሰው ሁሉ እንደ አበሻ ከአውሬ ሁሉ እንደ አንበሳ ጨካኝ ፍጥረት አላየንም» እያሉ አለቀሱ ይሉናል። /ገፅ 21/

አዎን ኢጣልያኖች ትክክል ናቸው፤ አልተሳሳቱም የኢትዮጵያ ህዝብ ህልውናውን ለማጥፋት ለሚመጡበት ሁሉ ምሕረት አያደርግላቸውም። ካልነኩት ግን አይነካም። ደግነቱ የተመሰከረለት ህዝብ ነው።

የዶግዓሊ ጦርነት፣ ኢጣልያኖችን ብቻ ሳይሆን አውሮጳውያንን በሙሉ ነው ያስደነገጠው። በመሆኑም አፄ ዮሃንስ የጦርነቱን ሁኔታ ለእንግሊዝ መንግስት መግለፅ ነበረባቸው። በዚሁም መሰረት መጋቢት 7ቀን 1887 ዓ.ም ለንግስት ቪክቶርያ በፃፉት መልእክት፣

«ኢጣልያኖች፣ ግብፆች ወደ ነበሩበት ቦታ መጡ። ይህንን ቦታ እንደይዘዋለን ቢሉም፣ በመሬቴ ላይ ምን አላችሁ? አልኳቸው። ከዚያ በኋላ በሐይል ገብተው በሁለት ቦታ ላይ ምሽግ መሸጉ። ቀጥሎም ራስ አሉላ በሰው ቤት ምንታደርጋላችሁ? ብሎ ሊጠይቃቸው ሂደ። የኢጣልያ ሰራዊት አዛዥም ጦርነት እንዲደረግ ትእዛዝ ሰጠ። አሉላም ተዋጋ» በማለት በወቅቱ ስለነበረው ሁኔታ ግልፅ አድርገውላቸዋል፣ ይለናል ሃጋይ ኤርሊክ። /ገፅ 142/

ዶግ ዓሊ ላይ በተፈፀመው አሰቃቂ ጭፍጨፋ ምክንያት የሰለጠነው ዓለም በሙሉ እንደተቆጣና እንደተገረመ ለአፄ ዮሐንስ ነግሬያቸው ነበር የሚለው ደግሞ፣ ፓርታል የተባለው እንግሊዛዊ

ነው። በሃጋይ ኤርሊክ አባባል አፄ ዮሐንስ ለዚህ የሰጡት መልስ የማያሻማ ነው የነበረው። «አሉላ ስሕተት አልፈፀመም። ኢጣልያኖች፣ እሱ ወደሚያስተዳድረው ክልል መጡ። እሱ ደግሞ ወጋቸው። ይህ ደግሞ፣ አበሾች ወደ እንግሊዝ አገር ከመጡ አንተም የምታደርገው ነገር ነው» በማለት መልሰውልኛል ይላል። /ገፅ 155/

ይህ በእንዲህ እያለ ኢጣልያኖች አሁንም አልተኙም። ደማቸውን ለመበቀል እያውጠነጠኑ ናቸው። ሰሓጢ አካባቢ ትንሽ መሬት ይሰጠን የሚል ጥያቄም እያቀረቡ ነው። አሉላ አባ ነጋ፣ ለኢጣልያኖች የሰጡት መልስ ግን አጭር ነበር።

«ኢጣልያኖች ወደ ሰሐጢ የሚመጡት፣ እኔ የሮማ ገዥ ስሆን ብቻ ነው። ሃይሌን አንዴ አሳይቻቸዋለሁ። ካላረፉም እደግማቸዋለሁ» በማለት ነበር የትግራይ ትግርኚ ምድር፣ ያበሻ ዳርድንበር፣ የኢትዮጵያ ክብር፣ የማይ-ደፈር መሆኑን ያረጋገጡላቸው። «ኤርሊክ» /ገፅ 153/

ነገር ግን ለምድነው ትምክሕተኞች ሁሉጊዜ ሐቅን ቀብረው ውሸትን የሚያሰራጩት? ለምንድን ነው 100 ዓመት ሙሉ በትግራይ ህዝብ ላይ መርዝ እየረጩ የሚኖሩት? ወደዉ አይደለም። አሉ የሚባሉ የዓለም ሐኪሞች ቢሰበሰቡም የተበከለ አእምሮዋቸውን ለማዳን አይችሉም። በዘር ጥላቻና በትምክሕት የተበከለና የሻገተ አእምሮም መድሐኒቱ መቃብር ብቻ ነው።

# የዶግ ዓሊ ጦርነትን አስመልክቶ ለራስ አሉላ አባ ነጋ የተገጠሙ ግጥሞች

1. ያሉላ ፈረስ የረገጣቸው፣
   እስካሁን ድረስ አለ ቁስላቸው፣
   ያሉላ ፈረስ ተስቦ ወርዶ፣
   ያነን ነጭ ገብስ አረገው ነዶ::

2. መብቱን ዮሐንስ ላሉላ ቢሰጠው፣
   እንደ ቀትር እሳት ቱርክን ገላመጠው፣
   ጣልያንም ወደቀ እያንቀጠቀጠው፣
   አጭዶና ከምሮ እንደገብስ አሰጣው::
   አባ ነጋ አሉላ ካስመራ ቢነሳ፣
   እንዳንበሳ ሆኖ እሳት እያገሳ፣
   ቢቸግረው ጣልያን አለ ፎርሳ ፎርሳ::
   ጣልያን በሃገርህ አልሰማህም ወሬ፣
   የበዝብዝ አሽከሮች እነሞት አይፈሬ፣
   ዘለው ጉብ ይላሉ እንደ ጐፈር አውሬ::
   አባ ነጋ አሉላ የደጋ ላይ ኮሶ፣
   በጥላው ያደክማል እንኳንስ ተቀምሶ::
   ጣልያን ሰሐጢ ላይ እግሩን ቢዘረጋ፣
   በብረት ምጣዱ በሰሐጢ አደጋ፣
   አንገርግቦ ቆላው አሉላ አባ ነጋ::
   ተው ተመከር ጣልያን ይሻላል ምክር፣

ሰላጢ ላይ ሆነህ መሬት ብትቆፍር፣
ኋላ ይሆንሃል ላንተው መቃብር፣
ይቺ ኢትዮጵያ የበዝብዝ አገር፣
ምንም አትቃጣ እንደ አራስ ነብር::

/እነዚህ ግጥሞች፣ «ትቤ አኩሱም መኑ አንተ?» ከተባለው የአቶ አስረስ የኔሰው መፅሐፍና «ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ሃይለ ስላሴ» ከተባለው የአቶ ተክለ ፃድቅ መኩርያ መፅሐፍ የተወሰዱ ናቸው::/

3. ሓሽከር ፈንቅል ዝበለ ገባሪ፣
ሓሽከር በዝብዝ ዝበለ ገባሪ፣
ጐይታ ሓማሴን ምድሪ ቁሪ፣
ጐይታ ዓሳውርታ ገምገም ባሕሪ፣
ወደረኛ ጣልያን በዓል ምስሪ፣
ወደረኛ ቱርኪ በዓል ምስሪ፣
ወደረኛ ድርቡሽ ሓጀ ኑሪ፣
ሓፂርን ነዊሕን ብሓደ ዘማዕሪ፣
ይውሕጠና ዝብሉኻ ከም ባሕሪ፣
የንድደና ዝብሉኻ ከም ጓህሪ፣
ከም አንበጣ አብ ጎቦ ሰፋሪ፣
መጋረጃ ሓበሻ መቑሕ ቁሪ፣
ድፍእ የብሉኻ መነደሪ፣
ኩዒትካ ትቐብሮም ትሕቲ ምድሪ፣
መሓር ኢሎምኻ ዘይመሓሪ፣

ግበር ኢሎም'ካ ዘይገባሪ፣
ኣብ ልብ'ካ ትዕሕፉ ነታ ምኽሪ፣
ብኣነትዶ ውሒጡካ ምድሪ፣
ከም ኣባ ነጋ ዝበለዶ ኣብ ኣምበራ ይቐሪ፣
ብእግዚኣብሄር ድአ ኮይኑ ብፈጣሪ:: ግጥሙ ወደ አማርኛ ሲመለስ ከሞላ ጐደል፣

«የሐማሴን ጌታ፣ የዓሳውርታ ጌታ የልቡን ሰሪ፣
የጣልያን፣ የቱርክ የድርቡሽ ተወዳዳሪ፣
የፈንቅል አሽከር የበዝብዝ አሽከር የልቡን ሰሪ፣
አጭርና ረጅም እኩል አስተካካይ፣
እንደ ባሕር የሚያሰምጥ እንደ እሳት የሚያጋይ፣
እንደ አንበጣ ጉብታ ሰፋሪ፣
የአበሻ አለኝታ ጠላትን ቀባሪ፣
ማገር ቢሉህ እልኸኛ፣
አድርግ ቢሉህ እምቢተኛ፣
ሁሉም ነገር በልብህ መዝግበህ፣
እውነት ምድራችን አንተን ዋጠችህ?
መቼ ይቀር ነበር አምበራ ላይ
አባ ነጋን የመሰለ፣
እንደዚያ ሆነ እንጂ ፈጣሪ ስላለ»
የሚል መልእክት ነው ያለው::

4. ጮማ ተበሊዑ ኢልኩም አይትህረፉ፣
ነጪ ተበሊዑ ኢልኩም አይትህረፉ፣

ሜስ ተሰትዩ ኢልኩም አይትህረፉ፣
ያባትን አልጋ መስጠት ክፉ፣
ሓዊር ዓጢቕኩም ግዳ ተራገፉ፣
ኣባ ነጋ ኣሉላ እንድሕር ደጊፉ፣
ሓለቓ ሰናዲር ፀቢብ ኣፉ፣
ምእይቲ ዓመት ትገዝኡ ውዝፉ::

ግጥሙ ወደ አማርኛ ሲመለስ፣

«ጮማ ተቆረጠ፣ ነጭ ጤፍ ተበላ፣ ጠጅ ተንቆረቆረ ብላችሁ አትሳሱ:: ከሁሉ የከፋ ነገር ያባትን አልጋ ማስረከብ ነውና፣ ይልቅስ ባጭር ታጥቃችሁ መፋለም ይኖርባችሁዋል:: የሰናዲር ጌታ የሆነው አሉላ አባ ነጋ ከእናንተ ጋር ከተሰለፈ፣ ገና ከእንግዲህ አንድ መቶ ዓመት መግዛታችሁ አይቀርም» የሚል መልእክት አለው::

5. ክንሰምዮም ዶሞ ኣባ ነጋ ጐይታና፣
ሳዕሊ ምቕማጦም ከም ደበና፣
ንድኻ ይፀንሖዎ ብትሕትና፣
ንሓያል ይፀንሖዎ ብልዕልና፣
ናይ ልቦም ዝገብሩ ከም እግዚኢና፣
ናይ ዶግዓሊ ዶሞ ክነግረሎም ዜና፣
ሕርድ ወዓልዎም ንበዓል ጣልያና፣
ናይ ኮፌት ዶሞ ክንነግረሎም ዜና፣
ድርቡሽ መፀት ክትመስል ደበና፣
ናይ ኣባ ነጋ ወረ ዶኾን ዘይሰምዐት ኮይና፣

ልብድን ድርዕን ኩላ ተኸዲና፣
ርእሳ ሰበርካያ ከም ሽክና፣
ዓዕሚ ኣጻም ሰራሕኻዮ ኺና፣
ኣብ ሓመድ አሕደርካዮ ንኣቶማን ጅግና፡፡
ግጥሙ ወደ አማርኛ ሲመለስ፣

«ውዳሴ እናቅርብ ወይ ለአባ ነጋ ጀግና፣
መኖሪያቸው ላይ ነው፣ እንደ ሩቅ ደመና፣
ደሃን ይቀርቡታል በታላቅ ትሕትና፣
ዓመፀኛን ደግሞ በልዕልና፣
የልብ አድራሽ ናቸው እንደ ጌታ፡፡

ዶግዓሊን ላንሳ ወይ ጣልያን ያረዱበት፣
ወይስ ከፊትን ደርቡሽ የወቁበት፣
ደርቡሽ እኮ መጣ እየተዝናና፣
አልሰማም መሰለኝ የአባ ነጋን ዝና፣
እራሱን ሰበርከው እንደ ሽክና፣
በጠላቶች አጥንት እየሰራህ አጥር፣
የአቶማን ጀግናን ከተትከው መቃብር»

የሚል መልእክት ነው ያለው፡፡

ራስ አሉላ አባ ነጋን የሚመለከቱ የትግርኛ ግጥሞች እነዚህ ብቻ አይደሉም፡፡ ጊዜና ሁኔታ ከፈቀደ፣ ለወደፊቱ እዕፋቸዋለሁ የሚል ተስፋ አለኝ፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የንጉስ ምኒልክ ሃገራዊ ሴራና የአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግስት ፍፃሜ

ከዚህ በኋላ የኢጣልያ መንግስት ዶግ ዓሊ ላይ የደረሰበትን ሽንፈት ለመበቀል ማውጠንጠን ጀመረ:: በዚሁም መሰረት ሮባላንቴ የተባለው የኢጣልያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መጋቢት 11 ቀን 1887 ዓ.ም ለኮንት አንቶኔሊ እንዲህ ብሎ ፃፈለት:: ይህ ሰው የኢጣልያ መንግስት ሰላይ ሲሆን፣ የንጉስ ምኒልክም የቅርብ ወዳጅና አማካሪም ነው::

«የኢጣልያ ልጆች ክቡር ደም በኢትዮጵያ ምድር ከፈሰሰ፣ ሐሳባችን ሁልጊዜ ኢትዮጵያን በቁጥጥራችን ለማስገባት መታገል ነው:: ለዚህም ብዙ የፖለቲካ ስራ መሰራት አለበት:: መጀመሪያ ንጉስ ምኒልክ ከነትጥቁ ከኛ ጋር ሆኖ አፄ ዮሐንስን ለመውጋት መዘጋጀቱን ማወቅ አለብን:: በሌላው ነገር ደግሞ እርስዎ በዚያው ስፍራ ሆነው፣ በኢትዮጵያ ውስጥ የተደረገውንና የሚደረገውን ነገር ሁሉ ለመንግስታችን ማሳወቅ አለብዎ:: እስካሁን በክቡርነትዎ በየጊዜው የተሰሩትን ነገሮች ሁሉ ገልጠው እንዲፅፉልኝ እለምንዎታለሁ::

«ከዚሁም በተጨማሪ፣ ንጉስ ምኒልክ ከኛ ጋር ተሰልፎ ንጉሰ ነገስት ዮሐንስን ለመውጋት ዝግጁ መሆኑን ይጠይቁት:: ከኛ ጋር ሆኖ አፄ ዮሐንስን ከወጋ በኋላ የሚፈልገው ጥቅም ምን

እንደሆነም ይጠይቁት። አፄ ዮሐንስን በግድ አስለቅቀን በሰሜን በኩል ለንጉስ ምኒልክ ትልቅ ስልጣን ለመስጠት ተዘጋጅተናል። በጐደለ ነገር ሁሉ እናግዘዋለን።

«አፄ ዮሐንስ ለማንገራገር ከሞከሩም በኛ በኩል ጥበቃ እንደሚደረግለት ያስታውቁት። ይህን ሁሉ አስረግጠው ምላሹን እንዲፅፉልኝ እጠብቅዎታለሁ።

ሮባላንቴ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መጋቢት 11 ቀን 1887 ዓ.ም» ይላል ቀደም ብዬ የጠቀስኩት የአቶ አስረስ የኔሰው መፅሐፍ። /ገፅ 21-22/

በተጨማሪም በዚህ ቀንና ዓ.ም ከኢጣልያ ንጉስ ኡምበርቶ አንደኛ ለንጉስ ምኒልክ አንድ ደብዳቤ ተልኮላቸዋል። የደብዳቤውም ይዘት እንደሚከተለው ነው።

«ባገርና በእግዚአብሄር ፈቃድ የነገሰው ወደ ቻዩ ወዳጄ ዳግማዊ ምኒልክ፣ የሸዋ፣ የከፋ፣ የጋላ አገር ሁሉ ንጉስ፣ ጤና ይስጥልኝ። ጳጉሜን 4 ቀን 1878 ዓ.ም የፃፉት ደብዳቤ ደርሶኛል። ልዑል ግርማዊ ያመለከተኝን ነገርም ማለት የኔ አሽከር ኮንት አንቶኔሊ እንዳሳሰብዎ ለጥቂት ጊዜ ከርሶ ጋር መቆየቱ እጅግ ደስ አለኝ። ይህ የማይናወጥ ዘላለማዊ ፍቅራችን ሁልጊዜ እያደገ፣ እየበዛና እየጋለ እንደሚሄድ ተስፋ አለኝ። እየተረዳዳንና እየተመካከርን በሰላምና በደስታ እንድንኖር ተስፋዬ የላቀ ነው።

«ካሁን ቀደም ከማርኪዞ አንቺኖራ ጋር ብዙ እምነትና ወዳጅነት እንደነበርዎ ሁሉ፣ አሁንም ከኮንት አንቶኔሊ ጋር ላቅ ያለ ፍቅር እንዳላችሁ አውቄ እጅግ ደስ ብሎኛል። በአንቶኔሊ ፍቅርም ከልዑል ግርማዊነትዎ የተላኩትን መልእክተኞችዎን

የኢጣልያ ሰዎች በታላቅ ክብርና በብዙ ወዳጅነት ተቀብለዋቸዋል። ወደ እኔ ግቢ ሲመጡም፣ ከዚያ በበለጠ በማይረሳ ወዳጅነትና ትልቅ አጀብ ልቀበላቸው ነኝ።

«ያሳዝናል። ለምን ቢሉ፣ ያጄኔራል በዚያ ስፍራ ስልጣኔንና ሰላምን ለማስፋፋት የተላከ ነበር። አሁን ግን የኔ ሐሳብ ቀጥሎ ለመሄድ ነውና ኮንት አንቶኔሊ፣ እንደ ብዙ እምነትዎና ወዳጅነትዎ የምናደርገውን ነገር ሁሉ ይነግረዎታል። የፃፍንልዎን ነገር ሁሉ እሙን ሰው ካልሆነ በቀር ለማንም ሰው እንዳይናገሩ። እምነትዎን እንዲያስረግጡ አደራዎን። ምክንያቱም ምስጢር የባከነ እንደሆነ ነገሩ ሁሉ ይጋለጣል። ----

«ስለወታደሮቻችን ጉዳት ግን ብዙም አያሳዝነንም። እነሱ ፊታቸውን ሳይቀለብሱ ለባንዴራቸው የተፈጁ ናቸው። ነገር ግን ዘንድሮ ጥር 26 ቀን 1887 ዓ.ም በምፅዋ የተፃፈብን ነገር ለኢጣልያ መንግስት አእምሮ እንደሌለው ልጅ አስመስሎ የሚያስነቅፈን በመሆኑ ብቻ አዝናለሁ። ነገር ግን ከዚህ በኋላ ያች ስፍራ የኢጣልያ ደም የፈሰሰባት ናትና የኢጣልያ ርስት እንደምትሆን እርግጠኛ ነኝ። አልሰጥም የሚል ሰው ቢገኝ ደግሞ በኢጣልያ ያለ ሰው ሁሉ እስቲያልቅ ድረስ ይዋጋላታል።

«ልዑል ሆይ፣ በዚህ አገር የሚመጣ ጦርነት ይህን ያህል ይመስላል ብዬ ልገልፅልዎ አልችልም። ነገር ግን ለጦርነት የተዘጋጁና የተባረኩ ወታደሮችዎን ይዘው ይጠብቁ። በዚያ በኩል ያሉ እንግዶች ወታደሮችዎን በጨካኝ ከዳተኛ እጅ መስዋእት እንዳይሆኑ ይጠብቁልኝ። ወዳጅነታችን በእኔና በርስዎ እየተጠበቀች እንድትሄድ ብዙ ተስፋ አለኝ። ለመንግስትዎ ረጅም

ዕድሜና ሰላም ይሁን:: ወዳጅዎ ንጉስ ኡምበርቶ አንደኛ የኢጣልያ ንጉስ መጋቢት 11 ቀን 1887 ዓ.ም» ይላል የንጉስ ኡምበርቶ ደብዳቤ፣ አቶ አስረስ የኔሰው እንደሚተርኩልን:: /ገፅ 22-23/

እዚህ ላይ መገንዘብ የሚያስፈልገው፣ በአሉላ አባ ነጋ የሚመራው የትግራይ ሰራዊት ዶግዓሊ በሚባለው ጦር ሜዳ በኢጣልያ ወራሪ ሰራዊት ላይ የተጐናፀፈው አንፀባራቂ ድል ዓለምን በሙሉ እንዳስረገመና የኢጣልያንም ህዝብ እንዳስለቀሰ ቀደም ብለን አይተናል:: ከዚህም የተነሳ የኢጣልያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የንጉስ ምኒልክ አማካሪ ለነበረው ለኮንት አንቶኔሊ ስለሳውን እንዲያጠነክር የሚያሳስብ ደብዳቤ ለመፃፍ ተገደደ::

የኢጣልያው ንጉስ ኡምበርቶም በበኩላቸው፣ ለንጉስ ምኒልክ በላኩት ተመሳሳይ ደብዳቤ፣ ኢትዮጵያ ምድር የገባው የኢጣልያ ጦር፣ «ጨካኝ» ብለው በሚጠሩት የሰሜን ኢትዮጵያ ሰራዊት፣ ጉዳት እንዳደርስበት የንጉስ ምኒልክ ጥበቃ እንዳይለየው ይጠይቃል::

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ደብዳቤ የሚጠቁመው ተጨማሪ ነጥብም አለ:: የንጉስ ምኒልክ ሰራዊት ከኢጣልያ ጦር ጐን ተሰልፎ አፄ ዮሐንስን ከወጋ፣ ሰሜን ኢትዮጵያን ከኢጣልያ መንግስት ጋር በመቀራመት ለንጉስ ምኒልክ ትልቅ ስልጣን ለመያዝ እንደሚፈቀድላቸው ይገልፃል::

ከዚህ በኋላ ንጉስ ምኒልክ ከወዳጃቸው ከኢጣልያ መንግስት በቀረበላቸው ጥያቄ መሰረት አንድ ስምምነት ላይ መድረስ ነበረባቸው:: ስለሆነም አቶ አስረስ የኔ ሰው፣ ከላይ

በተጠቀሰው መፅሓፋቸው እንደሚተርኩልን፣ በልዑል ዳግማዊ ምኒልክ፣ የሸዋ፣ የከፋ፣ የጋላ ንጉስና በኢጣልያ መንግስት መልእክተኛ በኮንት አንቶኔሊ መሃከል ውል ተደረገ:: የውሉ መንፈስም እንዲህ ይላል::

1. «በሸዋና በኢጣልያ መንግስት መሃከል አንድነት እና ወዳጅነት በሚያስደንቅ ሁኔታ በስራ ላይ ይውላል::
2. የኢጣልያ መንግስት ለዳግማዊ ምኒልክ ስልጣናቸውን ከፍ የሚያደርግ የጦር መሳርያና ሌላም ነገር በተቻለው መጠን እንዲያግዛቸው ተስማምቷል::
3. የኢጣልያ መንግስት ከንጉስ ምኒልክ ድርሻ ግዛት አልፎ እንዳይነካባቸው በግልፅ አረጋግጧል::
4. የኢጣልያ መንግስት ለንጉስ ምኒልክ አምስት ሺህ የጦር መሳርያ አሰብ ባለው ቆንሲል አድርጎ ለመላክ ተስማምቷል::
5. የሸዋ ንጉስም፣ ይህንኑ የጦር መሳርያ ተቀብሎ መንግስቱን ሊጠብቅ ካልሆነ በቀር የኢጣልያ መንግስትን የሚጐዳ ነገር እንዳይፈፅም በግልፅ አረጋግጧል:: ችግር ባጋጠመ ጊዜም ይህንኑ የጦር መሳሪያ ይዞ ለኢጣልያኖች ሊያግዝ ተዋውለዋል::

አዲስ አበባ ጥቅምት 10 ቀን 1880 ዓ.ም::» /ገፅ 23/

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ትንሽ ሓፍረት ሳይሰማቸው፣ አፄ ምኒልክ ቢያንስ ትግራይን ከኢጣልያ ቅኝ ተገዥነት አዳኑ ብለው ለመመፃደቅ የሞከሩላቸው የአፄ ምኒልክ ሐቀኛ ታሪክ ይህን ይመስላል:: ሌላ ይቅርና አፄ ምኒልክ ሰሜን ኢትዮጵያን በተለይም ትግራይ ትግርኚን እንደ ራሳቸው አገርና

ግዛት አድርገው ይመለከቱት ነበር ለማለትም አይቻልም:: እንደዚያ ባይሆን ኖሮ፣ ኤርትራን የሚያክል ጥንታዊ የኢትዮጵያ ክልል፣ ሮማ ከተማ ተፅፎ የመጣላቸውን ውል ጓዳ ውስጥ ተደብቀው በመፈረም ለወራሪዎች በገፀበረከት መልክ ባላስረከቡት ነበር:: በተጨማሪም፣ የትግራይ ትግርኚ ህዝብ ከ1875-1887 ዓ.ም ድረስ ዳርድንበሩን ለማስከበር ከተለያዩ ወራሪ ሃይሎች ጋር በመፋለም የከፈለውን መስዋእትነት ደመ ከልብ ሆኖ እንዲቀር ማድረጋቸውን እናያለን:: ይህም የሚያሳየን የተከፈለው መስዋእትነትና የፈሰሰው ደም፣ አገሬን ለመከላከል ከዜጎቼ የተከፈለ መስዋእትነት ነው፤ የሚል እምነት እንዳልነበራቸው ነው የሚያሳየን:: የኢትዮጵያ መሪ ነኝ የሚል ንጉስ ይቅርና፣ የኢጣልያ ወራሪዎች ንጉስ ኡምበርቶ እንኳ ሓፍረት ሳይሰማው፣ «ያቺ ስፍራ የኢጣልያ ክቡር ደም የፈሰሰባት ናትና የኢጣልያ ርስት እንደምትሆን እርግጠኛ ነኝ» ብሎ ነው በልበሙሉነት አቋም የወሰደ::

አፄ ምኒልክ የሰሜን ኢትዮጵያን ህዝብ እንደ ህዝባቸው እንደማይመለከቱት የሚጠቁመን ሌላ አብነትም አለ:: ነጋድራስ ገብረሀይወት ባይከዳኝ «አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ» በተባለ መፅሓፋቸው፣ «አጤ ምኒልክ በአንዲት ነገር ሊታሙ የተገባ ነው:: የትግሬን ህዝብ እንደ ህዝባቸው አልቆጠሩትም:: በትግሬ መሬት ሽፍቶ ባላገሮችን ሲያጠፋ የነበረውን ወንበዴ ሁሉ ሲገባላቸው ምረው ሲሾሙት፣ ሲሸልሙት ነበሩ:: ትግሬ በዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ ፈፅሞ ጠፍቷል:: የትም የትም ብትሄድ በዚያች አገር የለማ መንደር አታገኝም:: ሰው ከሚኖርባቸው ጎጆች ይልቅ

የድሮ ልማትዋን የሚመሰክሩ ፍርስራሾቿ ይበዛሉ፡፡ የትግሬ ጉበዝ በዛሬ ዘመን ባባቱ አገር አይገኝም፡፡ አውራ እንደሌለው ንብ አድራሻው ሳይታወቅ ወደ አራቱ የዓለም መዓዝኖች ተዘርቷል እንጂ፡፡ በሃገሩም ላይ ድህነት ሰፍታለች፡፡ የሌሎች ወገኖች መተረቢያ እስክትሆን ድረስ፡፡ ሁሉም መሬት በሰላም ሲኖር፣ ምስኪንይቱ ትግሬ ግን፣ ሽፍታና ወንበዴ አልተለያትም፡፡ ባላባቶቹም ዘወትር እርስበርሳቸው ሲዋጉ ይኖራሉ» በማለት አጤ ምኒልክ በትግራይ ህዝብ ላይ ያደርሱት የነበረውን ግፍና በደል በግልፅ ያስቀምጡታል፡፡

በንጉስ ምኒልክና በኢጣልያው መልእክተኛ መሃከል የተደረገውን ውል ከላይ አይተናል፡፡ ይህን በተመለከተም አቶ አፈወርቅ ገብረኢየሱስ «ዳግማዊ ምኒልክ» በተባለው መፅሐፋቸው ሲተርኩ፣ «ቀጥሎም አፄ ምኒልክ ከኢጣልያ መንግስት ጋር ውስጥ ለውስጥ ተዋዋሉ፡፡ ውሉም አጤ ምኒልክ አጤ ዮሐንስን ወግተው በተገባዎ መንግስት ሊቆሙ፤ ለኢጣልያ መንግስትም በመሳሪያ ስላገዘ ተምጥዋ በላይ ጥቂት ታውራጃው አገር አሥመራን ሊሰጡ፡፡ ኢጣልያ ግን፣ ከተቀበለው ሌላ ተሻግሮ መሬት ለመያዝ እንዳያምረው፣ ፍቅር እንዲ ሰፋ፣ ንግድ እንዲለማ ነበር» በማለት የእምዬ ምኒልክን ሃገራዊ ክሕደት ይገልፁታል፡፡ /ገፅ 48/

አፈወርቅ ገብረኢየሱስ እንደገና በመቀጠል፣ «የዚህን ጊዜ አጤ ዮሐንስ ሰሐጢ ላይ ከኢጣልያ ጦር ጋራ ተሰላልፈው ነበር፡፡ ድርቡሽም አጤ ዮሐንስ በጦርነት መያዛቸውን አይቶ ወደ ጐንደር ገፋ» ይላሉ፡፡ /ገፅ 48/

ግዛት አድርገው ይመለከቱት ነበር ለማለትም አይቻልም:: እንደዚያ ባይሆን ኖሮ፣ ኤርትራን የሚያከል ጥንታዊ የኢትዮጵያ ክልል፣ ሮማ ከተማ ተፅፎ የመጣላቸውን ውል ጓዳ ውስጥ ተደብቀው በመፈረም ለወራሪዎች በገፀበረከት መልክ ባላስረከቡት ነበር:: በተጨማሪም፣ የትግራይ ትግርኚ ህዝብ ከ1875-1887 ዓ.ም ድረስ ዳርድንበሩን ለማስከበር ከተለያዩ ወራሪ ሃይሎች ጋር በመፋለም የከፈለውን መስዋእትነት ደመ ከልብ ሆኖ እንዲቀር ማድረጋቸውን እናያለን:: ይህም የሚያሳየን የተከፈለው መስዋእትነትና የፈሰሰው ደም፣ አገሬን ለመከላከል ከዜጎቼ የተከፈለ መስዋእትነት ነው፤ የሚል እምነት እንዳልነበራቸው ነው የሚያሳየን:: የኢትዮጵያ መሪ ነኝ የሚል ንጉስ ይቅርና፣ የኢጣልያ ወራሪዎች ንጉስ ኡምበርቶ እንኳ ሓፍረት ሳይሰማው፣ «ያቺ ስፍራ የኢጣልያ ክቡር ደም የፈሰሰባት ናትና የኢጣልያ ርስት እንደምትሆን እርግጠኛ ነኝ» ብሎ ነው በልበሙሉነት አቋም የወሰደ::

አፄ ምኒልክ የሰሜን ኢትዮጵያን ህዝብ እንደ ህዝባቸው እንደማይመለከቱት የሚጠቁመን ሌላ አብነትም አለ:: ነጋድራስ ገብረህይወት ባይከዳኝ «አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ» በተባለ መፅሓፋቸው፣ «አጤ ምኒልክ በአንዲት ነገር ሊታሙ የተገባ ነው:: የትግሬን ህዝብ እንደ ህዝባቸው አልቆጠሩትም:: በትግሬ መሬት ሸፍቶ ባላገሮችን ሲያጠፋ የነበረውን ወንበዴ ሁሉ ሲገባላቸው ምረው ሲሾሙት፣ ሲሸልሙት ነበሩ:: ትግሬ በዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ ፈፅሞ ጠፍቷል:: የትም የትም ብትሄድ በዚያች አገር የለማ መንደር አታገኝም:: ሰው ከሚኖርባቸው ጎጆች ይልቅ

አዎ አፄ ዮሐንስ፣ አቶ አፈወርቅ ገብረእየሱስም እንደሚያረጋግጡት በሶስት ተፃራሪ ሃይሎች ተከበዋል። በሰሜን በኩል ኢጣልያ፣ በደቡብ በኩል ንጉስ ምኒልክ፣ በምዕራብ አቅጣጫ ደግሞ ድርቡሽ መሆናቸው ነው። ይህም ሆኖ ግን አፄ ዮሐንስ እስከ መጨረሻ የደም ጠብታ ድረስ የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ለማስከበርና የኢትዮጵያን ጠላቶች ለመፋለም ዝግጁ ነበሩ። የሰሐጢ ግንባር ውጥረት ወደ ከፍተኛ ደረጃ በተሸጋገረበት ወቅት፤ የአፄ ዮሐንስ መኳንንትና ወታደሮች ደግሞ፣ «ጃንሆይ! ሁላችንም ወደ ምፅዋ ሄደን ኢጣልያን ወግተን ከእናት ኢትዮጵያ ምድር ማባረር አለብን» እያሉ ይፎክሩና ይሮክሩ ነበር። አፄ ዮሐንስም ይህንን አይተው እጅግ ደስ አላቸው። እንዲህም አሉ።

«ልጆቼ ሆይ! እኔም ስለ እናት ኢትዮጵያ ሕይወቴን ለመስዋት ዝግጁ ነኝ። እናም እኔ እራሴ ከእናንተ ጋር እሄዳለሁ» አሉ። ሚያዝያ 3ቀን 1888 ዓ.ም/1880 ዓ.ም/ የክተት አዋጅ በማወጅም ወደ ምፅዋ አቀኑ። ነገር ግን እንደገና ደግሞ ከበስተጐንደር ሌላ ጥሪ ቀረበላቸውና ፊታቸውን ከአስመራ ወደ ጐንደር አዞሩ ይላሉ አቶ አስረስ የኔሰው ከላይ በጠቀስኩት መፅሐፋቸው። /ገፅ 26/

ሃጋይ ኤርሊክ የተባለ የታሪክ ባለሞያም በበኩሉ፣ የንጉስ ምኒልክን ሴራ በተመለከተ ሲፅፍ «ንጉስ ምኒልክ፣ ከአፄ ዮሐንስ ሊሰነዘርባቸው የሚችለውን ጥቃት ለመከላከል ከሚያደርጉት ዝግጅት ሌላ፣ ኢጣልያኖች ከምፅዋ ወደ አስመራ እንዲንቀሳቀሱ

በማድረግ የአፄ ዮሐንስን እንቅስቃሴ በማደናቀፍ ላይ ነበሩ» ይላል። /ገፅ 175/

እዚህ ላይ አንድ ግልፅ መሆን ያለበት የታሪክ እሻራ አለ። ኢትዮጵያ ከትግራይ ህዝብ በሚወለድ ሰው የምትመራ ከሆነ፡ ትምክሕተኞች ከኢትዮጵያ ጠላቶች ጐን ተሰልፈው የኢትዮጵያን ህዝብ ከመውጋት ወደኋላ አይሉም።

አፄ ዮሐንስ በጐንደር በኩል የጥሪ መልእክት ከደረሳቸው በኋላ ልባቸው ከሁለት ተከፈለ። የሰሜን ግንባር በመተውም ወደ ጐንደር ለመዝመት ነው እየተዘጋጁ ያሉት። በዚሁም መሰረት ለንጉስ ተክለሃይማኖት፣ አንድ መልእክት ልከውላቸው ነበር። አቶ አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ ይህን በተመለከተ የሚሉን አላቸው።

«አጤ ዮሐንስ፣ ለንጉስ ተክለሃይማኖት ውረድና ከድርቡሽ ተዋጋ ብለው ላኩ። ንጉስ ተኽለሃይማኖት ግን፣ የደርቡሽን ብርታት አይተው ዛሬ የመጣው ደርቡሽ ለኔ የሚቻል አይደለም ብለው ላኩ። አፄ ዮሐንስም እንዲህ ማለትህ ፈርተህ ነው፣ ውረድና ተዋጋ ብለው ላኩባቸው። ንጉስ ተክለሃይማኖትም ምንም ነገሩ ቢያውቁት በኔ ምንም ፍርሐት የለብኝም፣ እስትሞት እዋጋለሁ ብለው ተዋጉ። ድል ሆኑ፣ ሰውም አለቀ። እርሳቸውም ሸሽተው አመለጡ። አጤ ዮሐንስ ግን በዚህ ተናደው አንተ በፈከርኸው ወደህ ድልሆንህ፣ ሰውን አስፈጀህ ብለው ተቆጥተው ለንጉስ ተክለሃይማኖት ላኩ» በማለት ስለ ሁኔታው ያብራራሉ። /ገፅ 49/

አፄ ዮሐንስ ለንጉስ ምኒልክም ሌላ መልእክት ልከዋል። አቶ አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ ለንጉስ ምኒልክ የተላከውን ደብዳቤ

አስመልክተው ሲፅፉ፣ «አጤ ዮሐንስ ላጤ ምኒልክ እባክህ ድርቡሽ መጥቶ ቤተክርስቲያን ሲአቃጥል፣ ታቦት ሲአረክስ ዝም አትበል:: ለኔ አልልም፣ ስለሃይማኖትህ፣ ስላገርህ ብለህ ተዋጋ አሉና ላኩ:: አጤ ምኒልክ ከወሎ ገስግሰው ወደ ጐንደር በሄዱ ጊዜ፣ ድርቡሽ ጐንደርን አቃጥሎ አገሩ ገባ:: ደርቡሽና አጤ ምኒልክ ግን፣ ነገር ለነገር ተዋውቀው ነበር አስቀድመው» ይሉናል:: /ገፅ 49/ አዎ፣ ንጉስ ምኒልክ ከድርቡሽ እና ከኢጣልያ ጐን ተሰልፈው የኢትዮጵያን ህዝብ ወግተዋል:: ትምክሕተኞች እነሱ የሚጠሉት መንግስት ስልጣን ላይ ካለ ከማንም ጠላት ጋር ተሰልፈው የኢትዮጵያን ህዝብ ከመውጋት እና በኢትዮጵያ ዳር ድንበር ላይ ከመደራደር ፈፅሞ አያመነቱም ያልኩትም ያለ ምክንያት አይደለም::

የአፄ ዮሐንስ ደብዳቤ ህሊና ላለው ኢትዮጵያዊ አጥንትን የሚቀሰቅስ ነው «ለኔ አልልህም፣ ላገርህ ብለህ ተዋጋ» የሚል ሃይለቃል አለበት:: የንጉስ ምኒልክ መልስ ግን፣ «ሞኝህን ፈልግ» የሚል ነው:: ምክንያቱም ከድርቡሽ ጋር ምስጢራዊ የትግል ግንኙነት ነበራቸውና ነው:: ለንጉስ ምኒልክ ስልጣን እንጂ፣ ሃገር ምናቸውም አይደለም:: ስልጣን ላይ ለመውጣት ግን ከማንም የኢትዮጵያ ጠላት ጋር ለመተባበር የሚቀድማቸው አልነበረም:: ለንጉስ ምኒልክ ከአፄ ዮሐንስና ከትግራይ ህዝብ በቀር ሌላ ጠላት አልነበራቸውም:: የትግራይ ተወላጅ የሆነው ዮሐንስ የሚመራት አንድነቷ የተጠበቀ ኢትዮጵያን ከሚያዩ፣ ውድቀትዋንና መበታተንዋን ለማየት ይመርጣሉ:: ይህም በታሪክ የተረጋገጠ ሐቅ ነው:: በአገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚንቀሳቀሱት

የዘመናችን የትምክሕት ሐይሎችም እንዲሁ፣ ይህን አመለካከት በላቀ መልኩ ይጋሩታል። በተግባርም ኢትዮጵያን ለመበታተን ከተሰለፉ ሐይሎች ጋር ግንባር ፈጥረው እየተንቀሳቀሱበት ነው።

ከላይ እንዳየነው ንጉስ ምኒልክ ጐንደር አካባቢ በነበሩበት ወቅት፣ የሰራዊታቸውን ሰልፍ ይመለከቱ ነበር። አፈወርቅ ገብረኢየሱስ፣ ይህን በተመለከተ የሚሉት አላቸው።

«አጤ ምኒልኩ አዘዞ ላይ ሰራዊታቸውን ሁሉ አሰልፈው አዩ። ሰልፉ አምሮ፣ ሰራዊቱ፣ እንኳን ድርቡሽ ይቆምለት ላጤ ዮሐንስም ሰራዊት ቢሆን በግርማው ብቻ አለመድፍና አለነፍጥ የሚያንቀጠቅጥ ነበረ። አጤ ምኒልክ ያን ሁሉ ሰልፍ በፈረስ ሁነው ዳር እስከ ዳር እየቃኙ አዩ አዩና ከልበዎ በደረሰ ጊዜ ቀኝና ግራውን በዘንግ እያሳዩ፣ በዚህም ቢመጣ፣ በዚህም ቢመጣ ውሎህ እንዲህ ነው፣ አሉና ለሰራዊትዎ ነገሩ። የዚያን ጊዜ ነገሩን አውጥተው ባይናገሩትም፣ ትግሬ ቢመጣ እንዲህ ሁነህ ተሰልፌህ በሰናድርና በመድፍ አቅልጠው፣ በፈረስ አዳባየው፣ ማለትዎ ለሁሉ ገባው። የመከዳታቸው ነገር ታወቀ» በማለት ይገልፁታል። /ገፅ 50/

ንጉስ ምኒልክ አሁን አይደለም የከዱት ክሕደታቸው ከጉንዳጉንዲ ጦርነት ጀምሮ ነው። የንጉስ ምንሊክ ጠላቶች አፄ ዮሐንስ እና ወራሪውን የኢጣልያ ሰራዊት የሚፃረሩ ወገኖች ብቻ ናቸው። ሁሉ ጊዜ ትግሬ ከመጣ እንዲህ አድርገን እንመታዋለን፣ እንገድለዋለን፣ እናጠፋዋለን ብቻ ነው ሕልማቸው። አሁን ከፊታቸው መሽጎ ያለው፣ ጐንደርን ያቃጠለው ጠላት፣ በጐንደር ከተማ ላይ ያደረሰውን ውድመት ለመበቀል አይደለም

እያውጠነጠኑ ያሉት። ሕልማቸው አንድና አንድ ብቻ ነው። ከማንም ጠላት፣ ጋር ተባብሮ የትግራይን ሐይል መስበር እና የአፄ ዮሐንስን መንግስት ማስወገድ።

አፄ ዮሐንስም የንጉስ ምኒልክን ክሕደት መገንዘባቸው አልቀረም። በተጨማሪም የሸዋው ሰራዊት፣ በቤጌምድር ህዝብ ላይ ከፍተኛ ውድመት በማድረስ ላይ ስለነበር አፄ ዮሐንስ፣ ንጉስ ምኒልክን ወደ ሸዋ እንዲመለሱ አዘዝዋቸው።

ሃጋይ ኤርሊክም ይህነን አስመልክቶ ሲፅፍ፣ «የሸዋ ሰራዊት ቤጌምድር ላይ ሰፍሮ፣ አካባቢውን በማውደም ላይ ስለነበረ፣ በግንቦት ወር ወደ ሸዋ እንዲመለስ፣ አፄ ዮሐንስ ትእዛዝ አስተላለፉ» ይለናል። /ገፅ 170/

ንጉስ ምኒልክም እግረመንዳቸው አባይን ተሻግረው ከንጉስ ተክለሃይማኖት ጋር ተገናኙ። ለአፄ ዮሐንስ መንግስት ላለመታዘዝም ተማማሉ። ቃል ኪዳን ገቡ። አቶ አፈወርቅ ገብረእየሱስ ይህን በተመለከተ የሚሉንን ደግሞ እንስማ።

«አፄ ዮሐንስ፣ በመጣህበት መንገድ ወዳገርህ ተመለስ ብለው ላጤ ምኒልክ ላኩ። አጤ ምኒልክ ግን ይልቁን ተናደዱና በደንገል በር አድርገው ወደ ጐጃም ተሻገሩ። የጐጃም ሰውም እልልታውን እያቀለጠ ተቀበላቸው። ንጉስ ተክለሃይማኖትም በያገሩ፣ በየመንገዱ፣ ሁለንተናውን እያሰናዱ በደስታ ተቀበልዋቸው። ከዚህ ወዲያ ሁለቱም ንጉሶች በትግሬ ሰው ተባበሩበት፣ ከዱ። ውላቸውም አጤ ዮሐንስ ወደ ጐጃም የሄዱ እንደሆነ አጤ ምኒልክ በቤጌምድር ሂደው በስተጀርባ ሊታዘሉና ሊከቡ። አጤ ዮሐንስ ወደ ሸዋ የሄዱ እንደሆነ ግን፣ ንጉስ

ተክለሃይማኖት በጌምድር ወርደው በስተጀርባ ሊከቡ ነበር» በማለት ይተርካሉ። /ገፅ 51/ እዚህ ላይ ንጉስ ምኒልክና ንጉስ ተክለሃይማኖት እየተማማሉ ያሉት በወራሪው ደረቡሽ ላይ ሳይሆን፣ በአፄ ዮሐንስና በትግራይ ህዝብ ላይ ነው። ለምን?

ከዚህ የምንማረውስ ምንድነው? ንጉስ ምኒልክ የአፄ ዮሐንስና የትግራይ ህዝብ ጠላት መሆናቸውን ብቻ አይደለም ማየት ያለብን። ንጉስ ምኒልክ፣ ስለ ኢትዮጵያ ዳርድንበር፣ ስለ ኢትዮጵያ አንድነትና ህልውናም ደንታ አልነበራቸውም። የሳቸው ዓላማ፣ አንኮበር ላይ ዙፋናቸውን ዘርግተው፣ «ያቀናነው አገር» የሚሉትን አካባቢና እንደ እንስሳ የሚቆጥሩትን ህዝብ ያለተቀናቃኝ ረግጦ መግዛት ብቻ ነው። ይህ አመለካከት ግን፣ አሁንም ቢሆን ትምክሕት በተጠናወታቸው፣ የንጉስ ምኒልክ ደቀመዛሙሮች ሁሉ ጐልቶ ይታያል።

ይህም ያለፈ ታሪክ ብቻ ተደርጎ መወሰድ የለበትም። «ታሪክ እራሱን ይደግማል» እንደሚባለው፣ በአሁኑ ወቅትም፣ ከዚህ የከፋ ሃገራዊ ክሕደት እያየን ነው። ለዚህም አንድ አብነት ብቻ መጥቀስ በቂ ነው። በቅንጅት ስም የተደራጁት ዘረኞች እና በውጭ አገር የሚኖሩ ሂትለራውያን፣ በጀግናው የትግራይ ህዝብ ከፍተኛ የህይወት መስዋእትነት እና በኢትዮጵያ ህዝቦች የጋራ ተጋድሎ በተገኘው ዴሞክራሲያዊ መድረክ ተጠቅመው፣ የትግራይን ህዝብ ከገፀ ምድር ለማጥፋት ጐራዴያቸውን ስለው ባገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ ግንባር ፈጥረው ተንቀሳቅሰዋል። አሁንም አልተኙም። ለወደፊትም ይተኙለታል

ማለት ዘበት ነው። «ወዲ ድሙ ነይገድፍ ግብረ እሙ» /የድመት ልጅ የእናቱን ተግባር አይተውም/ ነውና።

አሁን ደግሞ ከላይ ወደ ጀመርነው ታሪክ እንመለስ። አፄ ዮሐንስም፣ የጐንደር ህዝብ ባቀረበላቸው ጥሪ መሰረት ከአስመራ መልስ አደረጉ። በዚህ መሃከል ግን አንድ አሳዛኝ ነገር ተከሰተ።

ማለትም የአፄ ዮሐንስ ልጅ ራስ አርአያ ድንገት አረፉ። ንጉሰ ነገስቱም በከፍተኛ ሐዘን ላይ ወደቁ። ኢትዮጵያም በየቅጣጫው በጠላቶች ተከባለች። ኢጣልያ በሰሜን፣ ደርቡሽ ደግሞ በምዕራብ በኩል ግንባር ፈጥረው ኢትዮጵያን ለመውረርና ለማፈራረስ ዝግጅታቸውን ጨርሰዋል። ንጉስ ምኒልክና ንጉስ ተክለሃይማኖትም ከነዚህ ወራሪዎች ጐን በመሰለፍ አፄ ዮሐንስን ለመውጋት ቃል ኪዳን ገብተዋል። ሃገራዊ ክሕደት የምንለውም ይህንኑ ነው። ስለሆነም አፄ ዮሐንስ በተለያዩ ችግሮች ተወጥረዋል። በወቅቱ፣ አፄ ዮሐንስን ለማፅናናት የቀረበው ግጥምም የሚከተለው ነበር።

«ጃንሆይ እምብዛ ኣይሕዘኑ ኣይንደዱ፣
ጃንሆይ እምብዛ ኣይሕዘኑ ኣይንደዱ፣
ንጉስ ውን'ዶ ይሓዝን ብኸብዱ፣
ካባይ ካብ ገረዶምድአ ምኸሪ ይተአንገዱ፣
እቶም ቱርኪ ኢዶም ከይሰዱ፣
እቶም ግብፂ ኢዶም ከይሰዱ፣
እቶም ድርቡሽ ኢዶም ከይሰዱ፣
እቶም ጥልያን ኢዶም ከይሰዱ፣
እቶም ሸዋ ኢዶም ከይሰዱ፣

መድፍዕን መትረየስንድአ የዋድዱ፣
ንጐንደር ይገስግሱ ምንፃፍ ከእንገዱ፣
ንጐጃም ይገስግሱ ቅኔ ከእንገዱ፣
ንወሎ ይገስግሱ ፈረስ ከእንገዱ፣
ንሽዋ ይገስግሱ ሰንጋ ከእንገዱ፣
ጃንሆይ አይሕዘኑ ኣይንደዱ፣
ንጉስ ውንዶ ይሓዝን ብሽብዱ፣
ህዝቢ የሰናብትዎ ይኺድ ዓድዓዱ፣
ከረስቶስከ ወዲዶ ወሊዱ።»

የዚህ ግጥም መልእክት ባጠቃላይ አፄ ዮሐንስ በልጃቸው ሞት ምክንያት ልባቸው መጐዳት እንደሌለበት ነው፤ የሚያሳስበው። እንዲሁም ኢትዮጵያ አገራችን በውጭና በውስጥ ጠላቶች ተከባ ያለችበት ወቅት በመሆኑ ይህነን አደጋ ለመመከት መዘጋጀት እንደሚያስፈልግ ይጠቁማል። ከዚህ በኋላ፣ የአፄ ዮሐንስ ጉዞ ወደ ጐንደር፣ ከዚያም ወደ ጐጃም ሆነ። ንጉስ ተክለሃይማኖትም ከንጉስ ምኒልክ ጋር ተዋውለዋልና፣ ቃላቸውን አክበረው ከአፄ ዮሐንስ ሸሽተው ወደ አንድ ተራራ ወጥተው መሸጉ። አፄ ዮሐንስም ተራራውን ለሶስት ወር ያህል ከበቡት። ጐጃም የገባው የአፄ ዮሐንስ ሰራዊትም ከትግራይ ትግርኚ፣ ከቤጌምድርና ሰሜን፣ እንዲሁም ከወሎ የዘመተ ነበር። ይህ ሰራዊት ሶስት ወር ሙሉ ጐጃም ላይ ነው የተቀመጠው። በጐጃም ህዝብ ላይ ያደረሰው ጉዳትም ከፍተኛ ነው። የጐጃም ገበሬም ሐጢአት ሳይሰራ ከባድ ዕዳ ከፍሏል።

ደብተራ ፍስሃ ጊዮርጊስ «ታሪክ ኢትዮጵያ» በተባለ መፅሐፋቸው፣ እንደሚሉት፣ ንጉስ ተክለሃይማኖት ለሶስት ወር ያህል ተከበው ከቆዩ በኋላ አንገታቸው ላይ ገመድ በማሰር ምሕረት ጠይቀው ገቡ። ሶስት ወር ሙሉ በተራራ የቆዩበት ምክንያት ግን ንጉስ ምኒልክ መሐላውን አክብሮ ይደርስልኛል የሚል ተስፋ ስለነበራቸው ነው፣ በማለት ይገልፁታል። ሁኔታውን ሲያብራሩም አፄ ዮሐንስ «አነገስንህ እንጂ ምን በደልንህ?» ብለው ጠየቁዋቸው። ንጉስ ተክለሃይማኖትም በበኩላቸው «ሰው ነው ያሳሳተኝ» ብለው መለሱ በማለት ይተርካሉ። ከዚያ በኋላም፣ አፄ ዮሐንስ እንግዲያውስ «አንተ አገርህን ጠብቅ» ብለው እሳቸው ግን ወደ መተማ ሄዱ ይሉናል። /ገፅ 118/

አፈወርቅ ገብረኢየሱስ ግን፣ ንጉስ ምኒልክን ብቻ ለማስደሰት፣ ባልታረመ አንደበታቸው፣ «ንጉስ ተክለሃይማኖትም ጅብላ ላይ ሶስት ወር ሙሉ በትግሬ ጦር ተከበው ተቀመጡ። ጐጃምን የመሰለ ደግ አገርም ሶስት ወር ሙሉ በትግሬ አንበጣ ተመደመደ» በማለት ይገልፁታል። /ገፅ 52/ በጐጃም ገበሬ ላይ በወቅቱ የደረሰው ጉዳት፣ ከላይ እንደገለፅኩት አንድና ሁለት የለውም። የአፄ ዮሐንስ ሰራዊት ወደ ጐጃም የሄደው ግን፣ የጐጃም ገበሬን ለመጉዳት እንዳልሆነ ህሊና ያለው ሰው ይገነዘበዋል። የአፈወርቅ ገብረኢየሱስ አቀራረብ ግን፣ ትምክሕተኞችንና ከዳተኞችን ለማስደሰትና የትግራይን ህዝብ ለማጥላላት ተብሎ የተቀናበረ ዘረኛ አመለካከት ነው።

አፈወርቅ ገብረኢየሱስ በዚህ አላቆሙም። በተጨማሪም፣ «የትግሬ ወታደር፣ በዚያ ጉረሮ በሚፍቅ ቋንቋው፣ ኩሪ ኩሪ

እያለ፥ እርጉዝ አስወረዳት፥ እምጫት ጡቷ ደረቀባት፣ ቄሱ ተቤተክርስቲያን፥ ገበሬው ተዱሩ፣ ነጋዴው ተመደብሩ ተሸሸጎ በትግሬ ወታደር አለቀስ፥ ተማለለ» ይላሉ። /ገፅ 54/

ትምክሕተኞች፣ የትግራይን ህዝብ ለማንኳሰስ እና ለማጥላላት የማይጠቀሙበት ቃል የላቸውም። ቋንቋውን በተመለከተ ብቻ እንኳ ብናይ፣ የትግራይን ህዝብ «ኩሬ ኩሬ የሚል፥ ቋንቋው ጉረሮ የሚፍቅ፣ ጉረሮ የሚያንቅ፣ የወፍ ቋንቋ፣ አብዚ አብዚ የሚል» ሊላም፣ ሌላም እያሉ ነው የሚያንቋሽሹት። የዚህ ዓላማም አንድና አንድ ብቻ ነው። እሱም የትግራይ ህዝብ በቋንቋው፣ በባህሉ፣ በታሪኩና በማንነቱ እንዲያፍርና እንዲሸማቀቅ፣ የበታችነት እንዲሰማውና «አምሐርሒኑ» /የአማራነት ጭንብል አጥልቆ/ ስጥለበጥ ብሎ በመገዛት፣ በሁለተኛ ደረጃ ዜጋ ተፈርጆ ለዘለአለሙ እንዲኖር ለማድረግ ነው።

አቶ አፈወርቅ ገብረኢየሱስ፣ በሐቅ ላይ ተመስርተው የፃፉ ሰው እንጂ፣ አድርባይና እበላባይ የትምክሕተኞች አፈቀላጤ አለመሆናቸውን ሊነግሩንም ይሞክራሉ። እስቲ ምን እንደሚሉ እንስማቸው።

«ይሄን አጭር ታሪክ የጣፈው፣ አንድ እበላ ባይ አይደለም። ደግሞም እንዳይጠረጠር ይሄን የጣፈው የሸዋ ሰው አይደለም። አንድ የዘጌ ልጅ እንጀራ ሳይንቅ፣ እንጀራ የማይፈልግ ሰው ነው» በማለት ስለራሳቸው እራሳቸው ይመሰክራሉ። /ገፅ 58/ ግን የአቶ አፈወርቅ ገብረኢየሱስ ታሪክ እራሳቸው እንደሚገልፁት ነው?

ዶ/ር ሃብተማርያም አሰፋ፣ «የኢትዮጵያ ታሪክ ጥያቄዎችና ባህሎች» በተባለ መፅሐፋቸው፣ ስለ አፈወርቅ ገብረኢየሱስ ማንነት በከፊል እንደሚከተለው ይሉናል::

አቶ አፈወርቅ፣ «ዳግማዊ ምኒልክ» በሚል አርእስት ለመፃፍ የተነሳሱባቸው ምክንያቶች ብዙ ሲሆኑ ዋናዎቹ ግን ሁለት ናቸው::

«አንደኛ በኢጣልያ ሃገር በነበሩበት ጊዜ በአፄ ምኒልክ ላይ ከፍተኛ አድማና ክህደት ፈፅመው ስለነበረ ይቅርታ እንዲደረግላቸው መለማመጫና መቆለማመጫ ብለው የፃፉት ነው::

«ሁለተኛ፡- ከአፄ ምኒልክ በፊት ነግሰው የነበሩትን አፄ ዮሐንስንና ሰራዊታቸውን በማዋረድና አፄ ምኒልክን እያወደሱ፣ እያመሰገኑ በመፃፍ ተወዳጅ በመሆን እንጀራ ለመብላት ነበር::
አቶ አፈወርቅ ገብረኢየሱስ ግማሽ ጐናቸውን እያመሰገኑ እያጋነኑና እየመረቁ፣ ግማሽ ጐናቸውን ደግሞ እያዋረዱ፣ እያረከሱና እየረገሙ፣ በቀኝ እጃቸው የግራ እጃቸውን እንደመቁረጥ በሚያስቆጥር አኳሁዋን፣ አንድ ሆኖ ሲኖር የነበረውን የኢትዮጵያ ህዝብ በሚለያይ ሁኔታ በስሜት ግፊትና ግንፍልነት በስጋዊ አድላዊነት ግፊት በውስጣቸው በተደበቀው የጥላቻ ቁስል ስቃይ ወደ ተሳሳተ አመለካከት ስላደረሳቸው፣ የስድብ ውርጅብኝ መፅሐፍ ሊፅፉ በቅተዋል::

«አዲስ ዘመን ጋዜጣ ታሕሳስ 19 ቀን 1984 ዓ.ም ስለ እኚሁ ሰው ባወጣው እትሙ ላይም «ነጋድራስ አፈወርቅ ገብረኢየሱስ በመፅሐፋቸው ከሃቅ የራቀ ልብ ወለድ ነው የፃፉት::

አፈወርቅ ገብረኢሱስ የሚታወቁት በምሁርነታቸው ሳይሆን በከሐዲነታቸው ነው:: በኢጣልያ አገር የኢትዮጵያ ሚኒስቴር /አምባሳደር/ ሆነው በሚያገለግሉበት ጊዜ ለኢጣልያ መንግስት ሰላይ መሆናቸው ሲታወቅ ከሹመታቸው ተሻሩ::--- ከፋሺሽት ኢጣልያ ወረራ በኋላም በአዲስ አበባ የሮማ መንግስት አፈ ቄሳር አፈወርቅ ሆነው--- ሲኖሩ፣ ባንዴራችን ከተመለሰ በኋላም በሰሩት ወንጀል ተጋልጠው ጅማ ታስረው የነበሩ--- ናቸው፣» በማለት በሰፊው ተዕፎባቸዋል:: /ገፅ 646/

በ1888 ዓ.ም ኢጣልያኖች ኢትዮጵያን በወረሩበት ወቅት፣ አቶ አፈወርቅ ገብረኢየሱስ ከወራሪዎች ጐን ተሰልፈው እስከ ዓዲግራትና ዕዳጋ ሐሙስ ድረስ እንደዘመቱም ዶ/ር ሃብተማርያም ይተርካሉ:: በመቀጠልም «አቶ አፈወርቅ በፈፀሙት ክሕደትና ተልእኮ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ ምን ዓይነት ችግርና ፈተና እንደሚጠብቃቸው ያውቃሉና አፄ ምኒልክና እቴጌ ፀሐይቱ ይቅርታ እንዲያደርጉላቸው አፄ ዮሐንስንና የሰሜኑን ህዝብ መሰዋት ነበረባቸው:: አቶ አፈወርቅ ገብረኢሱስና መሰሎቻቸው በትግራይ ትግርኚ ተወላጆች ላይ ከፍተኛ ጥላቻ የሚያሳድር የዘሩት የመርዝ ዘር በየቦታው በቅሎላቸውና በየቦታቸው አፍርቶላቸው ፍሬውን ሲለቅሙ ቆይተዋል::» /ገፅ 645/

ዶ/ር ሃብተማርያም አሰፋ፣ በተጨማሪም እንዲህ ይላሉ:: «አቶ አፈወርቅ ገብረኢየሱስ፣ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስትና የመላ ኢትዮጵያ ህዝብ ወኪል እንደራሴ ሆነው በኢጣልያ በሮማ ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር ሆነው ተሹመው ነበር:: የኢጣልያን ሰራዊት በሰልፍ ከተቀበሉት ኢትዮጵያውን አንዱ አፈወርቅ

ገብረኢየሱስ ነበሩ። ካሊጉላ የተባለው ከ37 እስከ 41 ዓ.ም የነበረው የሮማውያን ቄሳር «ምነው የሮማውያን ራሶች በሙሉ በአንድ ራስ ተጠቃልለው አንድ በሆኑ ኖሮ፣ በአንድ ጊዜ ቆርጬ በጣልኩዋቸው ነበር» አለ፤ እየተባለ እንደሚነገርለት አቶ አፈወርቅም እንደዚሁ «ምነው የትግሬዎች ራሶች ተጠቃልለው በአንድ ራስ በተቀመጡ ኖሮ፣ ያለ ርህራሄና ማወላወል በአንድ ጊዜ በሰይፍ ቆራርጬ ቀይ ባሕር ውስጥ በከተትኩዋቸው ነበር። ትግራይና ኤርትራም ባዶ በሆኑ ነበር እያሉ ያማርሩ ነበር እያሉ የሚያውቁዋቸው ሰዎች ሲናገሩ ሰምቻለሁ» በማለት ይተርኩልናል፣ ዶ/ር ሃብተማርያም አሰፋ። /ገፅ 653/

እንግዲህ ከላይ እንዳየነው አፈወርቅ ገብረኢየሱስ ቁጥር አንድ ከሐዲ ናቸው። አንድ ሰው ከሐዲ ከሆነ ሐቅ አይዋጥለትም። ጀግና ሰው፣ ጀግኖችን ያከብራል። ከሐዲና አድርባይ ግን፣ እየዋሸና እየተልከሰከሰ ነው ከሁለት ያጣ ጐመን ሆኖ የሚቀረው። ፍፃሜውም የሞት ሞት ይሆናል።

እስቲ አሁን ደግሞ የአፈወርቅ ገብረኢየሱስ የመጨረሻ ፍፃሜ ምን እንደሚመስል እንይ።

ዶ/ር ሃብተማርያም አሰፋ ከላይ በጠቀስኩት መፅሐፋቸው «ኢጣልያኖች ዋና መናገሻ ከተማችንን ከያዙ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ ይግረማችሁ፣ አቶ አፈወርቅ አፈቄሳር አፈወርቅ ተብለው ተሾሙ። --- በኛ ስርዓት አፈ ንጉስ እንደማለት ነው።»

አቶ አፈወርቅ ገብረኢየሱስ፣ እንዲህ እንደደላቸው ግን አልቀጠሉም። በመጨረሻ ላይ ከፍተኛ ውድቀትና ውርደት ሊጐናፀፉ ነው። አንዴ ከኢጣልያ ጋር፣ አንዴ ከምኒልክ ጋር፣

እንደገና ደግሞ ከሃይለስላሴ ጋር እየተልከሰከሱና እየዋሹ የሞት ሞት ሞቱ::

አቶ አፈወርቅ ገብረኢየሱስ፣ ትንሽ ሃፍረት የማስማቸው ወራዳ ሰው ናቸው:: ከላይ እንደጠቀስኩት ስለራሳቸው እራሳቸው በመመፃደቅ ሲመሰክሩ «ይሄን አጭር ታሪክ የጣፈው፣ አንድ እበላ ባይ አይደለም:: ደግሞ እንዳይ ጠረጠር ይሄን የጣፈው የሸዋ ሰው አይደለም:: አንድ የዘጌ ልጅ እንጀራ ሳይንቅ፣ እንጀራ የማይፈልግ ሰው ነው» ብለውናል::

እንደ አቶ አፈወርቅ ገብረኢየሱስ አመለካከት ከሆነ፣ የትግራይ ህዝብ ጠላት ለመሆን ከሸዋ መወለድን ይጠይቃል ማለት ነው:: እጅግ ሲበዛ ነው የተሳሳቱት:: የሸዋ ህዝብ በታሪኩ የትግራይ ህዝብ ጠላት ሆኖ አያውቅም:: የትግራይ ህዝብ ጠላት ለመሆንም ታሪካዊ መነሻ የለውም:: የትግራይ ህዝብ በኢትዮጵያ ምድር ከትምክሕተኞች በቀር ጠላት የለውም:: ከትምክሕተኞች ጋር ግንባር የፈጠረ የትግራይ ተወላጅም የትግራይ ህዝብ ጠላት ነው:: ትምክሕተኛ ለመሆን ደግሞ ሰሜን ሸዋ መወለድን አይጠቅም:: ወይም ደግሞ አማራ መሆንን ብቻ የሚጠይቅ አይደለም:: ትምክሕተኝነት አመለካከት ነው:: የትምክሕተኞችን አመለካከት የተሸከመ የማንም ብሄር ብሄረሰብ ተወላጅ ትምክሕተኛ ነው::

ወደ አቶ አፈወርቅ ገብረኢየሱስ የመጨረሻ የሕይወት ፍፃሜ ልመለስ:: ዶ/ር ሃብተማርያም አሰፋ፣ የአቶ አፈወርቅ ገብረኢየሱስን ፍፃሜ እንደሚከተለው ያስቀምጡታል::

«አቶ አፈወርቅ ገብረኢየሱስ እናት ሃገራቸውን በመክዳታቸውና የኢትዮጵያንም ምስጢር ለጠላት አሳልፈው በመስጠታቸው፣ በከፍተኛ ሃገርን የመክዳት ወንጀል ተከሰው በፈፀሙት ከባድ የወንጀል ድርጊት መሰረት የሞት ፍርድ ተወሰነባቸው:: ነገር ግን የሞት ፍርዱ ወደ ዕድሜ ይፍታሕ ተሻሽሎላቸው፣ በጅማ እስር ቤት ውስጥ ሳሉ በዚያ ሞተው ቀሩ» ብሎ ማለት ነው የሚተርኩልን:: /ገፅ 656/

ስለዚህ እስካሁን እንደተከታተልነው፣ አፄ ዮሐንስ፣ ንጉስ ምኒልክ በሸረቡት ሴራና ሃገራዊ ክሕደት ምክንያት በከፍተኛ ውጥረት ላይ ነው የነበሩት:: በተጨማሪም ንጉስ ምኒልክ በደጃዝማች ስዩም አባ ጒበዝ የሚመራ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ትግራይ ውስጥ እንዲቀጣጠል አድርገዋል:: ንጉስ ምኒልክ ከደርቡሽ ጋርም አፄ ዮሐንስን በጋራ ለመመከት ምስጢራዊ ግንኙነት ፈጥረዋል:: ኢጣልያም ከንጉስ ምኒልክ በሚላክለት የዕለት ተለት መረጃ እየተረዳ አስመራን ለመቆጣጠር በዝግጅት ላይ ነው ያለው:: ይህንና ይህን በመሳሰሉ ውጥረቶች ተከበው እያሉ ነው እንግዲህ አፄ ዮሐንስ ወደ መተማ የዘመቱት:: የመተማ ጦርነት ባኢትዮጵያውያን ድል አድራጊነት እንደተጀመረ ነው የሚታወቀው:: ነገር ግን አፄ ዮሐንስ ወደ ጦር ሜዳ ገብተው ሲፋለሙ በጥይት መወጋታቸው ተሰማ:: የኢትዮጵያ ሰራዊትም በንጉሱ መቁሰል ምክንያት ተደናግጦ ለጠላት ተጋለጠ:: ድሉም የደርቡሾች ሆነ:: አፄ ዮሃንስም ለዘላለም የማይደበዝዝ አኩሪ ታሪክ በደማቸው ፅፈው ከዚህ ዓለም ተሰናበቱ::

አፄ ዮሐንስ፣ በሰላም ለመግዛት የታደሉ ንጉሰ ነገስት አልነበሩም። የኢትዮጵያ ዳርድንበር በዘመናቸው አልተደፈረም። አገርን አሳልፎ ለመስጠት የተዘጋጀ ህሊናም አልነበራቸውም። ባገር ጉዳይ ላይ ድርድር አያውቁም። ለዚህም ይመስለኛል አንዳንድ ሰዎች የፓለቲካ ችሎታ አልነበራቸውም የሚሉዋቸው። በመሆኑም እንደ አፄ ምኒልክ አልተመቻቸውም።

አቶ አፈወርቅ ገብረኢየሱስ፣ ስለመተማው ዘመቻና ስለውጤቱም የሚሉት አላቸው።

«ነገሩ እያደረ ከበደ። የሸዋ ፀሐይ ገና ተመስኮትዋ ብቅ ብላ ስታበራና ስታፀድል፣ የትግሬን ሰፈር የቀን ጨለማ ወርዶ አጠለቀው። ይኼ ሁሉ ሲሆን፣ አጤ ዮሐንስ መቸነፋቸውን በልብ ተረድተውት ሳለ፣ ባፋቸው ምንም አልተረቱ ነበረ። በዚህ መካከል ወግድ ምኒልክ መቸም አምልጦ አየመልጠነና፣ አሁንስ ቤተክርስቲያናችነን ያቃጠለውን፣ ታቦታችነን ያረከሰውን ደርቡሽን ሂደን እንውጋ፣ ደማችንን እንመልስ ብለው ወደ መተማ ወረዱ። አጤ ዮሐንስ፣ ማዋጋታቸውን ትተው፣ ሳይቸግራቸው፣ ያን ያህል እንዳንደኛ እሸለምና እሾም ባይ ወታደር ተመሃል ገብተው ደረታቸውን ላረር ባልሰጡም ነበረ» በማለት ነው አቶ አፈወርቅ የሚተርኩልን። /ገፅ 53-55/

አዎ አቶ አፈወርቅ፣ እዚህ ላይ እንኳ ልክ ናቸው። የትግራይ ሰፈር የቀን ጨለማ ነግሶበታል። አጤ ዮሐንስ መቸነፋቸውን ተርድተውት ነበር፣ የሚሉት ግን ፈሪው ንጉስ ምኒልክን አሞካሽተው የውሸት እንጀራ በልተው ለማደር ስለፈለጉ

ነው እንጂ፣ አጤ ዮሐንስ፣ ንጉስ ምኒልክን ይቅርና የንጉስ ምኒልክ ጌቶችንም አይፈሩም።

ሌላ አስገራሚ ነገርም ተናግረዋል፣ አቶ አፈወርቅ ገብረኢየሱስ። ላገሩና ለዳርድንበሩ መስዋእት መሆን ያለበት እበላና እሸለም ባይ ወታደር ብቻ ነው እንጂ፣ አፄ ዮሐንስን የመሰለ ንጉሰ ነገስት ጦር ሜዳ ገብቶ ደረቱን ለጠላት መስጠት አልነበረበትም ይሉናል።

መቸስ ከሐዲዎች እና ትምክሕተኞች መስዋእት መሆንን አይፈልጉም። ሆነውም አያውቁም። ሌሎች በከፈሉት መስዋእትነት፣ በተገኘ መድረክ ላይ ተኮፍሰው፣ ስላገር ነፃነት፣ ስለ ወገንና ስለዳርድንበር ሲመፃደቁ ግን ሚወዳደራቸው አይገኝም። ስለዚህ አቶ አፈወርቅ ገብረኢየሱስ እያሉን ያሉት፣ አፄ ዮሐንስ የፖለቲካ ብስለት ስለሌላቸው ከወራሪዎች ጋር ተስማምተው ለመኖር አልቻሉም። በዚህም ምክንያት አንድም ቀን ሳይደላቸው ባጭሩ ተቀጠፉ ነው ነገሩ። የአቶ አፈወርቅ ገብረኢየሱስ አመለካከት፣ በሐሰት ላይ የተመሰረተ ያድርባዮች እና መሰሎ አዳሪዎች አነጋገር ስለሆነ ግራ የሚያጋባ ነው። ለሃገራቸው እና ለወገናቸው ክብር ሲሉ ውድ ህይወታቸውን የሚገብሩት፣ ከህይወታቸው ይልቅ፣ የናት ሃገርንና የወገንን ፍቅር የሚያስቀድሙ ሁሉ ጀግኖች ናቸው እንጂ፣ እሾምና እበላ ባይ ከሐዲዎች ሊሆኑ አይችሉም። ትምክሕተኞች ግን፣ ሌሎች በከፈሉት መስዋእትነት እየተመፃደቁ ነው፣ የውሸት ክበሮ እየደለቁ የሚኖሩት።

አፈወርቅ ገብረኢየሱስ ሌላ ታሪክም ይነግሩናል:: ታሪኩ ግን በትግራይ ህዝብ እንደበትም እስካሁን ድረስ የሚነገር ነው:: አፈወርቅ ገብረኢየሱስ ስለ አፄ ዮሐንስ አሟሟት ጉዳይ እንዲህ ይላሉ:: «የአፄ ዮሐንስ ሞት ግን፣ ባጤ ምኒልክ ብርታት እንጂ በዚያ በደካማ ደርቡሽ ብርታት እንዳልሆነ ሁላችን እናውቃለን» በማለት አፄ ዮሐንስ በንጉስ ምኒልክ ሰላዮች እንጂ፣ በደርቡሽ ወታደሮች እንዳልተገደሉ ይመሰክራሉ:: /ገፅ 56/

አፈወርቅ ገብረኢየሱስ ከመተማ ጦርነት በፊት ትግራይ ውስጥ ስለነበረው ሁኔታም ይተነትናሉ:: «አጤ ምኒልክ ያደሩበት አገር ለምልሞ ያድር ነበር እንጂ፣ ደሃ ምንም አይጐዳም ነበረ:: ትግሬ ባለፈበት ግን እንዳንበጣ ልሶት ነበረ የሚያድር:: የትግሬ ሰፈር እለ ምኒልክ ጉኑ አይቀናም ነበረ:: በመጀመርያ የትግሬ ሰው ቆዳ ሽዌ እያለ ሲሳደብ ይኖር ነበረ፣ ኋላ ግን፣ እለ ምኒልክ የተጣጋው ጉኑ እንዳይጠረቃ ባየው ጊዜ ለምለሙ ሽዌ መጣ ይል ጀመረ» እያሉ ባልታረመ አንደበታቸው የትግራይን ህዝብ ያብጠለጥሉታል:: /ገፅ 26-31/

መቸስ መዋሸት ካልቀረ ደህና አድርጎ መዋሸት ነው:: አቶ አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስም ጥሩ አድርጎ መዋሸትን ያውቃሉ:: አጤ ምኒልክ ተአምረኛ ሰው ነበሩ ይላሉ አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ:: አጤ ምኒልክ የረገጡት መሬት ሁሉ ለምልሞ ያድራል ይሉናል:: የትግራይ ህዝብ የረገጠው ምድር ግን ሁሉጊዜ በድርቅ ይጠቃል ይላሉ::

አቶ አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ በትግራይ ህዝብ ላይ የሚያወርዱት የስድብና የማብጠልጠል ውርጅብኝ አያልቅም::

የትግራይን ህዝብ ማዋረድ፣ የትግራይን ህዝብ ማንቋሸሽ በአንኮበር ቤተመንግስት ውስጥ ክብርና ስልጣን ያሰጣል። አፈወርቅ ገብረኢየሱስም ይህን ያውቃሉ። አፄ ምኒልክ በኢትዮጵያ ምድር እንደ ትግራይ ህዝብ የሚጠሉትና የሚፈሩት ህዝብ አልነበራቸውም። አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ በትግራይ ህዝብ ላይ የነበራቸው ጥላቻም፣ ከአፄ ምኒልክ የተለየ ነበር ለማለት አይቻልም።

አቶ አፈወርቅ ገብረኢየሱስ ሌላም የሚሉት ነገር አላቸው። «ተዚህ ቀጥሎ፣ የትግሬ ሰው የቤጌምድርን ሲሳይ ምጥጥ አርጎ አራገፈና እንኳን በጥርሱ የሚነክሰው ስጋ፣ ባፉ የሚጎርሰው እንጀራ፣ በምላሱ የሚልሰው ሙቅ እንኳ አጥቶ ሌትና ቀን ተኩምቱ /ምስኩዕንቱ/ ጋራ ሲጫወት ሲያድር የሸዋ ድልብ፣ የሸዋ ሽሀር፣ የሸዋ ሲሳይ በደረሰለት ጊዜ የትግሬ ሰፈር በዘፈን ደምቆ ያድር ነበረ። ቀጥሎም የሸዋ ሲሳይ እንዲህ የወር መንገድ ገሸግሶ መጥቶ ሲያጠግበነ፣ ከዚያ ከሰፍራውስ ብንሄድ እንዴት ያልፍልነ? እያለ የትግሬ ሰው ሌት በጨለማ፣ ቀን በደመና እየከዳ ሸዋ መግባት ጀመረ። ድሮ የአጤ ዮሐንስ ሰፈር ሳል እንደያዘው ድመት እየመነመነ ሲሄድ፣ ያባ ዳኛው ከተማ እየሰፋ፣ ስፍራ እየጠበበው፣ ተግርማ ግርማ እየጨመረ ያድር ጀመረ። አፄ ዮሐንስም በዚህ ተደናገጡና ሰው እየከዳቸው እንዳይሄድ በየበሩ ያስጠብቁ ጀመረ። ነገር ግን ምን ሊሆን? ማን አግቶ ሊያስቀረው? ችጋር ያባረረው ትግሬና ባሩድ የሸተተው አውሬ አንድ ናቸው። እንደ ቡኸር በሂትም እየዘለለ ሸዋ ለመግባት አልቦዝን አለ» እያሉ ይዘላብዳሉ። /ገፅ 31/

አፈወረቅ ገብረኢየሱስ እያሉን ያሉት፣ የትግራይ ህዝብ እምዬ ምኒልክ ከሸዋ የላኩለትን ሲሳይ በልቶ ስለጠገበ መንደሩ ሁሉ በዘፈን ደምቆ ያድር ነበር። ምክንያቱም የሚላስ የሚቀመስ ነገር በማግኘቱ፣ ቀንም ሆነ ማታ ስራስር እየቆፈረ ይበላ ነበርና ነው፣ እያሉ ነው፡ የትግራይን ህዝብ ኢየሰደቡት ያሉት። «ችጋር ያባረረው ትግሬና ባሩድ የሸተተው አውሬ አንድ ናቸው። እንደ ቡኸር በሄትም እየዘለለ ሸዋ ለመግባት አልቦዝን አለ» ይሉናል አፈወርቅ ገብረኢየሱስ። መቸስ አቶ አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ ከሐዲና ስስታም ከመሆናቸውም ሌላ፡ ልባቸውም በጭፍን የዘር ጥላቻ ስለተመረዘ ነው እንጂ፣ የትግራይን ህዝብ ለረሃብ፣ ለስደትና ለመከራ የዳረጉት እነ አፄ ምኒልክና ስርዓታቸው ናቸው። ስለዘፈኑ ጉዳይ ግን አንድ ነገር ልጨምር።

ትምክሕተኞች «እግዚአብሄር ዘፈን ሲያምረው ትግሬን ያጠግባል» ይላሉ። እንግዲህ በነሱ አባባል፣ እግዚአብሄር ደስታን ሲፈልግ የትግራይን ህዝብ ያጠግባል ማለት ነው። ሐዘንና ዋይታ ሲያምረው ደግሞ ትምክሕተኞችን ያጠግባል ነው፡ እያሉን ያሉት። ይህ አባባል ትክክል ነው። እግዚአብሔር ፍቅርን፣ ደስታን፣ ሰላምን፣ አብሮ ተባብሮ መኖርን ይፈልጋል። የትግራይ ህዝብም በልቶ፣ ጠጥቶ፣ ከጠገበ በኋላ፣ ፈጣሪውን ያመሰግናል፣ ይዘምራል፣ ይስቃል፣ ይጫወታል፣ ይዘፍናል እንጂ፣ ህዝቦችን አያሰቃይም፣ አያስለቅስም፣ አያሳዝንም። አያጋጭም ወይም ደግሞ ጦር አውርድ ብሎ ምድርን አይገርፍም።

ትምክሕተኞች ግን፣ ከማንም በላይ እኛ ነን ብለው ስለሚያምኑ፣ «እምቢ ላለሰው ጥይት አጉርሰው» በሚል

መፈክራቸው እየተመሩ ህዝቦችን እያስለቀሱ፣ እያስቃዩ፣ እያናከሱ፣ እየዘረፉ፣ እየበዘበዙና እየረገጡ ይኖራሉ:: የኢትዮጵያ ህዝብም እነዚህን ትምክሕተኞች የሚያውቃቸው ፈሪዎች ናቸውና፣ ችግር ሲከሰት ሲፈረጥጡ፣ ሰላም ሲነግስ ደግሞ ከተሰደዱበት አገር ተመልሰው ሲያበጣብጡ ነው:: የሕይወት መስዋእትነትን በሚጠይቅ ፈተና ወቅት ግን፣ የትምክሕት ሐይሎች አይገኙም::

አቶ አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስም፣ እንዲሁ ለውሸት ታድለው ነው እንጂ፣ ትምክሕተኞች፣ እንደመኻገር የሰው ደም እየጠጡ ከመኖር በቀር፣ የተራቡ ህዝቦችን የመመገብና የመርዳት ባሕሪም ሆነ ታሪክ የላቸውም:: እስቲ አሁን ደግሞ የመተማውን ፍፃሜ እንይ:: ሃጋይ ኤርሊክ እንደሚተርክልን፣ አፄ ዮሐንስ ለውጭ ወራሪዎች እንጂ፣ ላገር ውስጥ ተቀናቃኞቻቸው ብዙም ትኩረት አይሰጡም ነበር:: እስቲ ምን እንደሚለን ከዚህ በታች ያለውን እንይለት::

«እንደሚታወቀው፣ አፄ ዮሐንስ ባገር ውስጥ ያሉ ተቃዋሚዎቻቸውን በመውጋት ፈንታ በባዕዳን ወራሪዎች ላይ ጦርነት መክፈትን መረጡ» ይለናል:: /ገፅ 158/ ስለሆነም፣ አፄ ዮሐንስ ወደ ሸዋ መጥተው ከጸተኛውን ንጉስ ምኒልክ በመውጋት ፈንታ ከውጭ ወራሪዎች ጋር መዋጋቱን ስለመረጡ፣ በኢትዮጵያ አቆጣጠር መጋቢት 2 ቀን 1881 ዓ.ም ከደርቡኞች ጋር ሲፋለሙ መተማ ጦር ሜዳ ላይ በጀግንነት ወደቁ:: ኢትዮጵያዊ ሃገራዊነት ማለትም ይህ ነው:: የትግራይ ህዝብ ኢትዮጵያዊነትም፣ ሁል ጊዜ በጀግንነትና በመስዋእትነት የታጀበ ነው::

ሃጋይ ኤርሊክ ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ የሚተርከልን ተጨማሪ ነጥብም አለ:: የሸዋው ንጉስ ምኒልክ፣ መጋቢት 26 ቀን 1889 ዓ.ም ወደ ንጉስ ኡምበርቶ አንድ ደብዳቤ ልከው ነበር:: የደብዳቤው ይዘትም፣ ምዕዋ ላይ ያሉት የኢጣልያ ሰራዊት አባላት ወደ አስመራ የሚያመራውን አካባቢ እንዲጠብቁ ይጠይቃል:: በተጨማሪም፣ የትግራይ ተቃዋሚዎች፣ ስለ ትግራይ ጉዳይ የሚያቀርቡት አቤቱታ ሁሉ፣ በኢጣልያ በኩል ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይገባ ነው የሚያሳስበው:: ከዚህም ሌላ ወደ ንጉሱ የሚላከው መሳርያም በኢጣልያ ሰራዊት በኩል እንዲተላለፍላቸው የሚጠይቅ ነው የነበረው:: /ገፅ 189-190/ የአፄ ምኒልክ ሃገራዊ ክሕደትም ይህን ይመስላል::

ስለ አፄ ዮሐንስ ጀግንነትና መስዋእትነት የተገጠሙ ግጥሞች:-

1. ከላይ የወረደ ከፅዮን መቅደስ፣
ባበቱ ሚካኤል በናቱ ስላስ፣
አጨደው ከመረው ያን ያህዛብ ገብስ፣
ወቃው ደበደበው ሰጠው ለነፋስ፣
ዓሊሙ ነፍጠኛ አፄ ዮሐንስ::

2. ተከተለኝ ብዬ ዞሬ ዞሬ ሳይ፣
ወይ ጥጋብ ወይ ኩራት ጐንደር ቀረህ ወይ፣
ወገራ፣ አሳነፊ ደንቢያ እንጀራ ጣይ፣
ተበላህ ጐንደሬ አትነሳም ወይ::

3. አፄ ዮሐንስ ሞኝ ናቸው፣
እኛም ሁላንችን ናቅናቸው፣

ንጉስ ቢሉዋቸው በመሃሉ
ወሰን ጠባቂ ልሁን አሉ::

4. አፄ ዮሐንስ ይዋሻሉ፣
መጠጥ አልጠጣም እያሉ፣
ሲጠጡ አይተናል በርግጥ
ራስ የሚያዞር መጠጥ::

5. በጐንደር መተኰስ፣
በደንቢያ መታረድ አዝኖ ዮሐንስ፣
ደሙን አፈሰሰ እንደ ክርስቶስ::
እንዳያምረው ብሎ ድሃ ወዳጁን፣
መተማ አፈሰሰው ዮሐንስ ጠጁን::
የጐንደር ሃይማኖት ቆማ ስታለቅስ፣
አንገቱን ሰጠላት ዳግማይ ዮሐንስ::

/እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ግጥሞች፣ ከሞላ ጐደል የቀረቡ ሲሆኑ፣ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ሃይለ ስላሴ ከተባለው የአቶ ተክለፃድቅ መኩሪያ መፅሐፍ የተወሰዱ ናቸው::

በትግርኛ ቋንቋ ከቀረቡት ግጥሞች ውስጥ ደግሞ የሚከተሉት ይገኙባቸዋል::

1. ከመይ ኢኹም አሉላ ሓጐሳ፣
ኣበይድኣ ሓዲግኩሞ ንወሬሳው ካሳ፣
ሀበይ'ኳ እትማላእ ረይሳ፣
ስረ ትግራይ መተማ ሃሪሳ::

የዚህ ግጥም ትርጉም ወደ አማርኛ ሲመለስ፣

«እንዴት ናችሁ አሉላ ሐጐሳ፣

ወዲያት ተዋችሁት ወሬሳውን ካሳ፣
ዝንጀሮ እንኳን ታመጣለች ሬሳ፣
የትግራይ ሰሪ መተማ ተረሳ» የሚል ነው።

2. ዮሃንስ ክልዓል ሓዊ ፊቱ፣
ኣባ ነጋ እንትዕጠቅ ጥይቱ፣
ቁፅሬታ ዘይብሉ ሰራዊቱ፣
ብዘይካ ፊት ደጀን ዘይኣቱ፣
ኣብቲ ምስሪ ግብሪ ክተእቱ፣
ኣብ ሽዋውን ግብሪ ክተእቱ፣
ከም ሰሎሞን ብዙሕ ዝብልሐቱ፣
ብኣፍኪ ተደፍኢ ዓለም ከንቱ፣
ብሩኽ ንጉስ አብ መተማ ሞይቱ፣
ንሃይማኖት ዝሃበላ አንገቱ።

የዚህ ግጥም ትርጉም ወደ አማርኛ ሲመለስ የሚከተለውን ይመስላል።

«ዮሐንስ ሲነሳ እሳት ነው ፊቱ፣
አባ ነጋ ሲታጠቅ ጥይቱ፣
ስፍር ቁጥር የለዉም ሰራዊቱ፣
ደጀን ሳይሆን ከፊት የሚገባ፣
ከምስር አገር ግብር ሊታስገባ፣
ከሸዋም እንዲሁ ግብር ሊታስገባ፣
«እንደ ሰሎሞን ባለ ብዙ ብልሓት፣
ግና ምን ይሆናል ዓለም ከንቱ ናት፣
መተማ ነው ሞቱ ዮሐንስ ሰማእት፣

አንገቱን የሰጠ ለሃይማኖት።

ስለ አፄ ዮሐንስ በትግርኛ ቋንቋ የቀረቡ ግጥሞች እነዚህ ብቻ አይደሉም። ለወደፊቱ ግን ተጠቃልለው የሚፃፉበት ዕድል በፈጣሪ እርዳታ ይኖር ይሆናል። ለጊዜው ግን የአፄ ዮሐንስና የትግራይ ህዝብ የአስራ ሰባት ዓመት ፀረ ባዕዳን ተጋድሎ ከሞላ ጎደል ይህን ይመስላል።

# ምዕራፍ አምስት

# «ትግሬ ከጠገበና አንድ ከሆነ አይገዛም»

ከጸተኛውና አድርባዩ አፈወርቅ ገብረኢየሱስ «ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሰ ነገስት ዘኢትዮጵያ» በተባለ መፅሐፋቸው ስለ ንጉስ ምኒልክ ማንነትና ስለ ትግራይ ህዝብ መጥፎነት ሲተርኩ፣ «ድፍን ኢትዮጵያ በትግሬ ጥፍር ገብታ፣ መቸም ተጨንቃለች፣ ታለቅሳለች፣ መከራዋን ታያለች። ብልሃቱ አይታወቅም። ገና ከዚህ ሁሉ በፊት የሸዋው ምኒልክ በኢትዮጵያ ሰባት ዓመት ይነግሳል ማለቱ፣ «ት» ተሳስታ አለስፍራዋ ገብታ ነው እንጂ፣ ነግሩ ሰባ ዓመት ለማለት ይሆናል። በዚህ ንግር የተነሳ ምኒልክ መቼ በነገሰልነና፣ ይሄ አንበጣ ትግሬ በጠፋልን እያለ የማይመኝ ሰው በኢትዮጵያ አልነበረም» ይላሉ። /ገፅ 47/

የአቶ አፈወርቅ ገብረኢየሱስ መፅሐፍ ሮማ ከተማ ላይ የተፃፈው በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በ1901 ዓ.ም ነው። ስለ ሆነም ከአቶ አፈወርቅ መፅሐፍ ብዙ የምንገነዘበው ነገር አለ። ይኸውም፣ አፄ ምኒልክ በኢትዮጵያ አቆጣጠር 1882 ዓ.ም ከነገሱበት ዘመን ጀምሮ፣ አንኮበራውያን ትምክሕተኞች፣ በትግራይ ህዝብ ላይ ብቻ ያነጣጠረ ዘረኛ አመለካከትና እንቅስቃሴ ነበራቸው። ለዚህ አባባልም በአፄ ምኒልክ መልካም

ፈቃድ በመሳ ኢትዮጵያ እንዲሰራጭ የተደረገው የአቶ አፈወርቅ ገብረኢየሱስ መፅሐፍ ትልቅ አብነት ነው።

ቀደም ብለን እንዳየነው፣ አፄ ምኒልክ፣ የሰሜን ኢትዮጵያን ህዝብ ባጠቃላይ፣ በተለይ ደግሞ የትግራይ ትግርኚን ህዝብ እንደ ራሳቸው ህዝብ አያዩትም ነበር። ይህም ብቻ አይደለም። የሰሜን ኢትዮጵያን ህዝብ በጣም ነበር የሚጠሉት። ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ «አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ» በተባለው መፅሐፋቸው፣ «በሸዋዎች ሐሳብ ከድሮው ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ፣ ጐንደሬ ወይም ትግሬ ማለትና ክፉ ሰው ማለት ትርጉሙ አንድ ነው» ይሉናል። ነገር ግን አፄ ምኒልክ እና ትምክሕተኞች ብቻ አይደሉም የትግራይን ህዝብ አምርረው የሚጠሉት። የኢጣልያ ወራሪዎችም ከላይ እንዳየነው ይህነን ህዝብ «ጨካኝ፣ ክፉ፣» እያሉ ነው የሚጠሩት። ስለሆነም አፄ ምኒልክ በወራሪዎች ሁለንተናዊ ድጋፍ ስልጣን ለመጨበጥ፣ የትግራይ ትግርኚን ህዝብ ከሁለት መክፈል ነበረባቸው። በመሆኑም ከአፄ ዮሐንስ ሞት በኋላ በአንድ ወር ውስጥ ማለትም በኢትዮጵያ አቆጣጠር ሚያዝያ 25 ቀን 1881 ዓ.ም ገና የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ሳይሆኑ ከኢጣልያው መልእክተኛ ከኮንት አንቶኔሊ ጋር የውጫሌን ውል ተዋዋሉ። ይህ ባለ 20 አንቀፅ ውል፣ ሮማ ከተማ ተፅፎ ነው በቀጥታ የመጣው። አፄ ምኒልክም በትእዛዝ መልክ ነው የፈረሙበት። ይሁን እንጂ፣ ይህ ውል ለአፄ ምኒልክ አዲስ አልነበረም። ከዓመታት በፊት አፄ ዮሐንስ በሕይወት እያሉ ከአባ ማስያስና ከኮንት አንቶኔሊ ጋር አፄ ዮሐንስ እንዳይነቁባቸው በምስጢር ሲመክሩበት የከረመ ውል ነው።

አቶ ተክለፃድቅ መኩሪያ «ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ» በተባለው መፅሐፋቸው ውስጥ አስመልክተው ካስቀመጡት የተወሰኑትን ብቻ አቀርባለሁ።

አንቀፅ ሶስት፡- «በነዚህ በሁለቱ ነገስታት ወሰን ጠብና ክርክር እንዳይነሳ በዕውቅ የተመረጡ፣ ከሁለቱ ወገኖች ሁለት ሁለት ሽማግሌዎች ልከው በማይጠፋ ምልክት የግዛቱን ድንበር ይወስናሉ።

«ከድንበሩ ወዲህ የሚጨመሩት አገሮች እነዚህ ናቸው። የደጋው አፋፍ በኢትዮጵያና በኢጣልያ መሃከል ወሰን ይሆናል። ከራፋይሌ ጀምሮ ሐላይ፣ ሰገነይቲ፣ አስመራ፣ ሶስቱ የኢጣልያ መንግስት መንደር ይሆናሉ።

«ዳግመኛም፣ በበጎስ በኩል ዓዲ ነፋስ፣ ዓዲ ሞገስ በኢጣልያ መንደር ውስጥ ይሆናሉ። ከዓዲ ሞገስ መንደር ጀምሮ ከምስራቅ ወደ ምዕራብ ባቀና ይከፈላል።

«አንቀፅ አራት፣ የደብረ ቢዘን ገዳም ከነጉልቱ ከነርስቱ የኢትዮጵያ መንግስት እንደሆነ ይቀራል። የጦር አምባ መሆን ግን፣ አይቻለውም።

«አንቀፅ ስድስት፡- የጦር መሳሪያ ንግድ በምጥዋና በኢትዮጵያ መካከል የሚመላለሰው፣ ለንጉሰ ነገስት ብቻ ይፈቀድልዎታል። ሲያስመጡም፣ ባለማሕተም ደብዳቤዎን ለኢጣልያ ሹማምንት እየላኩ ያስመጣሉ። ነፍጡንም የያዘውን ሰፈር ከምጥዋ ጀምሮ እስከ ኢትዮጵያ ድንበር ድረስ የኢጣልያ መንግስት ወታደሮች ዘበኛ ሆነው ይሸኛሉ።

«አንቀፅ አስራ ሶስት፦ ከኢትዮጵያ መንግስት ሸፍተው ወደ አንደኛው መንግስት የመጡ ሰዎች፣ በሁለቱም መንግስታት ቅጣት እንደሚገጥማቸው አስቀድመው በየግዛታቸው ያስታውቋቸው። ይህን ሰምተው የሚከዱ ቢገኙ ታስረው ወደ መንግስታቸው ተመልሰው ሊቀጡ ናቸው» ይላል፣ በንጉስ ሚኒልክና በኢጣልያ መንግስት መካከል የተፈረመው የውጫሌ ውል በከፊል። /ገፅ 94-95/

እስቲ እዚህ ላይ ቆም ብለን አፄ ዮሐንስና አሉላ አባነጋ ከኢጣልያ መሪዎችና ጄኔራሎች ጋር ሲለዋወጡዋቸው የነበሩትን ደብዳቤዎች በአንክሮ እንያቸው። እስካሁን እንደተከታተልነው የእነ አፄ ዮሐንስ፣ የእነ አሉላ አባ ነጋና የእምዬ ምኒልክ ሃገራዊ ፍቅርና ኢትዮጵያዊነት እንዴት ይመዘናል?

የቱርክ መንግስት በ16ኛው ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ ላይ ወረራ ከከፈተበት ጊዜ ጀምሮ የምፅዋና የቀይ ባሕር ዳርቻዎች፣ ሁልጊዜ ለጠላትና ለወራሪ የተጋለጡ ነበሩ። ይሁን እንጂ ማእከላዊ መንግስት በነበረበት ዘመን ይቅርና በዘመነ መሳፍንት እንኳ አገርን ያህል ሸንሽኖ ለባዕዳን ያስረከበ መሪ በረጅሙ የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ ከአፄ ምኒልክ በቀር አልታየም።

ዶ/ር አድሃና ሃይለ፣ በሃጋይ ኤርሊክ መፅሐፍ ላይ ሞያዊ አስተያየቱን ሲያስቀምጥ፣ በአሁኒቱ ኤርትራና በትግራይ መካከል ስለነበረው ታሪካዊ ትስስርም የሚለው አለው።

«መረብ ምላሽና ትግራይ፣ እራሳቸውን የቻሉ የኢትዮጵያ ክልሎች እንደነበሩ ይታወቃል። ከዘመነ አፄ ስሱንዮስ 1607-1632

ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1889 ዓ.ም ድረስ ደግሞ፣ መረብ ምላሽና ትግራይ አንድ አካል ሆነው ተጠቃልለው ቆይተዋል፣» ይለናል።

ይህ እንዳለ ሆኖ ግን፣ የትግራይ ትግርኚ ህዝብ፣ በተፈጥሮ አንድ ከመሆኑም በላይ፣ በትንሹ ከአክሱም ዘመነ መንግስት ጀምሮ በወቅቱ በስልጣኔያቸውና በኪነጥበባዊ ሞያቸው በዓለማችን ጐልተው ይታዩ ከነበሩት ህዝቦች ጋር የሚወዳደር ህዝብ ነበር። ስለሆነም ይህን የመሰለ የዘመናት አኩሪ ታሪክና ህዝባዊ አንድነት ያለውን ህዝብ ረግጦ መግዛት እንዳማይቻል ለአፄ ምኒሊክ እንደ ፀሐይ ብርሃን ግልፅ ነበር። በመሆኑም ስልጣን ጨብጦ አንከበር ላይ ዘውድ ለመድፋት ከተፈለገ፣ ይህን ኩሩና ለጠላት የማይበገር ባለታሪክ ህዝብ፣ ከኢጣልያ ወራሪ ሃይሎች ጋር ግንባር በመፍጠር፣ ሁለት ቦታ ላይ እንዲከፈል ከማድረግ ውጭ ሌላ አማራጭ አልነበረም።

ሃጋይ ኤርሊክም ይህን አስመልክቶ የሚለው አለው። «የሸዋው ንጉስ፣ የውጫሌው ውል ለመፈራረም የተገደዱበት ዋናው ምክንያት ራስ መንገሻ ዮሐንስ፣ ከአባታቸው የተቀበሉትን ያልጋወራሽነት ስልጣን ሽባ በማድረግ የራሳቸውን ስልጣን ለማረጋገጥ ሲሉ ነው» ይለናል። /ገፅ 185/ ስለዚህ አፄ ምኒልክ፣ አፄ ዮሐንስን አስወግደው ስልጣን ለመጨበጥ ብቻ ሲሉ፣ አገራቸውን ቆርሰው ለባዕዳን ያስረከቡ ብቸኛ የኢትዮጵያ ንጉስ ነገስት ናቸው።

አቶ አስረስ የኔሰውም «ትቤ አክሱም መኑ አንተ?» በተባለ መፅሐፋቸው የሚሉን አላቸው። «አፄ ምኒልክ ልባቸው በኢጣልያኖች ሲራ ስለተቸነፈ፣ ንጉሰ ነገስት ዮሐንስ በህይወት

እያሉ አገር ለወራሪዎች አስረክበው እስከመፈረም ደረሱ። ከዚሁም ሌላ ንጉሰ ነገስት ዮሐንስን ከኢጣልያ ጉን ተሰልፈው ለመውጋት 5ሺህ የጦር መሳሪያ ከኢጣልያ መንግስት ተቀበሉ። በተጨማሪም ለጊዜያዊ የንግድ ጥቅም ሲሉ የአሰብን በር አሳልፈው ለኢጣልያኖች ሰጡ» በማለት ይተርካሉ። /ገፅ 24/

እዚህ ላይ ለሐቀኛ የታሪክ ባለሞያዎች የማቀርበው ጥያቄ አለኝ። አቶ አስረስ የኔሰው፣ «አፄ ምኒልክ ለጊዝያዊ የንግድ ጥቅም ሲሉ የአሰብን በር አሳልፈው ለጣልያኖች ሰጡ» እያሉን ነው። እስካሁን ድረስ በትምክሕተኞችና ኢሃገራውያን የታሪክ ሰዎች ሲነገረን የቆየው ግን፣ ምስኪኑ ሱልጣን ኢብራሂም አሰብን እንደሸጠ ነው። ከሁለቱ የትኛው ነው ትክክል? ሁሉም ቢመራመርበት አይከፋም።

በኔ በኩል ግን የአቶ አስረስ የኔሰው አባባል ነው ትክክል ብዬ አምናለሁ። የዓፋሮችና የአፄ ምኒልክን ታሪክ ስናነፃፅር፣ አፄ ምኒለክ ናቸው ለስልጣንና ለጥቅም ሲሉ አገርን የሚሸጡ እንጂ ዓፋሮች አይደሉም። ኤርትራ አንድ ትንሽ የማይባል ክፍለ ሃገር ነው። አንድ ሺሕ ኪሎ ሜትር የባሕርዳርቻም አለው። ይሁን እንጂ ይህን ትልቅና ጥንታዊ የኢትዮጵያ ክልል ለጠመንጃና ለስልጣን ሲሉ፣ ለኢጣልያ ወራሪዎች የሸጡት አፄ ምኒልክ ሆነው እያለ፣ ስለዚህ ጉዳይ ግን፣ በግልፅና ባደባባይ ሳይሸማቀቁ ሐቁን የሚናገሩ የታሪክ ሰዎች ስምተን አናውቅም። ለምን? የትምክህተኞችና ኢሃገራውያን የክሕደት ታሪክ በውዳሴ ከንቱ ለመቀባባት ስለተፈለገ ነው። ምስኪኑ ሱልጣን ኢብራሂም ግን «የአብዩን ለእምዩ» እንደሚባለው፣ «ሱልጣን ኢብራሂም ዓሰብን

የሸጠ» እየተባለ ሲወነጀል እንሰማለን። ሐቁ በግልፅ መነገር አለበት። ሐቁ በማያሻማ መንገድ ለአዲሱ ትውልድ መቅረብ አለበት። ከእንግዲህ ወዲህ የትምክሕተኞች የውሸት ድርሳናት ቦታ ሊኖራቸው አይገባም።

ባለፉት ምዕራፎች የገለፅኩት ቢሆንም፣ ደብተራ ፍስሃ ጊዮርጊስም በበኩላቸው ስለ ዓፋሮች ሃገራዊ ጀግንነት የሚሉት አላቸው።

«ባሻይ ሙዝንጀር ከአለቃ ብሩ ጋር ሆነው፣ ብዙ የባሕር ማዶ ዕቃዎችና ጦር መሳሪያ ይዘው ተነሱ። ከእነሱ ጋርም ወደ 300 የሚጠጉ ታጣቂ ዓረቦች ነበሩ። አውሳ አካባቢ ከደረሱ በኋላ ግን፣ ዓፋሮች አዩዋቸውና ወደ አውሳ ሄደው መሐመድ ሐንፋሪ ለሚባል ንጉሳቸው ያዩትን ሁሉ ነገሩት። ንጉሱም እንዲህ አላቸው። «እኔ ለእንግዶቹ የሚሆኑ ሰንጋዎችና ምግቦች ይዤ እሄዳለሁ። እናንተም የአካባቢውን ሰው በሙሉ ሰብስባችሁ በእንደዚህ ያለ ቦታ ጠብቁኝ አላቸው። እነሱም ንጉሳቸው እንዳዘዛቸው አደረጉ። ንጉስ መሐመድ ሐንፋሪም ሰንጋዎችንና የሚበላውን ነገር ሁሉ ይዞ ወደ ባሻይ ሙዝንጀር ሄደ። እንግዶቹም በክብር ተቀበሉት። እሱም እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ ሲያጫውታቸው አመሸ። ከዛ በኋላ ግን መንገደኞች ናችሁ ዕረፉ፣ እኔም ወደ ሰፈሬ እሄዳለሁ። ጉዳያችን ግን ነገ ረጋ ብለን እንወያይበታለን ብሎ ሄደ።

«በንጉሱ ታዘው የነበሩ ዓፋሮችም ተዘጋጅተው ቆዩት። ቀጥሎም መሐመድ ሐንፋሪ ወገኖቹን አስከትሎ በባሻይ ሙዝንጀርና ተከታዮቹ ላይ ከፍተኛ አደጋ አደረሰባቸው።

ሙዝንጀርና ተከታዮቹም በተሰነዘረባቸው አደጋ እዚያው ተገደሉ። 400 ከሚሆኑ ሰዎች፣ ወደ ምፅዋ የተመለሱት ሰላሳ ብቻ ነበሩ። ዓፋሮች፣ እየሸሹ የነበሩትን ወራሪዎች እየተከታተሉ በጐራዴ ፈጁዋቸው።

«ወራሪዎቹ በውሃ ጥም እንዲሞቱ ደግሞ፣ የውሃ ጉድጓዱን ይደፍኑት ነበር። ለወራሪዎቹ ምግብ ላለመስጠትም ቤቶቻቸውን እየተው ሸሹ» እያሉ ይተርኩልናል። /ገፅ 110-112/

ስለዚህ የዓፋሮች ሃገራዊ ፍቅርና ጀግንነት ይህን ስለሚመስል፣ የአፄ ምኒልክን ሃገራዊ ክሕደት ለመሸፋፈን ቢያስችለን ተብሎ እስከ ዛሬ ድረስ ሲነገረን የነበረው የተረት ተረት ታሪክ መቀየር አለበት።

እስካሁን ድረስ እንደተከታተልነው፣ አፄ ምኒልክ ኤርትራን የሚያህል ጥንታዊ የኢትዮጵያ ምድር በገፀበረከት መልክ ለኢጣልያ ወራሪዎች በማስረከብ፣ ሲቋምጡላት የነበረችውን የክሕደት በትረ ስልጣን ለመጨበጥ ቻሉ። ኢጣልያም ከትግራይ ትግርኚ ጀግኖች ጋር ለዓመታት ታግላ ማግኘት ያልቻለችውን ግዛት በአምፄ ምኒልክ ሃገራዊ ክሕደት ምክንያት ስለተፈቀደላት እጅግ ተደሰተች። ኤርትራ የምትባል የትግራይ ትግርኚ ክፋይ አገርም ተፈጠረች። ጀግናው የኤርትራ ህዝብም በአፄ ምኒልክ ክሕደት ምክንያት በቅኝ ገዥዎች ቀንበር ስር ወድቆ መማቀቅ ጀመረ። የትግራይ ህዝብ ዕድልም ከዚህ የከፋ እንጂ ያነሰ አልነበረም። እጅግ በሚጠሉትና፣ ጥፋቱን እንጂ ልማቱን ለማየት በማይፈልጉ የሸዋ ትምክሕተኞች ቁጥጥር

ስር ነበር የወደቀው:: የትግራይ ህዝብ፣ በሁለት ጠላቶች መሃከል ተቀረቀረ:: መፈናፈኛም አጣ::

ሃጋይ ኤርሊክ የተባለ እስራኤላዊ የታሪክ ባለ ሞያም፣ ይህን አስመልክቶ የሚያስቀምጠው ሐቅ አለው::

«የትግራይ ሰዎች በጦርነት የደቀቁ ነበሩና፣ ፖለቲካዊ ስልጣናቸውን ተቀምተው በኢጣልያ ወራሪ ሃይሎችና በንጉስ ምኒልክ መሃከል ተቀርቅረው ነበር» በማለት በትግራይ ህዝብ ላይ ተጭኖ የነበረውን አስከፊ የኑሮ ሁኔታ ይገልፀዋል:: /ገፅ 4/

አፄ ምኒልክ የኢጣልያ ወራሪዎችን ብቻ አይደለም አስከትለው የመጡት:: መላ ኢትዮጵያን ያወደመው የረሃብ ቸነፈርም እሳቸውን ተከትሎ ነው የመጣው::

አፈወርቅ ገብረኢየሱስ ይህን አስመልክተው ከሚተርኩት ትንሽ ልበል::

«አፄ ምኒልክ እንደ ነገሱ ኢትዮጵያ ከዳር እስከ ዳር እልል አለች፣ ደስ አላት:: ነገሰልን፣ መጣልን፣ እሰይ እሰይ የተመኘነው ደረሰልን አለች::

«ኢትዮጵያ የዚህን ደስታ ሳትጨርስ፣ ገና ድፍን ኢትዮጵያ፣ ታፏ እልልታዋን አንጠልጥላ፣ በደስታ ሰክራ ሳለ፣ የከብት እልቂት መጣና ድፍን አገሩ ባዶ እጁን ቀረ:: ኢትዮጵያ ደስታዋን ሳትጨርስ ባንድ ወገን ሐዘን፣ ባንድ ወገን ደስታ ሆነና ማር በኮሶ እየለወሱ መዋጥ ሆነባት:: እናት ለልጅዋ፣ ልጅም ለእናቱ ማልቀስ መላቀስ ቀረ:: የዚያን ጊዜ መቃብር የሚቆፈርላቸው እንብዛ ለታደሉት ነበረ:: ለቀረው ሁሉ ግን መቃብሩ ያሞራና የጅብ ሆድ ሆነ:: ካንዳንድ ስፍራስ፣ ሰውን

ሰው በላው:: ተንሳሮ አገር አንዲት ባልቴት ሰባት ልጆች በልታ ታይዛ መጣች» ይላሉ:: /ገፅ 63/

ፀሐፊ ትእዛዝ ገብረስላሴም በበኩላቸው፣ የአፄ ምኒልክ ንግስናን ተከትሎ በኢትዮጵያ ስለተከሰተው የረሃብ ቸነፈር የሚጨምሩት አላቸው::

«ዘመኑ ጥኑ ረሃብ ሆነ:: የፈረስ ስጋ፣ የአህያ ስጋ ተበላ:: ሰውን ሰው በላው:: ወሎም አንዲት ሴት ልጇን በላች:: አንሳሮም ከሚባለው አገር አንዲት ሴት ሰባት ሕፃናት በላች:: አራዊትም ሰለጠኑ:: አንበሳው፣ ነምሩ፣ ጅቡ፣ ሰውን በቁሙ ይበላዋል ሆነ:: ረሃብ ሆነ ስላልነ ግን በየአገሩ የሆነውን ፃፍነው እንጂ፣ ቤተ መንግስቱ ከጥንቱ አልጐደለም» በማለት በወቅቱ የነበረውን የረሃብ ቸነፈርና እልቂት ይገልፁታል:: /ገፅ 177/

ፀሐፊ ትእዛዝ ገብረ ስላሴ በዚሁ «ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ንጉሰ ነገስት ዘኢትዮጵያ» በተባለ መፅሐፋቸው አንድ ትልቅ ነገር ተናግረዋል:: «ረሃብ ሆነ ስላልነ ግን፣ በየሃገሩ የሆነውን ፃፍነው እንጂ፣ ቤተ መንግስቱ ግን ከጥንቱ አልጐደለም» ብለውናል:: አዎ፣ ከአፄ ቴዎድሮስና ከአፄ ዮሐንስ፣ የሃገራዊ ክብርና የህዝባዊ ልዕልና መስዋእትነት በኋላ፣ በሃገራዊ ክሕደት መሰላል ተንጠላጥለው ስልጣን ላይ የወጡት ትምክሕተኞች፣ በኢትዮጵያ ህዝቦች ላይ በተላያዩ ጊዜያቶች ይደርስ የነበረ የረሃብና የጦርነት ወላፈን አልናካቸውም:: ሁልጊዜ እንደ ደላቸው፣ ሁልጊዜ እንዳማረባቸው ነው የሚኖሩት:: ወራሪ ከመጣም አገር በመሸጥና በመለወጥ ተስማምተው ይኖራሉ:: የጠላትን ፍላጎት አሟልተውም ቢሆን፣ ለመኖር የማያስችላቸው

ሁኔታ መኖሩን ሲያረጋግጡ ደግሞ አገር ጥለው ይሻሸሉ:: ባጠቃላይ፣ ትምክሕተኞች ጅራፍ ሲያዩ ለመሽምጠጥ፣ ሰላም ሲነግስ ደግሞ ለማበጣበጥ ወደ ኋላ አይሉም::

አፄ ምኒልክ ኤርትራን ለኢጣልያ ካስረከቡ በኋላ ከኢጣልያ መንግስት ልዩ ድጋፍ ስለሚደረግላቸው የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ከመሆን የሚያግዳቸው ሃይል አልነበረም:: ስለሆነም በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ጥቅምት 25 ቀን 1882 ዓ.ም ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ንጉሰ ነገስት ዘኢትዮጵያ ተብለው በእንጠጦ ማርያም ቤተክርስቲያን ነገሱ:: የኢጣልያ መንግስትም እንዲሁ በአውሮጳ ዘመን አቆጣጠር ጥር 1 ቀን 1900 ዓ.ም ነበር፣ ከአፄ ምኒልክ በገፀ በረከት መልክ የተበረከተችለትን ሃገር ኤርትራ ብሎ የሰየማት::

አፄ ምኒልክ እንጠጦ ላይ ከመንገሳቸው በፊት ግን ደጃዝማች መኰንን /ኋላ ራስ/ ወደ ሮማ ተልከው ነበር:: የተላኩበት ምክንያት ደግሞ፣ በንጉስ ምኒልክና በኮንት አንቶኔሊ መሃከል የተደረጉትን ውሎች በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ እንደ ነበር ይታወቃል::

አቶ አስረስ የኔሰውም «ትቤ አኩሱም መኑ አንቲ?» በተባለ መፅሐፋቸው የነበረውን ሁኔታ በሚከተለው መልክ ያቀርቡታል::

«ደጃዝማች መኰንን፣ አፄ ምኒልክ በየወቅቱ ከኢጣልያ መንግስት ጋር የተዋዋሉትን ውል ለመግለፅ ከኢጣልያው መልእክተኛ ከኮንት አንቶኔሊ ጋር ነሐሴ 28 ቀን 1889 ዓ.ም

ወደ ሮማ ገቡ። በዚሁ ጊዜ ንጉስ ፊት ቆመው ካደረጉት ንግግር ውስጥ እንዲህ የሚል ይገኝበታል።

«ልዑል የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት፣ በልዑል ግርማዊ ፊት ቆሜ የሚቀጥል ፍቅራቸውን ለማቅረብ አዘውኛልና የርሳቸውን ሰላምታ አቀርብልዎታለሁ። የኔ ንጉስ የኢትዮጵያ ሁሉ አባት ነው እና፣ ስለዚህ ከመንግስትዎ የበለጠ ነገር ለመጠየቅ፣ የወዳጅነትና የንግድ ስራ የተዋዋልነውንም ፅኑ ለማድረግ መጣሁ። በኢትዮጵያና ባጠገቡ ያሉ ህዝብ፣ የኢጣልያ ግዛት ሰላምና ፍቅር እስኪ ሆን ድረስ ልዑል ግርማዎ ለመግስቴ ትልቅ ጥግታ እንዲሆነው በመንግስቴ ስም ሆኜ እለምነዎታለሁ።

«ስለምን የኔ ንጉስ የሚፈልገው፣ ለጥቅማችን የሚሆን ንግድ ማስፋፋትና ማመላለስ ነው እንጂ፣ ሌላ ነገር የለውም። በሆነው ነገር ሁሉ የኢጣልያ ጠላቶች የኛም ጠላቶች እንደሆኑ፣ ለልዑል ግርማዎ አረጋግጥለዎታለሁ» ይላሉ፣ የእምዬ ምኒልክ መልእክተኛ። /ገፅ 29/

በተለያዩ ምዕራፎች እንደተከታተልነው፣ የኢጣልያ መንግስት ቁጥር አንድ ጠላት፣ የትግራይ ህዝብ ብቻ ነው የነበረው። የኢጣልያ መንግስትም፣ «ጨካኝ፣ ክፉ» እያለ ነው ደሙን ለመበቀል ሌትና ቀን የሚዝትበት። ደጃዝማች /ራስ/ መኮንንም ይህንን ነው ለንጉስ ኡምበርቶ ያረጋገጡለት። «የኢጣልያ ጠላቶች የኛም ጠላቶች እንደሆኑ ለልዑል ግርማዎ አረጋግጣለሁ» ነው የሚሉን። ስለዚህ ትምክሕተኞች፣ የትግራይ ህዝብ ደመኞች ናቸው ስንል ታሪክን መሰረት አድርገን እንጂ፣ ከባዶ ነገር ተነስተን አይደለም። ትምክሕተኞች፣ ወረደ

መቃብራቸው እስኪ ፈፀም ድረስ፣ ለትግራይ ህዝብ ምንጊዜም አይተኙለትም። አምናም፣ ታች አምናም ከወራሪ ሃይሎች ጋር ግንባር ፈጥረው ወግተውታል፣ አድምተውታል። እንደዚሁም ለረሃብ፣ ለስደት፣ ለቸነፈር፣ ለድንቁርና እና ለኋላቀርነት ዳርገውት ቆይተዋል። ዛሬም፣ «ራዛ ናይ ኣቡኡ ሓዛ» እንደሚባለው በመሆኑ፣ ትምክሕተኞች የአፄ ምኒልክ፣ ሻዕቢያ ደግሞ የንጉስ ኡምበርቶ ጉዳይ አስፈፃሚዎችና አልጋወራሾች ሆነው የትግራይን ህዝብ ለማጥፋት ግንባር ፈጥረው እየተንቀሳቀሱ ነው።

ስለሆነም ደጃዝማች መኰንን /ራስ መኰንን/ ለንጉስ ኡምበርቶ በማያሻማ ሁኔታ እንዳረጋገጡት፣ ትምክሕተኞች፣ ዛሬም፣ ነገም፣ ለወደፊትም አቅምና አጋጣሚ ካገኙ ለትግራይ ህዝብ ይተኙለታል ማለት ዘበት ነው።

በመሆኑም፣ የትግራይ ህዝብ ከሁሉም የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰብና ከዲሞክራሲያዊያን ሃይሎች ጋር ሆኖ፣ የትምክሕተኞችን የጥፋት ተልእኮ ሽባ ለማድረግ ምንጊዜም ቢሆን በንቃት እና በትኩረት መከታተል አለበት።

ፀሐፊ ትእዛዝ ገብረ ስላሴ የአፄ ምኒልክን ንግስና አስመልክተው ሲፅፉ፣

«በአፄ ቴዎድሮስ 15 ዓመት፣ በአፄ ተክለጊዮርጊስ 3 ዓመት፣ በአፄ ዮሐንስ 18 ዓመት የቆየችው መንግስት፣ ከዳዊት፣ ከሰሎምን፣ ከምኒልክ መንግስት ገባች» ይሉናል። /ገፅ 165/ ፀሐፊ ትእዛዝ ፅሑፋቸውን በመቀጠል ሲተርኩ፣

«አፄ ምኒልክ ጋላ በወረረው አገር ሁሉ፣ በጅማ፣ በጉማ፣ በሊሙ፣ በጌራ፣ በከፋ፣ እስከ ነጭ ዓባይ ድረስ ሹም ሽር አድርገው አሽከሮችዎን ተከሉበት። አረመኔውም ያመልክበት በነበረው ስፍራ ሁሉ ቤተክርስቲያን ተሰራበት» እያሉ ያብራራሉ። /ገፅ 167/

በፀሓፊ ትእዛዝ ገብረ ስላሴ አባባል፣ ተገቢ ቦታዋን ስታ ብአፄ ቴዎድሮስ፣ በአፄ ተክለጊዮርጊስና በአፄ ዮሐንስ ቤት የቆየችው መንግስት፣ ከዳዊትና ከሰሎሞን እንዲሁም ከምኒልክ ቤት እንደ ገባች ነው እየተነገረን ያለው።

ለመሆኑ ይህ ሸዋ በቀል የሰሎሞናዊው ስርወ መንግስት አፈ ታሪክ አመጣጥ እንዴት ነው?

አኩሱማዊትዋ ንግስተ ሳባ፣ የንጉስ ሰሎሞንን ጥበብ ለማየት ወደ ኢየሩሳሌም በሄደችበት ወቅት፣ በታሪክ አጋጣሚ ቀዳማዊ ምኒልክን ከንጉስ ሰሎሞን ወለደች ተብሎ ይነገራል። ቀዳማዊ ምኒልክም ከንጉስ ሰሎሞንና ከንግስተ ሳባ የተወለደ የአኩሱም ንጉስ ነበር የሚል እምነት አለ።

በሌላ በኩል ደግሞ ዮዲት ጉዲት፣ አኩሱምን በወረረችበት ጊዜ፣ የአኩሱም ንጉስ ነገስት የነበረው አንበሳ ውድም ነው። የጉዲትን ወረራ መመከት ሲያቅተውም ወደሰሜን ሸዋ ተሰደደ። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ግን፣ ወደ አኩሱም ተመልሶ በዙፋኑ ላይ ተቀመጠ።

ከዚህም የተነሳ የሰሜን ሸዋ ነገስታት፣ «አንበሳ ውድም በስደት መልክ ወደ ሸዋ መጥቶ በነበረበት ጊዜ የወለደን ልጆቹ ነን» ይላሉ። «የንጉስ ሰሎሞን፣ የንግስተ ሳባ፣ የቀዳማዊ ምኒልክ

ዘሮች በመሆናችን ትክክለኛ አልጋ ወራሾች እኛ ብቻ ነን፣ እንደ እነ አፄ ቴዎድሮስ፣ አፄ ተክለጊዮርጊስና አፄ ዮሐንስ ያሉት ነገስታት ግና ከእግዚአብሄር ፈቃድ ውጭ በሕገ ወጥ መንገድ የነገሱ ናቸው» ብለው ነው የሚተርኩት፡፡

ለዚህም ነው፣ «ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ስዩመ እግዚአብሄር ንጉሰ ነገስት ዘኢትዮጵያ» እያሉ «ስልጣኑ ከፈጣሪ የተሰጠን ሰማያዊ ፀጋ እንጂ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚሰጠንና የሚነፍገን አይደለም» ሲሉን የነበረ፡፡

መዲናው ላስታ ላይ የነበረው፣ የአገዎች መንግስትም፣ ከዚህ ሰሎሞናዊ ስርወ መንግስት አፈታሪክ ጋር በተያያዘ መንገድ ነው፣ በአባ ተክለሃይማኖት ብልጠት የተሞላበት ተልእኮና፣ ልዩ ሃይማኖታዊ ሸሩን ምክንያት ወደቀ ተብሎ የሚነገረው፡፡

የአባ ተክለሃይማኖት ውለታም ከንቱ ሆኖ አልቀረም፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያው የደብረ ሊባኖስ ገዳም እጨጌ ተብለው ከመሾማቸውም በላይ፣ የሲሶ ለቀዳሽ መሬትም አግኝተዋል፡፡ ሲሶ ለነጋሽ፣ ሲሶ ላራሽ፣ ሲሶ ለቀዳሽ የሚባል የመሬት ስርዓት የተጀመረውም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እንደሆነ ይነገራል፡፡

ከዚህ በኋላም፣ የደብረሊባኖስ ገዳም ከሲያሚው በቀር፣ መታሰብያነቱ የባድቁ አባ ሊባኖስ ገዳም መሆኑ ቀርቶ፣ የእጨጌው አባ ተክለሃይማኖት ገዳም እንደሆነ ተደርጎ ነው የሚነገረው፡፡ አባ ተክለሃይማኖት ባለ ትዳር እንደነበሩም ይተረካል፡፡

አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌም፣ «መፅሓፈ ሰዋስው ወግስ፣ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ» በተባለ መፅሐፋቸው፣ «ተክለሃይማኖት አቦ ብልሐት፣ እጩጌነት ከሚስት» የሚሉት ይህን ለማስመልከት ነው:: /ገፅ 457/

«ሊቀ ጳጳስ ዘአኩሱም» የሚለው የአኩሱማውያን መዓርገ ሲመትም እጩጌነት ከተከሰተ በኋላ ነው፣ ቀስበቀስ እንዲቀር የተደረገው፣ ብለው የሚተርኩም አሉ::

አፄ ምኒልክም እንዲሁ፣ «አኩሱም ፅዮን ማርያም ርእሰ አድባራት ወገደማት ዘኢትዮጵያ» የሚለውን የአኩሱም ፅዮን ቤተክርስቲያን ስያሜን ለመሻማትና ታሪካዊ መሰረትዋን ለማናጋትና ለመደምሰስ፣ እንደ አኩሱም ስርዓት፣ በንቡረ እድ የምትተዳደር የማርያም ቤተ ክርስቲያን፣ አዲስ ዓለም በሚባል ቦታ አሳንፀው፣ «ርእሰ አድባራት ወገዳማት» ብለው ሰይመዋታል::

ቢሆንም፣ የአኩሱም ፅዮን ስያሜ፣ በታሪካዊ ዐጋ የተገኘ እንጂ፣ በነገስታት መልካም ፈቃድ የተሰጠ የመዓርግ ስም ስላልሆነ የሚፈጥረው ለውጥ አይኖርም::

ከዚህ በኋላ አፄ ምኒልክ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በጥቅምት 23 ቀን 1882 ዓ.ም ነግሰው፣ ታሕሳስ 9 ቀን 1882 ዓ.ም ላይ ስፍር ቁጥር የሌለው ሰራዊት አስከትለው ወደ ትግራይ ዘመቱ::

የትግራይ ህዝብ ግን፣ 17 ዓመት ሙሉ በጦርነት ሲጠበስ በመቆየቱ፣ በሞትና በሕይወት መሃከል የተንጠለጠለ ህዝብ ነው የነበረው::

ዐሐፊ ትእዛዝ ገብረስላሴም ይህን አስመልክተው ሲፅፉ፣ «ከዚህ በኋላ አፄ ምኒልክ ታሕሳስ 9ቀን 1882 ዓ.ም ወደ ትግሬ ዘመቻ ተነሱ። ራስ ዳርጌ ከተማ ለመጠበቅ ቀሩ። ደጃዝማች ተሰማም ከግቤ ወዲያ ያለውን አገር ለመጠበቅ ቀርተዋል። ሌላው ሰራዊት ግን ጠቅሎ ዘመተ» በማለት ይገልፁታል። /ገፅ 168/

ስለዚህ ከነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት ግለሰቦች በስተቀር፣ ከአፄ ምኒልክ ጐን የተሰለፈ የአገሪቱ ጦር በሙሉ ትግራይን ሳንደና ለሁሌ ለማጥፋትና ለማንበርከክ ዘምተዋል።

ደብተራ ፍስሃ ጊዮርጊስ፣ «ታሪክ ኢትዮጵያ» በተባለ መፅሐፋቸው በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ እንዲህ በማለት ይገልፁታል።

«ራስ መኰንን በኢትዮጵያ አቆጣጠር በሕዳር መጨረሻ 1882 ዓ.ም ላይ ነው፣ ከኢጣልያ ወደ ኢትዮጵያ የተመለሱት። እኛም መረብን ተሻግረን ዓድዋ ከተማ ደረስን። ዓድዋ ድሮ እንደምናውቃት አይደለችም። ስናያት ከመጠን በላይ ደነገጥን። እጅግ ተለዋውጣ ነው የቆየችን። የድሮ ልምላሜዋና ሃብትዋ ጠፍቶ፣ የሓዘን ልብስ ለብሳ ነው የቆየችን። ከነዋሪ ህዝብዋ ውስጥ፣ አንድ አምስተኛውም አልነበረም። እዚያው ያገኘነው ነዋሪም ቢሆን፣ ዘማቾችን ፈርቶ መድሃኔ ዓለም ቤተክርስትያን አጥር ግቢ ውስጥ ሰፍሮ ነበር።

«እኛ ያረፍነው ሚካኤል ቤተክርስትያን ባለው ሜዳ ላይ ነው። እዛ እያለን በሶስተኛው ቀን መሆኑ ነው፤ ደጃዝማች ስብሓት፣ ናዕዴር ዓዴት ዘመቻ ላይ ቆይተው ረፈድፈድ ሲል ወደ ዓድዋ መጡ። ከራስ መኰንን ጋርም ተገናኙ። ከዚያ ጉዞ

ወደ መቀሌ ሆነ። በጉዞ ላይ እያለን ግን የራስ መኰንን ተከታዮች የህዝብ ንብረት ዘረፉ። ሰዎችንም ገደሉ። ከዚያ በኋላ፣ ደጃዝማች ስብሓት ስለሁኔታው ለራስ መኰንን አቤቱታ አቀረቡ። ኮንት አንቶኔሊም ይህን እንደሰማ ብዙ ተቆጣ። የሰው ንብረት እንዳትዘርፉ ብሎም አዋጅ አስነገረ» ይሉናል። /ገፅ 128-129/

ከዚህ በላይ እንደተመለከተነው፣ አፄ ምኒልክ በትግራይ ህዝብ ላይ ያደረሱት ግፍና በደል በቀላሉ መገንዘብ እንችላለን። ሌላ ይቅርና ደብተራ ፍስሃ ጊዮርጊስ በሚተርኩልን አንፃር ሲታይ፣ ትንሽ የሰብአዊነት መንፈስ የሚያንፀባርቀው እንኳ፣ ከራስ መኰንን ይልቅ የኢጣልያው መልእክተኛ ኮንት አንቶኔሊ ይመስላል።

አቶ አፈወርቅ ገብረኢየሱስም በበኩላቸው፣ የአፄ ምኒልክ ዘመቻን አስመልክተው እንደሚከተለው ይተርካሉ።

«ይሄ ሁሉ ሲሆን ባረርጌም መገዛት፣ በጋላም እስከ ከፋ ድረስ ሰጥ ብሎ መገዛቱ፣ ለዳግማዊ ምኒልክ ገና ከልባቸው አልደረሰም ነበረ። ያባ ዳኘው ሐሳብ ገና እሩቅ ነበረ። እስከዚህ ድረስ አባ ዳኘው፣ በፈረስ ሶስቱን መአዝን ጋለበ ጋለበና አራተኛው ማዝን ቀረው።

«ያባ ዳኘው ፈረስ ተሸዋ ተነስቶ በጭራው ወሎን እየነካ፣ ባንድ ወገን አዳልን፣ አረርጌን፣ ባንድ ወገን አሩሲን ከፋን፣ ባንድ ወገን ወለጋን ሻንቅላን ረገጠ። ከዚህ በኋላ ያባ ዳኘው ፈረስ፣ ፈረስነቱን ንቆ አንበሳ መሆኑን ጨርሶ ወደደ።

«ይሄ አንበሳ ወደፊቱ የሚያይ እየመሰለ ወደ ኋላው ይመለከት ጀመረ። ይሄ የሰሎሞን አንበሳ፣ ድሮ ፊቱን ወደ

ትግሬ፣ ወደ ጐንደር ቀና ማድረግ ጀመረ:: ለዚህ የሙነተኛ አንበሳ፣ ያረርጌ ሰንጋ፣ የጋላ ድልብ፣ የሸዋ ሽሕር ስለቸውና የትግሬን ያንበሳ ለምድ የለበሰ በሬ መስበር ወደደ» በማለት ነው፣ የአፄ ምኒልክን ባህርይና ማንነት የሚገልፁት:: /ገፅ 47/

አፄ ምኒልክና የውዳሴ ከንቱ ፀሐፊዎቻቸው፣ ሁል ጊዜ የሚያስቡትና የሚናገሩት፣ ስለ የሃረር ሰንጋ፣ የኦሮሞ ድልብ፣ የሸዋ ሽሕር ብቻ ነው:: ማለትም ስለ ሃገርና ስለ ህዝብ ሀልውና እና እድገት ሳይሆን ስለሚበሉት ጮማና ቁርጥ ብቻ ነው እንቅልፍ አጥተው ሌትና ቀን ሲያስቡ የሚታዩት::

አሁን ደግሞ ደብተራ ፍስሃ ጊዮርጊስ፣ ጉዞዋቸውን አስመልክተው ወደሚተርኩልን ልንመለስ ነው:: «መቀሌ ከተማ አካባቢ ስንደርስ እኛን የሚቀበል ብዙ ጭፍራ በከተማዋ መግቢያ ላይ ጠበቀን:: ይዞት የነበረ ሰንደቅ ዓላማ ግን፣ ባለ ሶስት ቀለም ነው የነበረ:: የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ፣ የአንበሳ ስእል ከነዘውዱ ያለበት ነጭ ሃር ነው» በማለት በወቅቱ የተገነዘቡትን ሁሉ ይገልፃሉ:: እዚህ ላይ ጥንታዊው የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ፣ አሁን ባለው ባንዴራ የተተካውም በዘመነ ምኒልክ መሆኑን ነው የምንገነዘበው::

አፄ ምኒልክ መቀሌ ከተማ እንደደረሱ እቴጌ ድንቅነሽ ያቀረቡት ግጥምም ቀጥሎ ያለው ነበር::

«ከመይ ኢኹም ምኒልከይ በይዛ?
መዓርዶ ተምዕኡ ኣይነበርኩምን በኣዘዛ?
ስብሕትዶ ተምዕኡ ኣይነበርኩምን በኣዘዛ?
ሻዕዳ ጣፍዶ ተምዕኡ ኣይነበርኩምን በኣዘዛ፣

መንዐፍዶ ኣይነበረኩምን ከም ኣጕዛ?
ተዐጊዕኹም ዐኒሕኹም ኣብ ስምዕዛ፣
ሃዐይ ዮሃንስ ምስ ሞተ ከም ብዋዛ፣
ሎሚድአ እንታይ ኣምፅኣኩም ሰብ ዘይብላ ገዛ፡፡»

ግጥሙ ወደ አማርኛ ሲመለስ፣

«አፄ ምኒልክ! እንደምን አሉ?
በትእዛዝ ማር ያመጡ አልነበሩም እንዴ?
ሰንጋስ በትእዛዝ ያመጡ አልነበረም እንዴ?
ማኛስ በትእዛዝ ያመጡ አልነበሩም እንዴ?
እንደ በግ አጉዛ ማረፊያ አልነበሩም እንዴ?

«ታዲያ አፄ ዮሐንስ ድንገት፣ ከሞቱ በኋላ፣ ካንድ ዛፍ ስር ተጠግተው ቆይተው፣ አሁን ሰው ወደ ሌለበት ቤት ምን ሊሰሩ መጡ?» የሚል መልእክት ነው ያለው፡፡

አፄ ምኒልክ «ትግሬ ከጠገበና አንድ ከሆነ አይገዛም» የሚል ፍልስፍና እንደነበራቸው አያቶቻችን ይናገራሉ፡፡ ለዚህም ነው፣ የትግራይን ህዝብ ዳግም በማያንሰራራበት ደረጃ ለመምታት፣ እልፍ አእላፍ ሰራዊት አስከትለው የዘመቱት፡፡

እስቲ መጀመርያ አቶ አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ ስለ አፄ ምኒልክ ደግነት እና ህዝባዊነት ምን እንደሚሉን እንስማ፡፡

«ሞት አይቀርምና ምኒልክ ይሞታል፡፡ ይሄ ነው የኢትዮጵያ ጉዳት፤ ይሄ ነው፣ ብርቱ መከራዋ፣ አጤ ዮሐንስ ድሃው ያለውን ሁሉ በተሰሪ ጨርሶ፣ ለወታደር የሚያበላው ቢያጣ፣ ከብቱና ልጆቹን አስሸለጉት፡፡ ዳግማዊ ምኒልክ ግን፣ ድሃው የሚበላው ቢያጣ፣ የገዛ እህልዎን ናኙለት፡፡ ከብት አልቆ

የሚያርስበት ቢያጣ፣ ከሞት የተረፈውን የገዛ በሬዎን እረስበት ብለው በያገሩ ለድሃው አካፈሉት» ይላሉ አፈወርቅ ገብረኢየሱስ፣ ስለ እምዬ ምኒልክ ደግነት ሲመሰክሩ። /ገፅ 66/

እዚህ ላይ ብዙ አስተያየት መስጠት ይቻል ነበር። ነገር ግን የሌላ ፀሐፊ አስተያየት መስማት ስለሚሻል ወደዚያ እንለፍ።

ፀሐፊ ትእዛዝ ገብረስላሴ ደግሞ፣ የአፄ ምኒልክን የትግራይ ዘመቻ አስመልክተው፣ የሚሉት አላቸው።

«ከዚህ በኋላ አፄ ምኒልክ በየካቲት 25 ቀን 1882 ዓ.ም ተነስተው አብርሃ ወአፅብሃ ሰፈሩ። አገሩ ሁሉ ገብሮ የሚዘረፍ ታጥቶ ሰራዊቱ ተርቦ ነበር። እግረኛው ወታደርም ሌሊቱን ሁሉ ሲጓዝ አድሮ፣ ሲነጋ የአብርሃና የአፅብሃን ሃገርና በዙሪያውም ያሉትን አገሮች ሁሉ ዘረፈ። መጋቢት 3 ቀን 1882 ዓ.ም ከእንዳ ስላሴ ተነስተው አፅቢደራ ሰፈሩ። በአራት ቀን ፀዓዳ አምባ ሰፈሩ። ይህም አገር አምባም ዋሻም ያለበት ነውና፣ ባላገሩ እህሉን ከዚያው እያገባ በጠበንጃ ይጠብቅ ነበር። ነገር ግን፣ እግዚአብሄር ቀብቶ ያነገሰውን ንጉስ በጠበንጃ ከልክሎ ማዳን አልሆነለትም። ሰራዊቱም፣ ከአምባም ከዋሻም እየገባ፣ እየተኩሰ እህሉን ዘረፈው። ብርቱውም ዋሻና አምባ በመድፍ ተሰበረ» ነው የሚሉን ፀሐፊ ትእዛዝ ገብረስላሴ ደግሞ በበኩላቸው። /ገፅ 170/

አቶ አፈወርቅ ገብረኢየሱስና ፀሐፊ ትእዛዝ ገብረ ስላሴ፣ ሁለቱም የአፄ ምኒልክ ውዳሴ ከንቱ ፀሐፊዎች መሆናቸው ይታወቃል። ይሁን እንጂ በሁለቱ መሃከል እንኳ ልዩነት ይታያል።

አቶ አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ፣ «ድሃው የሚባለው ቢያጣ፣ አፄ ምኒልክ የገዛ እህላቸውን ናኙለት» ይሉናል።

ፀሐፊ ትእዛዝ ገብረ ስላሴ ደግሞ፣ ከዚህ የተለየ ታሪክ ነው የሚነግሩን። ለማንኛውም፣ ፍርዱን ለአንባቢዎች እተወዋለሁ።

ደብተራ ፍስሃ ጊዮርጊስ በወቅቱ እቦታው ላይ የነበሩ ዘጋቢ ናቸው። ከግራዝማች የሴፍ ጋር እንደነበሩም እራሳቸው ይገልፃሉ። በመሆኑም፣ የአፄ ምኒልክ ግፈኛ ሰራዊት በመቀሌ፣ በእንደርታ፣ በዕራእና በሐራማት ህዝብ ላይ የፈፀመውን አሰቃቂ ግፍና ጭፍጨፋ እንደሚከተለው ይገልፁታል።

«በዚያን ቀን የሸዋ ሰራዊት መቀሌን ሙሉ በሙሉ ዘረፋት። በአካባቢው የነበሩ መንደሮችም በሙሉ ተዘረፉ። እንደርታም እንዳልነበረች ሆነች። በየመንገዱ ትልቅ፣ ትንሽ፣ ህፃን ሳይሉ ሰለቡት።

«ደጃዝማች ስብሐትም ይህንን ጉድ ካዩ በኋላ ደነገጡ። አያይዘውም «የኔ ሰራዊት ከርስዎ ሰራዊት ጋር ተቀላቅሎ ከሄደ ችግር ይፈጠራል። ስለዚህ ለብቻዬ ልንዝ» ብለው ላጤ ምኒልክ ጥያቄ አቀረቡና ተፈቀደላቸው። ደጃዝማች ስብሐትም ከዚያ በኋላ አልተመለሱም። እንደ ሄዱ በዚያው ሸፈቱ» ይሉናል። /ገፅ 134/

የአፄ ምኒልክ ሰራዊት ተግባር ከተራ የበረሃ ሽፍታ ተግባር በታች ነው። ደጃዝማች ስብሐት አንድ መስፍን ናቸው። አፄ ምኒልክ ግን ለስሙ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መሆናቸው ነው። ነገር ግን ደጃዝማች ስብሐት የአፄ ምኒልክን ተግባር ሲያዩ

እጅግ ደነገጡ። «ከነማን ጋር ነው ያለሁት?» ብለው እራሳቸውን በራሳቸው ጠየቁ። ከእናንተ ጋር መሄድ አልችልም፣ ብለውም ወሰኑ። የትግራይ ህዝብ ከልሂቅ እስከ ደቂቅ ተደነቀ። አይቶት ሰምቶት የማያውቀው ግፍ ደረሰበት።

የደብተራ ፍስሃ ጊዮርጊስ ታሪክ ይቀጥላል።

«ቀጥሎም የምኒልክ ሰራዊት እንደርታን አወደማት። እንዳልነበረች ሆነች። ብቻ የወንድ ልጅ ይሁን እንጂ፣ የተገኘ ሰው ሁሉ ይገደላል። ይሰለባል። የእንደርታ ሰዎችም ቢሆኑ ዝም ብለው አልታረዱም። በየቋጥኙና በየጫካው እየተደበቁ የምኒልክን ሰራዊት ሲፋለሙት ነበር።

«የአፄ ምኒልክ ሰራዊትም፣ «ትግራይ ብር ያለበት አገር ነው» እያለ ብር ለማግኘት ብሎ የተገኘውን ቤት ሁሉ እንዳለ ይደረምሰው ነበር። ቤቱን ለመነቃቀልና ለመዝረፍ ጊዜ ካላገኘ ደግሞ፣ እሳት እየለቀቀበት ይሄዳል።

«ሌላ ይቅርና በመላ ኢትዮጵያ የተከበረውን የአብርሃ ወአፅብሃ ገዳምም እንዳለ ዘርፈውታል። የምኒልክ ሰራዊት ባጋጣሚ ሳይዘርፋቸው የቀሩ ከብቶችም በሽታ ገብቶ ጨረሳቸው። ያን ጊዜ ያንድ በሬ ወይም ላም ዋጋ አንድ ብር ብቻ ነበር።

«የምኒልክ ሰራዊት የመግደልና የመስለብ ሱስ ያለበት ነው፣ የሚመስለው። ሰዎችን በገደለና በሰለበ ቁጥር ይፎክራል። በዚያን ጊዜ በትግራይ ህዝብ ላይ ስለ ደረሰው ወሰን የለሽ ግፍ ልብ ያለው፣ ሁሉ ከመጠን በላይ ያዝን ነበር። የቤጌ ምድር ተወላጅ የሆኑ አማሮችም በጣም ያዝኑ ነበር። ያንጊዜም አንድ መነኩሴ፣ «የሰውን ህይወት እንደመናኛ ነገር እየገደልከው ነውና

ወዮልህ? እያለ ይለፍፍ ነበር» በማለት ደብተራ ፍስሃ ጊዮርጊስ በዓይናቸው ያዩትንና የተገነዘቡትን ሁሉ ይተርካሉ። /ገፅ 135/

እንግዲህ ከላይ እንዳየነው፣ የትግራይ ህዝብ ከአፄ ምኒልክና ከትምክሕተኛው ስርዓታቸው ያገኘው ፀጋና በረከት ይህን ይመስላል። ትምክሕተኞች የትግራይን ህዝብ ለማጥፋት ያልሸረቡት ተንኮል፣ ያልፈነቀሉት ድንጋይ፣ ቃል ኪዳን ገብተው ያልተባበሩት ወራሪ ሐይል የለም።

የምኒልክ አረሜናዊ ሰራዊት፣ በትግራይ ህዝብ ላይ ይፈፅመው የነበረ ጭፍጨፋና ግድያ የተመለከቱ የጐንደር ሰዎችም ከመጠን በላይ ያዝኑ እንደነበር አይተናል። ያለ ምክንያት አይደለም። በዘመናቸው እንደዚህ ያለ አረሜናዊ መንግስት ነበር ሲባል፣ ሰምተው ስለማያውቁ ነው። ወጣት፣ ሽማግሌ፣ ህፃን ሳይል ህዝቦችን የሚፈጅ ነው የትምክተኞች ስርዓት።

ደብተራ ፍስሃ ጊዮርጊስ ትረካቸውን እንዲህ በማለት ይቀጥላሉ።

«ከዚያ በኋላ ወደ ዕራእ ነው ያመራነው። በዕራእ አካባቢ ለማንም የማይበገሩ ተራሮች አሉ። የምኒልክ ሰራዊትም የሚዘረፍ ንብረት ለማግኘት ወደ ተራሮቹ ለመውጣት ብዙ ሞከረ። ነገር ግን አልሆነለትም። ህዝቡም ከምኒልክ ሰራዊት ጋር ግብግብ ገጠመ። እዚያ ላይም ከግራ ቀኙ ብዙ ሰው አለቀ። ከትግራይ በኩል የሞቱት ግን አብዛኞዎቹ ሽማግሌዎችና ደካሞች ብቻ ነው የነበሩ።

«በዚህ ቦታ ደግሞ አንድ ዋሻ ያለው ተራራ ነበር። የምኒልክ ሰራዊትም ዋሻውን መደርመስ አልቻለም። በኋላ ግን ዋሻው በመድፍ እንዲደረመስ አፄ ምኒልክ ኢልጊ ለተባለው የመድፍ ተኳሽ አዘዙት። ዋሻውም ፈረሰ። ከተራራው ጫፍ ላይ ግን መድፍ የማይደረስበት ሜዳ አለ። ቢሆንም ምንም ማድረግ ስላልተቻለ ቀረ።

«ከዚያ በኋላ ግን አንድ ሰው ከተራራው ጫፍ ላይ ሆኖ፣ «አንታ ሸወታይ ንፋለጥ እኮ ኢና፡ ዮሐንስ እንተ ሞተ ቆልዑኡስ ዝሞትና አይምሰልካ» አለ። ወደ አማርኛ ሲመለስም፣ «እናንተ የሸዋ ሰዎች! እንተዋወቃለን'ኮ! አፄ ዮሐንስ ቢሞቱ እኛ ልጆቻቸውስ የሞትን መሰልናችሁንዴ?» የሚል መልእክት ነው ያለው። ንጉስ ምኒልክም ይህንን እንዳሰሙ ተቆጡ። መድፍ ተኳሹን ፈረንጅ ይዘው ወደ ተራራው አቀኑ። ነገር ግን ምንም ማድረግ አልተቻላቸውም። የሆነ ሆኖ እዚያ ቦታ ላይ ነገሮች ሁሉ ጠንከር ብለው ነበር። ከዚህ ጋር ተያይዞ ደግሞ በአካባቢው በሽታ እጅግ ተስፋፋ» ይላሉ ደብተራ ፍስሃ ጊዮርጊስ። /ገፅ 136-137/

አፄ ምኒልክ በትግራይ ህዝብ ላይ የፈፀሙት ግፍና በደል በቃላት መግለፅ አይቻልም። የትግራይ ህዝብም፣ ያለ ምክንያት አይደለም ዘመኑን፣ «ዘመነ ሸዬ» /ዘመነ ሸዌ/ የሚለው። በዘመነ አፄ ምኒልክ፣ በትግራይ ህዝብ ላይ ያልተፈፀመ ኢሰብአዊ ተግባርና ወንጀል አለ ለማት አይቻልም። «ዘመነ ሸዬ» ማለትም ለትግራይ ህዝብ ዘመነ መከራ፣ ዘመነ ረሃብ፣ ዘመነ እልቂትና ዘመነ ስደት፣ ዘመነ ዘረፋና ኢሰብአዊነት ማለት ነው።

«ያንጊዜ አ·ነት ለመናገር የወዲህኛው ትግራይ ይቅርና፣ የሐማሴንና አከለጉዛይ ሰዎችም እንባ ተናነቃቸው። አንድ የተንቤን ሰውም የአፄ ዮሐንስ እልፈት ትዝ አለውና እጅግ አለቀሰ» ይላሉ ደብተራ ፍስሃ ጊዮርጊስ የዕራእ ትረካቸውን ሲያጠቃልሉ። /ገፅ 132/

በዚያን ጊዜ ትግራይ፣ ኤርትራ የሚባል ነገር አይታወቅም። ትግራይ ትግርኚ ነው የሚባለው። ወይም ደግሞ ከመረብ ወዲያ ትግራይ፣ ከመረብ ወዲህ ትግራይ ይባል ነበር። ደብተራ ፍስሃ ጊዮርጊስም፣ በዚህ ምክንያት ነው፣ «የወዲህኛው ትግራይ የወዲያኛው ትግራይ» የሚሉት። የህዝቡ ቋንቋም «ዘረባ ሐበሻ ወይም ዘረባ ትግራይ» ይባል ነበር። «ትግርኛ» የሚለው ቃል ግን፣ ከአማርኛ ቋንቋ ስርዓተ ሰዋስው ጋር በተያያዘ መልኩ ከ19ኛው ክፍለ ዘመን በኋላ የመጣ ስያሜ ነው። ለምሳሌ የዓድዋው ተወላጅ ደብተራ ማቴዎስ፣ በ1858 ዓ/ም /1866 ኤ/ ወንጌልን ወደ ትግርኛ ሲመልሱ «ወንጌል ቅዱስ ናይ ጐይታና፣ ናይ መድሐኒትና፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ብትግራይ» በማለት ነበር የተረጐሙት።

የደብተራ ፍስሃ ጊዮርጊስ ትረካ አሁንም አላበቃም። የአፄ ምኒልክን እግር እየተከተሉ ያዩትን ግፍ ሁሉ አንድ ባንድ እየመዘገቡ ነው። የትግራይ ህዝብ ይህን ዘመን ባጠቃላይ፣ «ክፉእ ዘበን» ብሎ ነው የሚጠራው። «ክፉእ ዘመን» የሚባለው በኢትዮጵያ አቆጣጠር ከ1882 እስከ 1884 ዓ.ም ያለውን ዘመን ነው። «ዘመነ ሽዬ» የሚባለው ግን የ1888 ዓ.ም የዓድዋ ጦርነት

የተደረገበት ዘመን መሆኑ ነው። ደብተራ ፍስሃ ጊዮርጊስ ትረካቸውን ቀጠሉ።

«ዕራእ ላይ ትንሽ ቀን ቆይተን ወደ ሐራማት አቀናን። ሐራማት ላይም ለምኒልክ ወራሪ ሰራዊት የማይበገሩ ተራሮች አሉ። እንደርታ፣ ሜዳ በመሆኑ ለወራሪው የምኒልክ ሰራዊት ምቹ ነበር። የዕራእ እና የሐራማት አካባቢ ግን፣ ተራራማ በመሆኑ፣ ለምኒልክ ሰራዊት እጅግ አስቸጋሪ ሆነበት። ስለሆነም፣ ወራሪው ሰራዊት ሐራማትን ሊያጠቃት አልቻለም። ህዝቡም እንዳለ በየተራራው ተንጠላጥሎ የድንጋይ እሩምታ ለቀቀበት» እያሉ በወቅቱ ያዩትንና የተገነዘቡትን ያብራራሉ።

የደብተራ ፍስሃ ጊዮርጊስ ዘገባ ብዙ ነው አሁንም የሚሉን አላቸው።

«ሁሉን ትቼ ሐራማት ውስጥ ከሚገኙት ተራራሮች መሃከል ባንዱ ስለ ተፈፀመው ሁኔታ ብቻ ልናገር። በዚሁ ቦታ አንድ ባላባት ነበር። ብዙ ታጣቂዎችም ነበሩት። በተራራው ላይም ወሃ አለ። ወሃው እስከ ታች ድረስ ነው የሚፈሰው። የተራራው በር ግን አንድ ብቻ ነው። ሰዎቹም ተራራውን ለጠላት እንደማይጋለጥ አድርገው አመቻችተውታል። ምናልባት የምኒልክ ሰራዊት ለዝርፍያ ከመጣ ለመከላከል በማሰብም፣ ከገደሉ የሚለቀቁ ትላልቅ ድንጋዮች /መረጋሕ/ አዘጋጅተው ነበር።

«የምኒልክ ወራሪ ሰራዊትም ዓይኑን ጨፍኖ ተራራው በር ላይ የተደረደረውን እህልና ንብረት ለመዝረፍ ወደ ተራራው አቀና። እነዚያ አድፍጠው ሲጠባበቁ የነበሩ ሰዎችም ሳይታሰብ የጥይት እሩምታ አዘነቡባቸው። በተጨማሪም የተለያዩ

ድንጋዮችን አከታትለው ሲለቁባቸው ሰው በሰው ላይ እየተደራረበ ወደ ገደል ገባ:: ይህን ሁኔታ ያዩ ሰዎች በሙሉ ወደዚያ ቦታ አይመለሱም ነበር:: ታሪኩን በወሬ ብቻ የሰሙቱ ግን፣ እስቲ እኛም እንሞክረው እያሉ እየመጡ እዚያው አለቁ:: በዚሁ መልክ ሶስት ቀን ሙሉ የሞት የሽረት ፍልሚያ ተደርጓል:: በኋላ ግን አፄ ምኒልክ ወደዚያ ቦታ ማንም ሰው እንዳይ ሄድ ብለው አዘዙ» ብማለት የትግራይ ህዝብ ስላካሄደው የሞት የሽረት ተጋድሎና ውጤቱ ምን ይመስል እንደነበር ይተርኩልናል:: /ገፅ 140-141/

የፅራእና የሐራማት ተራራሮች፣ የአፄ ምኒልክን ግፈኛ ሰራዊት መክተው በመግጠም ያሳዩትን ህዝባዊ ወገንተኝነት ስመለከት መንፈሴ ረካ:: አንድ ነገርም ትዝ አለኝ:: እሱም የአርቲስት ኢያሱ በርሀ ግጥምና ዜማ መሆኑ ነው:: የፅራእ እና የሐራማት ተራሮች የፈፀሙት ጀብዱና የኢያሱ በርሀን ግጥሞች ሳነፃፅራቸው፣ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅ ሆነው ታዩኝ:: እውነት ለመናገር ኢያሱ በርሀም በወቅቱ ከደብተራ ፍስሃ ጊዮርጊስ ጋር ኣብሮ የነበረ ይመስላል:: የኢያሱ በርሀ ግጥምም፣ በከፊል እንዲህ የሚል ይገኝበታል::

«ባሕርና ትሓፋሽ ህዝብና፣
ስንቅና ወያናይ ሓቦና፣
ድፋዕና ጎቦታት ዓድና፣
ዕጥቅና ካብ ፀላእትና፣
ዓወትና ፍረ መስዋእትና፣
እምነትና ኣብ ቅኑዕ መትከልና፣
እምባታት ሩባና፣ ጎቦታት ዓድና፣

ኣብ ጒድንና ኣለዉ ናይ ኩናት ዕርድና፣
ግዳማዊ ሓገዝ ኣይኮነን ተስፋና፣
ወሳናይ ነጥቢ ኢዩ ውሽጣዊ ቃልስና፣
ናይ ታሪኽ መንኰርኰር ትውዑዕ ኣብዝሓ፣
ነቒሖ ዝቃለስ ንናይ ደርቡ ረብሓ፣
ንሕና ዓሳ ኮይንና ንሰውን ባሕርና፣
ዝመፀ ፀላኢ ክንምክቶ ኢና።
ንሓፋሽ ሓገዝና ካብኡ ተደጊፍና፣
ክንግስግስ ክንምዕብል፣ ክንዕወት ውን ኢና»

የግጥሙ መልእክት ባጭሩ እንደሚከተለው ነው።

«የኛ ባሕር ሰፊው ህዝባችን ሲሆን፣ ስንቃችን ደግሞ አብዮታዊ ወኔያችን ነው። እምነታችን ግን በትክክለኛው መስመራችን ላይ የተመሰረተ መሆኑ ይታወቃል። የአገራችን አመባዎችም ምሽጎቻችን ናቸው። ትጥቃችን ግን ህይወት ገብረን ከጠላቶቻችን እናገኛለን። አምባዎቻችንና ወንዞቻችን በጦርነት ጊዜ ሁሌ ከጐናችን አይለዩም። ተስፋችንም በውጭ አገር ድጋፍ ላይ የተመሰረተ አይደለም። ወሳኙ ነጥብ ውስጣዊ ትግላችን መሆኑን እንገነዘባለን። ሰፊው ህዝባችንም የታሪክ መንኮራኩር ነውና፣ ለመደባዊ ጥቅሙ በንቃት ነው የሚዋደቀው። ስለሆነም፣ እኛ እንደ ዓሳ እሱም እንደ ባሕር ሆነን በመታገል የመጣውን ጠላት ሁሉ እንመክተዋለን። በመጨረሻም ከህዝባችን ጋር እጅና ጓንት ሆነን ወደፊት መራመዳችንና ድል ማድረጋችን አይቀሬ ነው» ይለናል፣ አርቲስት ኢያሱ በርሀ።

አፄ ምኒልክ ከአዲስ አበባ ተነስተው መቀሌ ከተማ እስኪደርሱ ድረስ፣ አንዲት ጥይት የተኮሰባቸው ሰው አልነበረም። በጭፍን ጥላቻ ተነሳስተው ሲጨፈጭፋት ግን፣ ባልሞት ባይ ተጋዳይነት መመከቱ አልቀረም። ቀደም ብዬ እንደገለፅኩት፣ አፄ ምኒልክ «ትግሬ ከጠገበና አንድ ከሆነ አይገዛም ወይም አይቻልም» የሚል እምነት ነበራቸው። በተጨማሪም የትግራይ ህዝብ ብዙ ብር አለው፣ ተብሎ ስለሚታመን ገበሬውን እየዘረፉ ሃብት ማካበትና ህዝቡን ማደህየትም እንደ ስልት የተያዘ በመሆኑ አስፈላጊ ነበር። አፄ ምኒልክ ወደ ትግራይ ያደረጉት ዘመቻም እነዚህን ሁለት ነጥቦች ለማሳካትና ተግባራዊ ለማድረግ ነው።

የደብተራ ፍስሃ ጊዮርጊስ ትረካ አላበቃም። እስቲ ቀጣዩ ትዝብታቸው ምን እንደሚመስል ደግሞ እንከታተል።

«የአፄ ምኒልክ ሰራዊት፣ ለምኖ ያመጣቸው ይመስል የትግራይን ህዝብ ይረግሙት ነበር። የትግራይን ህዝብ ቋንቋ ለመስማትም እጅግ ነበር የሚያስጠላቸው። /ገፅ 140/

«ቀጥሎ ግን ጉዟችን ወደ ዓጋመ ነው፣ እየተባለ ይወራ ነበር፣ ይህ ወሬ እንደተሰማ፣ ሰው ሁሉ በሓሳብ ተዋጠ። ቀደም ብሎ ይወራ እንደነበረው የአፄ ምኒልክ ዓላማ መጀመርያ ዓጋመን ማጥፋት፣ ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ ሌሎች አካባቢዎችን እየደመሰሱ ወደ አኩሱም ለመሄድ ነበር።

«ወደ ዓጋመ የመሄዱ ሁኔታ ግን፣ ለአፄ ምኒልክ ሰራዊት እጅግ አስቸጋሪ መስሎ ታየው። አፄ ምኒልክ ግን ዓጋመን ለማጥፋት ተዘጋጅቷል። የዓጋመ ሰዎችም፣ ለምኒልክ ሰራዊት አንምበረከክም ብለው ህይወታቸውን ለመስጠት ቆርጠኞች ነበሩ።

በየጫካውና በየቋጥኙ ተደብቀው ወራሪውን የምኒልክ ሰራዊት ለመመከት ይጠባበቁ ነበር:: የሓሓይለና የሌሎች አካባቢዎች ህዝብም ከምኒልክ ሰራዊት ዘረፋና ጥፋት ለመዳን በመመካከር ላይ ነበር:: የምኒልክ ሰራዊት ይፈፅመው የነበረው ግፍ ከመጠን በላይ በመሆኑ፣ እነዚያ ተባባሪዎች የነበሩ እንኳ፣ ከደጃዝማች ስዩም አባጐበዝ በቀር በሙሉ የአፄ ምኒልክ ጠላቶች ሆኑ:: ሰው ይቅርና የአፄ ምኒልክ የጋማ ከብቶች እንኳ ካገራቸው ይልቅ የትግራይ መሬት ተመቻቸው» በማለት ነው፣ በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ የሚገልፁት:: /ገፅ 140/

ደብተራ ፈስሃ ጊዮርጊስ ከዚህ በላይ እንደተገለፀው በትግራይ ህዝብ ላይ የተፈፀመውን ግፍና ኢሰብአዊ ድርጊት ከገለፁ በኋላ «በኢትዮጵያ የተደረገ ነገር ሁሉ አሰቃቂ ነው:: እንኳንስ ተፅፎ ለሰው ሊተላለፍ ቀርቶ ማስታወስም ባለስፈለገ ነበር:: ስለሆነም እዚህ ላይ ላቁም» ብለው ያጠቃልሉታል:: /ገፅ 144/

የትግራይ ህዝብ በዘመነ ምኒልክ የደረሰበት መከራ በቃላት መግለፅ አይቻልም:: «ከሰው ሁሉ እንዳበሻ፣

ካውሬ ሁሉ እንደ አንበሳ ጨካኝ ፍጥረት አላየንም» እያሉ የኢጣልያ ወራሪዎች ስሙ ሲነሳ ብቻ የሚፈሩትና የሚንቀጠቀጡለት ጀግና እና ኩሩ ህዝብ፣ በአፄ ምኒልክ ሴራና ሃገራዊ ክሕደት ምክንያት የጠላቶቹ መተረቢያና መሳለቂያ ሆነ:: አስመራ ከተማ ላይ ወድቆ ከኢጣልያኖች እጅ ፍርፋሪ ለመነ:: በጐዳጉዲ፣ በጉራዕ፣ በሰሐጢ፣ በኮፊትና በዶግዓሊ አውደ ውግያዎች አባቶቻችን ያስመዘገቡት የጀግንነት ውሎና አኩሪ

ታሪክ፣ በአፄ ምኒልክ ሃገራዊ ክህደት ምክንያት ተደመሰሰ። ያባቶቻችን ደም፣ ደመ ከልብ ሆኖ ቀረ።

የኢጣልያ ወራሪዎችና ትምክሕተኞች በትግራይ ህዝብ ላይ አፌዙ። ሰደቡት፣ አዋረዱት። አፄ ምኒልክ «ትግሬ ከጠገበና አንድ ከሆነ አይገዛም» በሚል ፍልስፍናቸው እየተመሩ፣ ያለ የሌለ ጥሪቱን ዘረፉት። ህዝባዊ አንድነቱንም ለጥፉት እንጂ፣ ሊልማት በማይውል ሰይጣናዊ ጥበባቸው አዳከሙት።

# ምዕራፍ ስድስት

# ኢጣልያና የትግራይ ህዝብ የህልውና ተጋድሎ

አፄ ምኒልክ እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸውን አውራጃዎችና ከተሞች ከደመሰሱና ከዘረፉ በኋላ ወደ ሸዋ ተመለሱ። ሰራዊታቸውም ከትግራይ ህዝብ የዘረፈውን ከብትና ንብረት ሰብስቦ ወደ ሃገሩ ጉዞ ጀመረ። ትግራይ አሁን መቶ በመቶ ወድማለች። የአባቴ እናት ወይዘሮ አብነት ገብረወልድ ይባላሉ። በ1945 ዓ.ም-በ95 ዓመታቸው ነው ከዚህ ዓለም የተለዩት።

ስለሆነም «ክፉ ዘመንን» እንዲህ ይገልፁታል። «አፄ ዮሐንስ መተማ ላይ ከሞቱ በኋላ በትግራይ ህዝብ ላይ መከራ ወረደ። ከብቶች አለቁ። የሚታረስ በሬ ጠፋ። ሰው በሙሉ በተላላፊ በሽታ አለቀ። በዘመኑ እንኳን በህይወት የተገኘ ይቅርና ማንኛውም እንስሳ ሞቶ የተገኘ ጥንብ ሁሉ ይበላ ነበር። ጅንዶ፣ አጉዛ፣ የበሬ ቆዳ ከተገኘማ ትልቅ ፀጋ ነው። በዚያን ጊዜ የሰው ስጋ የበሉ ሰዎችም ነበሩ» ይላሉ አያቴ። «ይህን ሁሉ መከራ ያመጡብን ደግሞ አፄ ምኒልክና ኢጣልያ ናቸው። ኢጣልያ ከብት የሚጨርስ መርዝ ለአጤ ምኒልክ ስለሰጣቸው ነው» ብለው ነበር የሚያምኑት። ይሁን እንጂ በሽታው በአፄ ምኒልክ አማካይነት ነው የመጣ የሚል እምነት ባይኖረኝም፣ ችግሩ የትግራይን ህዝብ እንዳልነበረ በማድረጉ ግን፣ አፄ ምኒልክ ደስተኛ ነበሩ። የችግሩም ተባባሪም ነበሩ። ስለሆነም ጉልበት ያለው

ዓይኑን ጨፍኖ የትም ተሰደደ፡፡ ጉልበት የሌለው ደግሞ ቀባሪ አጥቶ እየሰማ፣ እያየ፣ የጅብና የአሞራ ሲሳይ ሆኖ ቀረ፡፡

መረብ ምላሽ አሁን በኢጣልያ ቁጥጥር ስር ነው ያለችው፡፡ ኤርትራ የሚል ስያሜም ወጥቶላታል፡፡ ኢጣልያ የትግራይ ህዝብ ጠላት ነው፡፡ አፄ ምኒልክም የትግራይ ህዝብ ጠላት ናቸው፡፡ የአዲሲትዋ ኤርትራ ህዝብ ግን፣ የትግራይ ህዝብ ግማሽ አካልና ወንድም ነው፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳ ኤርትራን እየገዛ ያለው መንግስት የትግራይ ህዝብ ጠላት ቢሆንም፣ ነዋሪው ህዝብ ማለትም፣ የኤርትራ ህዝብ ግን የትግራይ ህዝብ ወንድም በመሆኑ፣ የትግራይ ህዝብ ወደ ኤርትራ መሰደድን መረጠ፡፡ ወገኔና ወንድሜ ወደሚለው ህዝብ፡፡

ዐሐፌ ትእዛዝ ገብረስላሴና አቶ አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ እንደሚተርኩልንም፣ የከብት እልቂቱም ሆነ ቸነፈሩ በመላ ኢትዮጵያ ተከስቶ ነበር፡፡ ከትግራይ ጋር ሲነፃፀር ግን የስማይና የምድርን ያህል ልዩነት ነበረው፡፡ አንደኛ የትግራይ ህዝብ 17 ዓመት ሙሉ በጦርነት ተጠምዶ በመክረሙ ሰብአዊና ቁጠባዊ አቅም አልነበረውም፡፡ በተጨማሪ ደግሞ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንደሚባለው፣ አፄ ምኒልክ ለመዝመት አቅም ያለውን ሰው ሁሉ አስከትለው ደምስሰውታል፡፡ ስለዚህ የትግራይ ህዝብ የሚላስ የሚቀመስ ነገር ፈፅሞ አልነበረውም፡፡ ይህ ብቻ ግን አይደለም፡፡ «የኔ ህዝብ ነው» ብሎ የሚያረጋጋው፣ የሚመራውና፣ የሚያስተዳድረው መንግስትም አልነበረውም፡፡ ቀደም ብዬ እንደገለፅኩት፣ ንጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዱኝም ይህን ሁሉ ስለተገነዘቡ ነው፣ «አፄ ምኒልክ የትግሬን ህዝብ እንደ ህዝባቸው

አልቆጠሩትም» ብለው የሃፉት:: የከብቶች በሽታም የመጣው፣ በኤርትራ በኩል ነበር ብለው አባቶቻችን ይናገሩ ነበር:: ለዚህም ነው፣ ጣልያንና አፄ ምኒልክ ናቸው ያመጡብን ብሎ ህዝቡ የሚናገረው:: ምክንያቱም ሁለቱም የትግራይ ህዝብ ጠላቶች ነበሩ እና ነው::

እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል:: የከብት እልቂቱም ሆነ ረሃቡ ኤርትራ ውስጥም ካለ፣ ለምንድነው የትግራይ ህዝብ ወደ ኤርትራ የተሰደደው? ብለን ለመጠየቅ እንገደድ ይሆናል:: ጥያቄው ትክክል ነው::

ነገር ግን ኤርትራ ውስጥ ያለው ቅኝ ገዥ አውሮጳዊ ሃይል መሆኑ ይታወቃል:: በመሆኑም በቁጥጥሩ ስር ያለውን ህዝብ ለመመገብ ችግር አልነበረውም:: በተጨማሪም ይህ ወቅት ለኢጣልያ ቅኝ ገዥዎችም ጥሩ አጋጣሚ ነበር:: ማለትም በትግራይና በኤርትራ ህዝቦች መሃከል የአመለካከት ልዩነት ለመፍጠር ተጠቅሞበታል::

ጊዜው የትግራይና የኤርትራ ጀግኖች በአፄ ምኒልክና በኢጣልያ መሃከል የተፈረመውን የውጫሌ ውል አንቀበለውም ብለው በጋራ የሚንቀሳቀሱበት ወቅት ነው የነበረው:: ስለሆነም የኢጣልያ ቅኝ ገዥዎች፣ የኤርትራውያንን ልብ ለመስለብ በከፍተኛ ደረጃ ተንቀሳቀሱ:: ለቅስቀሳ ከሚጠቀሙባቸው ነጥቦች መሃከልም የሚከተሉት ይገኙበታል::

«እውቀት በመቀበል፣ በፈጠራ ችሎታ፣ በግብረ ገብነትና በመንፈሰ ጠንካራነት፣ ኤርትራውያን፣ ከመረብ ደቡብ ካሉ ህዝቦች ይልቃሉ:: የመረብ ሰሜን ህዝቦች፣ ከመረብ ደቡብ

ህዝቦች "በተፈጥሮኣቸው" የተለዩ ናቸው። እያሉ ያለ ሐፍረት ይቀሰቅሱ ነበር» ይላል መድሃኔ ታደሰ። /የኤርትራና የኢትዮጵያ ጦርነት ገፅ 41/ «የኤርትራ ሰው በማንኛውም መመዘኛ፣ ከዓጋመ/ ከትግራይ ሰው/ በላይ ነው። የሚል ትምህርት በተከታታይ ይሰጣቸው ነበር። ፋሺስታዊና ዘረኛ አመለካከቱን በከፍተኛ ደረጃ ለማስረፅም «እናንተ ኤርትራውያን ምርጥና ልዩ ዘሮች ናችሁ። በጀግንነትም የሚወዳደራችሁ ህዝብ የለም። እንደ ሌላው ጥቁር ህዝብ አይደላችሁም። ነጭ ካልሆነ በስተቀር እናንተን ድል ሊያደርግ የሚችል ጥቁር ህዝብ በዚህ ዓለም ሊገኝ አይችልም። እናንተን ይዞን የማንቆጣጠረው አገርና፣ ድል የማናደርገው ምድራዊ ጦር አይኖርም» እያለ ነበረ የኢጣልያ ወራሪ ሃይል ኤርትራውያንን የሚቀሰቅሰውና የሚደልለው። ይህ ዘረኛና ፋሽሽታዊ ኣመለካከትም ቀስበቀስ ባንዳንድ የውሃን ኤርትራውያን አእምሮ ውስጥ መስረፁ አልቀረም። የሻዕቢያዎች የማንነት ቀውስ በሽታም፣ ከዚህ በላይ ከተገለፀው፣ የቅኝ ገዥዎች ውስጠ ባዶ የማንነት ልዕልና ጋር የተያያዘ ነው። ይህ ሁሉ ጥረት ግን፣ የትግራይና የኤርትራ ህዝቦችን ታሪካዊ አንድነት ለመበጣጠስና ረግጦ ለመግዛት ብቻ ነው። በአሁኑ ወቅትም እንዲሁ፣ የትምክሕት ሐይሎች እና የሻዕቢያ መንግስት፣ መሰረት አልቦ የሆነ የጥላቻ መርዝ በመርጨት፣ የትግራይንና የኤርትራን ህዝቦች ታሪካዊ አንድነትና ቤተሰባዊ ትስስር ለመበጣጠስና ለመበከል፣ ከንጉስ ምኒልክና ከንጉስ ኡምበርቶ የታሪክ አደራ የተቀበሉ ይመስላል። ይሁን እንጂ፣ በወርቃማ የትውልዶች ታሪክ ለዘመናት የተገነባው፣ የትግራይና የኤርትራ ህዝቦች ቤተሰባዊ

ትስስር ግን፣ ሻዕቢያና የትምክሕት ሐይሎች የታሪክ አደራቸውን ለመተግበር ሲሉ፣ ነጋ ጠባ በሚረጩት የጥላቻ መርዝ ምክንያት ይበከላል ተብሎ አይገመትም::

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም፣ «የክሕደት ቁልቁለት» በተባለ መፅሐፋቸው፣

«የኤርትራና የትግራይ ማሕበረሰቦችን የሚለያቸው ነገር ቢኖር የኢጣልያ ቅኝ አገዛዝ ታሪክ ነው:: በተረፈ ከመረብ ሰሜንና ደቡብ ያሉት ሰዎች ከጥንት ጀምሮ እየተጋቡና እየተዋለዱ በዝምድናና በቋንቋ፣ በባህል ተሳስረው ለብዙ ምእተ ዓመታት የኖሩ ናቸው:: የኤርትራ ተወላጅ ሆኖ ከትግራይ ሰዎች ጋር የማይዛመድ፣ የትግራይ ተወላጅ ሆኖ ከኤርትራ ሰዎች ጋር የማይዛመድ ሰው መኖሩ ያጠራጥራል:: እንደሚሰማው ከሆነ በሻዕብያም ሆነ፣ በወያኔ አመራር ውስጥ ያሉት፣ ከኤርትራም ከትግራይም የሚወለዱ መሆናቸው አጠቃላይ ሁኔታውን የሚያመለክት ነው» ይሉናል:: /ገፅ 49/

እዚህ ላይ ከፕሮፌሰር መስፍን ጋር ልዩነት አይኖረኝም:: ነገር ግን ከዚህ በበለጠ መልኩ ነው መቀመጥ ያለበት:: የኤርትራና የትግራይ ህዝብ በመሰረቱ አንድ ህዝብ ነው:: በጋብቻና በባህል ብቻ የሚንጠለጠል አይደለም:: ይህን ህዝብ ከሁለት እንዲከፈል ያደረጉትም የስልጣን ጥመኛው አፄ ምኒልክ ናቸው::

ፕሮፌሰር መስፍን ሌላም የሚሉን አላቸው::

«ምናልባትም ምኒልክ ዓድዋ ድረስ ዘምተው ትግራይን ነፃ ባያወጡት፣ ኤርትራ ከተባለው የኢጣልያ ቅኝ ግዛት ውስጥ ገብቶ

እንደ ኤርትራ የፈረንጅ አሽከር ሆኖ ይሰለጥን ነበር በማለት፣ የወያኔ መሪዎች በአፄ ምኒልክ ላይ የጠነከረ ቂም አድሮባቸው ይሆናል» ይላሉ የኛው ፕሮፌሰር:: /ገፅ 47/

ፕሮፌሰር መስፍን እንደመጣላቸውና እንደሚመስላቸው እንጂ፣ አስበውና አውቀው የሚናገሩ አልመሰለኝም:: አፄ ምኒልክ ስልጣንን ለመጨበጥ ብቻ ሲሉ በገፀ በረከት መልክ ሃገርን ለባዕዳን የሚያበረክቱ ንጉስ ናቸው:: የትግራይ ምድር ለወራሪዎች የእግር እሳት ነው:: አይደፈርም:: የትግራይ ህዝብና የትግራይ ምድር ለባዕዳን አይመችም:: የትግራይ ምድር በኢጣልያ ወራሪዎች የተደፈረውና የተረገጠው ሃገራዊ ፍቅር የሌላቸው ትምክሕተኞች ስልጣን ከጨበጡ በኋላ ነው::

ፕሮፌሰር! ለመሆኑ የትግራይ ህዝብ በስልጣኔ ይታማል እንዴ? የአክሱማውያን ሐወልቶች፣ የማሕሌታይ ያሬድ ዜማዎች፣ የአበሻ ልብሶች፣ የወርቅና የብር ጌጣጌጦች ወዘተ ሁሉ እኮ የትግራይ ህዝብ ቅርሶችና የስልጣኔ መገለጫዎች ናቸው:: የኢትዮጵያ ፊደል፣ የኢትዮጵያ ስርዓተ መንግስት፣ ስርዓተ ሃይማኖት፣ ጤፍ፣ እንጀራ፣ ጠላ፣ ጠጅ ወዘተ የእነዚህ ሁሉ ምንጭና ባለታሪክ እኮ የትግራይ ህዝብ ነው:: ከፈረንጅም ይሁን ከጥቁር ወይም ከብጫ ህዝብ፣ እውቀትን መሸመት ችግር የለውም:: ይሁን እንጂ፣ የትግራይ ህዝብ እንደ ትምክሕተኞች ለስልጣንና ለጥቅም ብሎ አገሩንና ክብሩን ለባዕዳን አሳልፎ መስጠት ግን፣ ታሪኩና ማንነቱ አይፈቅድለትም:: በክሕደት የተመዘገበ የታሪክ ጠባሳም የለውም:: ትምክሕተኛው ፕሮፌሰር መስፍንም፣ የትግራይን ህዝብ ማንነትና ትክክለኛ ታሪክ

ለመገንዘብ የሚችል ንፁህ አእምሮ ቢኖራቸው ኖሮ፣ ጀግናውን የትግራይ ህዝብ «የፈረንጅ አሽከር ሆኖ ይሰለጥን ነበር» ብለው ሊያፌዙበት ባልደፈሩም ነበር።

በመጨረሻ ላይ ግን፣ ፕሮፌሰር መስፍንና ትምክሕተኞች ሊገነዘቡት የሚገባ አንድ ነጥብ አለ። ይሄውም የኢትዮጵያ ህዝብ ባጠቃላይ፣ በተለይ ደግሞ የትግራይ ህዝብ፣ በሁሉም መመዘኛ አንድ መቶ ዓመት ወደ ኋላ ሊጐተት የቻለው፣ በዘረኛውና ትምክሕተኛው አንኮበራዊው ስርዓት ምክንያት ብቻ መሆኑን ነው።

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ችግሮች በሙሉ፣ ከሞላ ጐደል ከአፄ ምኒልክ ከፋፋይ ስርዓት ጋር የተያያዙ ናቸው። ለምሳሌ የትምክሕተኝነት ወይም የነፍጠኝነት አመለካከት፣ የዘረኝነትና የመናናቅ አመለካከት፣ የኤርትራ ችግር፣ የዓባይ ወንዝ ውል ችግር ወዘተ ሁሉ አፄ ምኒልክ የፈጠሩዋቸው ችግሮች ናቸው።

የኤርትራ ችግር ከተነሳ ከዚሁ ጋር የተያያዙ አንዳንድ ነጥቦችም ልጨምር። ራስ መኰንን አፄ ምኒልክ ከኢጣልያ መንግስት ጋር የተዋዋሉዋቸውን ስምምነቶች ለማስፈፀም ወደ ሮማ ተልከው እንደነበር ቀደም ሲል ተመልክተናል። ራስ መኰንን የተላኩበትን ስራ አከናውነው እስኪ መለሱ ድረስ ደግሞ፣ የኢጣልያ ወታደሮች በውጫሌ ውል ከተበረከቱላቸው መንደሮች ውጭ አልፈው፣ እስከ መረብ ወንዝ ድረስ ተቆጣጥረውት ቆዩ። ቀጥለውም ወታደሮቻችን የረገጡት መሬት በሙሉ የኛ ግዛት መሆን አለበት ብለው ጠየቁ። አፄ ምኒልክም

ከኢጣልያ መንግስት ጋር መጋጨትን ስለሚፈሩ፣ የቀረበላቸውን ጥያቄ አሜን ብለው በመቀበል ጎዳ ውስጥ ገብተው ፈረሙላቸው። ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም፣ ግን፣ «የክሕደት ቁልቁለት» በተባለ መፅሐፋቸው እንዲህ ይላሉ። «እስቲ እዚህ ቆም ብለን መቶ ዓመታት ወደኋላ እንመለስ፣ ኢጣልያ የባሕር ምድርንና ትግራይን በሙሉ ወረረችና አምባላጌ ደረሰች። ምኒልክና ጣይቱ የኢጣልያንን ጦር በታትነው አስለቀቁ። በመቀሌ መሽጎ የነበረውን የኢጣልያ ጦር አሸንፈው የበላይነታቸውን አረጋገጡ። መጨረሻውና ዋናው ጦርነት ዓለም በሙሉ የሚያውቀውን ዓድዋ ላይ ድል ተቀዳጁ» ይሉናል። /ገፅ 45/

ይህ አባባል ከአንድ ተራ ሰው ቢነገር ኖሮ ብዙም ሊያስደንቅ አይችልም ነበር። ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ግን፣ አሉ ከሚባሉት ምሁራን አንዱ ሆነው እያለ ይህን የመሰለ ሐቅነት የሌለው በታሪክ ላይ ያልተመሰረተ ፅሑፍ ማቅረባቸው እጅግ ያሳዝናል።

ለመሆኑ ኢጣልያ፣ ኤርትራን ለመቆጣጠር የቻለው እንዴት ነው? አፄ ዮሐንስ በ1881 ዓ.ም በኢትዮጵያ አቆጣጠር መተማ ላይ እንዳረፉ፣ ንጉስ ምኒልክ ከአንድ ወር በኋላ፣ ማለትም በሚያዝያ ወር 1881 ዓ.ም ላይ ነው ከኢጣልያ መንግስት ጋር የውጫሌን ውል የተፈራረሙት። ውሉም አፄ ምኒልክ በተገኙበት የተነደፈ አይደለም። ከሮማ ከተማ ተፅፎ የመጣላቸውን ነው በትእዛዝ መልክ እንዲፈርሙ የተደረጉት። ውሉም ደጋማውን የሐማሴን አካባቢ በሙሉ ለኢጣልያ

የሚያስረክብ ነበር። ቀስ በቀስም እስከ መረብ ወንዝ ድረስ ለኢጣልያኖች አበረከቱላቸው።

አቶ አስረስ የኔሰው፣ «ትቤ አክሱም መኑ አንተ?» በተባለ መፅሐፋቸው ይህን ቢተመለከተ ሲተርኩ፣« በኮንት አንቶኔሊና በአፄ ምኒልክ መሃከል የተዘራው ፍቅር ታመመና ችግር አጋጠመው። አፄ ምኒልክ ከትግራይ ወደ አዲስ አበባ እንደተመለሱ፣ ኮንት አንቶኔሊም አፄ ምኒልክን ተከትሎ ወደ ሸዋ መጣ። ከአፄ ምኒልክ ጋር ከተገናኙ በኋላም ስለ ዳርድንበር ጉዳይ በጥልቅ ተወያዩ። አፄ ምኒልክም ኮንት አንቶኔሊን እስቲ ወደ ውጭ ውጣና ከመኳንንቶቼ ጋር መክሬ አስታውቅሃለሁ ብለው ከመኳንቶቻቸው ጋር መከሩ። የሸዋ መኳንንት ግን ባንድ ቃል ሆነው፣ እንደ ውጫሌ ውል የቆመ እንደሆነ እሺ፣ ያለዚያ ግን አከለጉዛይንና ሰራዬን ለኢጣልያ ግዛት ሊሆን አንሰጥም፣ በጦርነት ካልሆነ በቀር አልዋቸው።

«አፄ ምኒልክ ግን ከኢጣልያ ጋር መጣላትን ፈሩና ኢጣልያኖች እንዳልዋቸው በመረብና በበለሳ ሙና ዳርቻ ምድር ሊሰጥዋቸው ፈለጉ። ነገር ግን የሸዋ መኳንንት በሕብረት ጠንክረው ባንድ ላይ ሆነው አከለጉዛይንና ሰራዬን ለኢጣልያ አሳልፈን ከመስጠት ደማችንን ማፍሰስ ይቀርበናል አሉ።

«መኳንንቶቹ በውጫሌ ውል ብቻ ይቁም ብለው ቁርጥ አቋዋም ከያዙ በኋላ፣ አፄ ምኒልክ እጅግ ፈሩ።

«ስለሆነም ከመኳንንቶቻቸው ተሸሽገው፣ ከኮንት አንቶኔሊ ጋር በእልፍኝ ሆነው፣ እስከ በለሳ ሙና እስከ መረብ ዳርቻ ድርስ የምጥዋ ገዥ ሊገዛው እሺ ብለው በመዋዋል ተፈራረሙ።

የኢትዮጵያ መኳንንት ግን አከለጉዛይና ሰራዬ የኢትዮጵያ ግዛት ነው:: ያለዝያ የአፄ ምኒልክ ውል ውላችን አይደለም እያሉ በየአደባባዩ ያለቅሱ ነበር» ይሉናል:: /ገፅ 30-31/

አቶ አስረስ የኔሰው በግልፅ እደሚያስቀምጡት ኤርትራ ለኢጣልያ የተሰጠችው፣ በአፄ ምኒልክ ቡራኬ እንጂ፣ በወረራ አይደለም:: ያውም የኢትዮጵያ መኳንንት እያለቀሱ:: አፄ ምኒልክ ፈሪ ስለ ነበሩ ከኢጣልያኖች ጋር ለመጣላት አልፈለጉም:: የራሳቸው መኳንንት ስለተቃወሙዋቸው ደግሞ፣ ወደ እልፍኝ ገብተው ኤርትራን የሚያህል ክፍለሃገር ለኢጣልያኖች በገፀበረከት መልክ አበረከቱ:: የአፄ ምኒልክ ዓላማ ግን ድንገተኛ አልነበረም:: ቀደም ሲልም ከግብፅ መንግስት ጋር ከፍተኛ ግንኙነት ነበራቸው:: ዓላማቸውም አንድ እና አንድ ብቻ ነበር:: ማለትም ማንኛውም ነገር በመክፈል፣ የትግራይን ህዝብ በተለያዩ ሴራዎች አዳክሞ ማንበርከክና ስልጣን መጨበጥ ብቻ::

ይህ በእንዲህ እያለ፣ አንዳንድ የትግራይ መሳፍንትም፣ የአፄ ምኒልክና የኢጣልያ ተባባሪዎች በመሆን በትግራይ ህዝብ ላይ ከፍተኛ ጥፋት አድርሰዋል::

ለምሳሌ ደጃዝማች ስዩም አባ ጉበዝና ደጃዝማች ደበብ አርአያ፣ በአፄ ምኒልክና በወራሪው የኢጣልያ መንግስት እየታገዙ ብዙ ወረራዎችና ግፍ የተሞላባቸው ጦርነቶች ትግራይ ውስጥ አካሂደዋል::

ደብተራ ፍስሃ ጊዮርጊስም ይህን አስመልክተው ሲተርኩ፣ «ደጃዝምች ስዩም አባ ጉበዝ ብቻ፣ የአፄ ምኒልክን ዓላማ ለማሳካት፣ ትግራይ ውስጥ በ25 አካባቢዎች ጦርነት አድርገዋል::

ይህም እራሳቸው ለአንድ መኰንን ከየፉት ደብዳቤ ያነበብኩት ነው፣» በማለት ይገልፁልናል። ደጃዝማች ደበብ አርአያም እንዲሁ፣ ባህታውያን ነን ባዮች «ትነግሳለህ ብለውኛል» ብለው በማደናገር ከትግራይ ህዝብ ደመኛ ጠላቶች፣ ማለትም ከአፄ ምኒልክና ከኢጣልያ ጐን ተሰልፈው በትግራይ ህዝብ ላይ ብዙ ግፍ ፈፅመዋል። እግራቸው የደረሰበትን አካባቢ ሁሉ እንዳልነበረ አድርገውታል። ዛሬም ቢሆን፣ የታሪክ ሕግ ነውና፣ ከትግራይ ህዝብ ደመኛ ጠላቶች ጋር ተሰልፈው፣ የትግራይን ህዝብ የሚያደሙ፣ የትግራይ ተወላጆች አልታጡም። በዚያን ጊዜ ትግራይ ውስጥ ሕግና ስርዓት አልነበረም። ሃይል ያለው ሰው ሁሉ የፈለገውን ነገር ያደርጋል።

መሪና ተመሪ፣ ጠያቂና ተጠያቂ የሚባል ነገር አልነበረም። የኢጣልያ ወታደሮችም ከአስመራ ተነስተው ያለምንም ችግር ወደ ትግራይ ከተሞች ይገባሉ፣ ይወጣሉ። ለምን? የሚል መንግስትና ሃይል የለም። አፄ ምኒልክ፣ «ትግሬ ከጠገበና አንድ ከሆነ አይገዛም» በሚል ፍልስፍናቸው እየተመሩ፣ የትግራይን ህዝብ ሽባ በማድረግና ስርዓተ አልበኝነትን በማንገስ ለወራሪዎችና ለዘራፊዎች ዳርገውታል።

ሃጋይ ኤርሊክም ይህን በተመለከተ የሚለው አለው።

«ትግራይ ተራበች፣ ተወረረች፣ ተበታተነች፣ ዓጋመም የብጥብጥ ቦታ ሆነች፣ ዓድዋ ደግሞ በኢጣልያኖች እጅ ወደቀች፣ እንደርታም በወራሪው የሸዋ ሰራዊት ተዘምታለች» በማለት በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ ይገልፀዋል። /ገፅ 202/

አፄ ምኒልክ ወደ ትግራይ የዘመቱት፣ የትግራይን ህዝብ ለመዝረፍና ለመደምሰስ እንጂ፣ ትግራይ ውስጥ ሕግና ስርዓት ለማስፈን አልነበረም:: ስለሆነም ማንኛውም፣ ሃይል የሚሰማው ሰው ሁሉ፣ ጦርነት የመከፈት፣ መንደር የመዝረፍ፣ ግለሰቦችን የመግደል ወዘተ ስልጣን ነበረው::

ሰሓጢ እግርጌ ላይ ለመቆናጠጥ እንኳ እድል አግኝተው የማያውቁት ኢጣልያኖችም፣ የነአሉላ አባነጋን ምድር በትዕቢት ረገጡት:: ናቁት፣ ፈነጩበት::

ሃጋይ ኤርሊክ ይህን አስምልክቶ ሲተርክ «ጄኔራል ባልዲሴራ አሬሮ፣ ራስ መንገሻንና ራስ አሉላን ማርኮ ወደ ኤርትራ ለመውሰድ ጥር 26 ቀን 1890 ዓ.ም ያለ ምንም ፈቃድ ወደ ዓድዋ ከተማ መጣ» ይለናል:: /ገፅ 202/

ሃጋይ ኤርሊክ፣ እዚህ ላይ ነገሩ ግልፅ የሆነለት አይመስለኝም:: ጄኔራል ባልዲ ሴራ ወደ ትግራይ ለመግባት ማንን ነው ፈቃድ የሚጠይቀው? ትግራይ'ኮ መንግስት የላትም:: የትግራይ ህዝብ'ኮ ግራ በተጋቡ ተቀናቃኝ መሳፍንትና ሽፍቶች ነው እየታመሰ ያለው:: ይህ እንዳለ ሆኖ ግን ጄኔራል ባልዲ ሴራ አፄ ምኒልክን ሳያማክር ወደ ዓድዋ ይመጣል ተብሎ መገመት የለበትም:: የአፄ ምኒልክና የጄኔራል ባልዲ ሴራ ዓላማ አንድ እና አንድ ብቻ ነው:: እሱም የትግራይን ህዝብ በማዳከም፣ በመደምሰስና በመበታተን፣ በአስመራና በአዲስ አበባ ያሉ መንግስታት ያለ ስጋት እንዲኖሩ ማድረግ ብቻ ነው:: ነገሩን በግልፅ ለማስቀመጥ ግን፣ አፄ ምኒልክም ቢሆኑ ጄኔራል ባልዲ

ሴራን ወደ ትግራይ ግባ አትግባ ለማለት ስልጣን አልነበራቸውም።

ትግራይ ውስጥ ለሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ሁሉ ትእዛዝ የሚመጣው ከአፄ ምኒልክ ሳይሆን ከኢጣልያ መንግስት ነበር ለማለት ይቻላል። ለምሳሌ ሃጋይ ኤርሊክ ይህን በተመለከተ የሚጠቁመን ነገር አለ።

«አፄ ምኒልክ በኢጣልያኖች ዓይን እንደ ወንጀለኛ ለሚታዩት ራስ አሉላ፣ ትግራይ ውስጥ ምንም ዓይነት ስልጣን እንዳልተሰጣቸው አረጋገጡላቸው» ይላል። /ገፅ 205/

ከዚህ ምን እንገነዘባለን? የሃጋይ ኤርሊክን አባባል መሰረት አድርገን ስናየው፣ አፄ ምኒልክ በትግራይ ላይ የሚወስዱት እርምጃ በሙሉ ከኢጣልያ ጋር በመመካከር እንደነበር መገንዘብ ይቻላል። ጄኔራል ባራቲሴራ፣ ራስ መንገሻንና ራስ አሉላን ለመማረክና ለማሰር ዕድል አላገኘም። ይህ የሆነበት ምክንያትም እነሱ በዚያን ጊዜ ዓድዋ ከተማ ውስጥ ስላልነበሩ ነው።

በውጫሌ ውል፣ አንቀፅ 13 በተደነገገው መሰረት፣ በዚሁ ወቅት ማንኛውም የጦር መሳሪያ በኤርትራ በኩል ወደ ትግራይ ሊገባ አይፈቀድም ነበር። የኤርትራ ህዝብም ከዚህ የተለየ ዕድል አልነበረውም። ይሁን እንጂ፣ የትግራይና የኤርትራ ህዝብ ባለው አቅም፣ ወራሪዎችን ከመመከት ወደ ኋላ ያለበት ጊዜ አልነበረም።

እንደነ ራስ አሉላ፣ ያሉ የትግራይ ጀግኖችም ኢጣልያን ከምድረ ኤርትራ ጠራርጎ ለማባረር ዕድል እንዲሰጣቸው አፄ ምኒልክን ነጋ ጠባ መጠየቃቸው አልቀረም።

ግን፣ ይህ ዓይነቱ ጥያቄ፣ «ትግሬ ከጠገበና አንድ ከሆነ አይገዛም» ከሚለው የአፄ ምኒልክ ፍልስፍና ጋር ስለሚጋጭ አልተፈቀደላቸውም::

ሃጋይ ኤርሊክም ይህን አባባል በዚህ መልክ ያስቀምጠዋል:: «ራስ አሉላ ግን፣ ሙሉ ሐላፊነት ተሰጥቶዋቸው ጣልያኖችን ለመውጋት እንዲፈቀድላቸው አዲሱ ጌታቸው ንጉስ ምኒልክን ይጐተጉትዋቸው ነበር» በማለት ያረግጥልናል:: /ገፅ 248/

የኤርትራ ጀግኖችም እንዲሁ የአፄ ምኒልክን የውጫሌ ውል በመፃረር ከወራሪው የኢጣልያ ጦር ጋር በየቦታው በመፋለም ላይ ነበሩ:: ከነዚሁ የኤርትራ ጀግኖች አንዱም ደጃዝማች ባህታ ሐጐስ ናቸው::

አቶ አስረስ የኔሰው «ትቤ አኩሱም መኑ አንተ?» በተባለ መፅሐፋቸው ይህን በተመለከተ የሚሉንን ደግሞ እንስማ::

«ደጃዝማች ባህታ ሐጐስ፣ ከጀግኖች ወታደሮቻቸውና ከዘመዶቻቸው ከባሻይ ምስጉን ጋር ሆነው ሐላይ በተባለ መንደር ከኢጣልያ ጄኔራሎች ጋር ሲፋለሙ ታሕሳስ 18 ቀን 1894 ዓ.ም ላይ በ3 ጥይት ተወግተው በጀግንነት ተሰዉ» በማለት ታሪኩን ይገልፁታል:: /ገፅ 37/

ይህ እንዳለ ይቆይልንና፣ እስቲ እንደገና ደግሞ ቀደም ብዬ ጠቅሸው ወደ ነበረው የፕሮፌሰር መስፍን ጥያቄ ልመልሳችሁ::

«አፄ ምኒልክ፣ ቢያንስ ትግራይን ከኢጣልያ ቅኝ ተገዥነት አዳኑ:: ኤርትራን ለምንና እንዴት ለኢጣልያ ተዉት? የሚለው

ጥያቄ ውስብስብና አከራካሪ ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን አንድ ሌላ ጥያቄም በግድ መቅረብ አለበት::

«አንድ ሺሕ ኪሎ ሜትር ተጉዘው የተዋጉትን ከመውቀስ የአካባቢው ሰዎች ኢጣልያን ከትግራይም ሆነ ከኤርትራ ለማስወጣት ምን እንቅስቃሴ አድርገው ነበር? ብሎ መጠየቅና መልሱንም ማግኘት ተገቢ በሆነ ነበር» ብለው ነው ፕሮፌሰር መስፍን የሚጠይቁት::

በጣም ነው የሚያሳዝነው:: ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም፣ የትግራይና የኤርትራ ህዝብ ኢጣልያን ካገሩ ለማባረር ለምን አልተንቀሳቀሰም? ብለው ጠይቀውናል:: እኔ በበኩሌ ፕሮፌሰር መስፍን ይህን ጥያቄ ያቀረቡት የእውቀት እጥረት ስላለባቸው ነው የሚል ግምት የለኝም:: ነገር ግን፣ እንደ ማንኛውም በጭፍን ጥላቻ የታወረ ትምክሕተኛ፣ የዚህን ኩሩና ጀግና ህዝብ ማንነትና ጀግንነት በማድበስበስ፣ በውሸትና በውዳሴ ከንቱ ያሸበረቀ የትምክሕተኞች የተረት ተረት ታሪክ አጉልተው ለማሳየት ስለሚፈልጉ ነው::

ይሁን እንጂ፣ «ሐቅን ወርቅን አይዝዕግን» እንደሚባለው፣ ውሸት ቢከመር ኪስ ስለማይሞላ ትርጉም አይኖረውም:: የትምክሕተኞች የተረት ተረት ታሪክም እየዋለ እያደረ መጋለጡ አይቀርም::

መቀሌ ከተማ ላይ ተወልዶ ያደገው አርቲስት ኪዳነ ማርያም ረዳ፣ በትግል ዓለም ውስጥ በነበረበት ጊዜ የገጠመውና ያዜመው ታሪካዊ ግጥም አለ:: የአርቲስቱ ግጥምም፣ እንደ ፕሮፌሰር መስፍን ያሉ ትምክሕተኞች፣ በትግራይ ህዝብ ታሪክና

ጀግንነት ሁልጊዜ እየ ተከፈሱ፣ በአንፃሩ ደግሞ የትግራይን ህዝብ በማጥላላትና በማንኳሰስ፣ የህዝባችንን ታሪክ እና ማንነት ለመቅበር ምን ያህል እንደተንቀሳቀሱ ነው ግልፅ የሚያደርግልን።

የአርቲስቱ ዘመን የማይሽረው ግጥምም፣ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው።

«እንተሸፈንካያ ዘይትሽፈን ሓቀኛ ቕያ፣
እንተትሓብአት'ውን ተቐላዒት ኢያ፣
ንኣብነት ማይ ጨው ዓድዋ እንተዘከርና፣
ተንቤን ዓቢይ ዓዲ ሽረ እንዳባጉና፣
ኩናት ምስ ገበሩ እቶም ወለድና፣
ዐላኢ ደምሲሶም ታሪኽ ሓደጉልና።
«ጀጋኑ ወለዲ ዓበይቲ ተጋሩ፣
ኣይኮነን ናይ ሎሚ ኩሉም ዝተላዕሉ፣
ዓመታት ሓሊፉ ካብ ቀደም ጀሚሩ፣
ኣንፃር'ቶም ባዕዳውያን ኣነ እምብለይ በሉ።
«ኣብ ብዙሕ ቦታታት ዝተዓወትናሉ፣
ጀጋኑ ተጋሩ ደሞም ዘፍሰሱሉ፣
ገዛእቲ ደርብታት ጨቆንትና ኣምሓሩ፣
ብናይ ደም ወለዲ ኣለዉ ይኾርዑሉ።
«ጨቆንትና ኣምሓሩ ምስታሪኽ ዐሓፍቶም፣
ንኻና ዓብሊሎም ታሪኽና ጉቢጦም፣
ኣለዉ ይምክሑ ብደም ወለድና፣
ንቃለስ ተጋሩ ክንምልስ ቅያና»

እያለ ነው አርቲስት ኪዳነማርያም ረዳ፣ የትምክሕተኞችን ማንነትና የፈጠራ ታሪክ የሚያጋልጠው::

ግጥሙ ወደ አማርኛ ቋንቋ ሲመለስ ደግሞ፣

«ሐቀኛ ታሪክ ተደብቆ አይቀርም:: ለምሳሌ፣ የማይጨውን፣ የዓድዋን፣ የተንቤን ዓቢይ ዓድንና የሽረ እንዳባጉናን ታሪክ ያኖን እንደሆን፣ አባቶቻችን ወራሪዎችን ድባቅ በመምታት አኩሪ ታሪክ ትተውልን አልፈዋል:: ሁሉም እምቢ ለጭቆና ብሎ በተነሳሳበት በአሁኑ ዘመን ይቅርና ጀግኖች አባቶቻችን አምናና ታች አምናም ቢሆን፣ ለወራሪዎች አንበረከክም ብለው፣ ዓመታትን አስቆጥረዋል::

«ይሁን እንጂ፣ አባቶች በብዙ ዓውደ ውጊያዎች ደማቸውን አፍስሰው ያስመዘገቡትን አኩሪ ታሪክ፣ ጨቋኖቹ የአማራ ገዥ መደቦች፣ በአሁኑ ወቅት እየተኩፈሱበት ነው:: ጨቋኞቹ የአማራ ገዥ መደቦችና የእነሱ ታሪክ ፀሐፊዎች፣ እኛን መቀመቅ ከተው፣ ታሪካችንም ቀብረው፣ ባባቶቻችን ደም እየተመኩ ናቸውና፣ ሁላችንም የትግራይ ልጆች፣ ታሪካችንን ለማደስ በዕናት መታገል አለብን» የሚል መልእክት አለው::

ኢጣልያኖች ቀደም ሲል፣ ደጃዝማች ባህታ ሐጐስን የአከለጉዛይ አውራጃ ገዥ አድርገው ሾመውት ነበር:: ከራሱ መንግሻ ዮሐንስ ጋር ሚስጢራዊ ግንኙነት ከመሰረተ በኋላ ግን፣ ከራስ መንግሻ ጋር ሆኖ ኢጣልያኖችን ከምድረ ኤርትራ ለማባረር ተስማማ:: ወራሪዎች ስለነቁበት ግን ዓላማውን ሳያሳካ ባጭሩ ተቀጨ:: ይሁን እንጂ ለትግራይ ትግርኚ ህዝብ አርአያ የሚሆን ጀብዱ ነው ፈፅሞ ያለፈው::

በደጃዝማች ባህታ ሐጎስ ጀግንነት የተሞላበት እርምጃ የተደናገጠው ጄኔራል ባራቴሪም፣ ራስ መንገሻንና የትግራይን ህዝብ ለማስፈራራት፣ ታሕሳስ 28 ቀን 1894 ዓ.ም ወደ ዓድዋ ከተማ ገባ:: የዓድዋ ከተማ ህዝብም ከፍተኛ የተቃውሞ ሰልፍ አደረገ:: የኢጣልያ ወራሪ ሃይልም ከሶስት ቀን ቆይታ በኋላ ተመልሶ ወደ አከለጉዛይ ሄደ:: የትግራይ ህዝብ ግን፣ በዚህ የኢጣልያ ድርጊት እጅግ ተናደደ:: «በአፄ ምኒልክ ሃገራዊ ክሕደት ምክንያት እንደ ሲኦል ይፈሩን በነበሩ ወራሪዎች ተረገጥን፣ ተዋረድን፣ ጠላቶቻችን አፌዙብን» ብሎ ከልብ አዘነ:: ወራሪዎች ከምድረ ኤርትራ ካልተባረሩ በስተቀር በሰላም ልንኖር አንችልም ብሎ ህዝቡ በቁጣ ተነሳ:: «አፄ ምኒልክ ራስ አሉላን ወደ ሸዋ ባይወስዱብን ኖሮ፣ ኢጣልያ እንዲህ ባልተጫወተብን ነበር» እያለ የትግራይ ህዝብ ቁጣውን ገለጠ::

ከዚህ በኋላ ራስ መንገሻ የደጃዝማች ባህታ ሐጎስን ደም ለመበቀልም በማውጠንጠን ላይ ነበሩና፣ ከዚሁ ጋር ተዳምሮ ንዴታቸው ከመጠን በላይ ሆነ:: የኢጣልያን ሃይል የሚመክት ትጥቅና ሰራዊት እንደሌላቸው ቢገነዘቡም፣ ባላቸው አቅም ከወራሪዎች ጋር መዋደቅን መረጡ::

ሃጋይ ኤርሊክም ይህን አስምልክቶ ሲፅፍ፣ «ራስ መንገሻም ይህነን ለመበቀል፣ ወደ 10000 የሚጠጋ ሰራዊት አስከትለው ጥር 9 ቀን 1895 ዓ.ም መረብን ተሻገሩ:: ቀጥሎም ከጥር 13-14 ቀን ኰዓቲት ላይ ጦርነት አደረጉ» ይላል:: /ገፅ 249/

አቶ አስረስ የኔሰውም፣ «ትቤ አኩሱም መኑ አንተ?» በለተባለ መፅሐፋቸው የኰዓቲትን ጦርነት አስመልክተው

የሚገልፁልን አላቸው:: «የባራተሪ ሰራዊት ቶሎ ብሎ የኩዓቲትን ተራሮች በመያዝ ጠላቶቹን ለመውጋት ተዘጋጅቶ ነበር:: ምክንያቱም ኢጣልያኖች ደማቸው ዘወትር በትግሬዎች እጅ እየፈሰሰ ይሄዱ ነበርና፣ በዚያች ቀን ግን ድል አድርገው የደማቸውን ዋጋ ሊያገኙ፣ እልልታ ሊሆንላቸው፣ ብዙ ተስፋ ነበራቸው:: ነገር ግን፣ አፄ ምኒልክ ራስ መንገሻን ለማገዝ እንዳይመጡ ብለው ይፈሩ ነበር» በማለት ይተርካሉ:: /ገፅ 40/

እዚህ ላይ አንድ የማይመስል ሐሳብ አለ:: ኢጣልያኖች ከአፄ ምኒልክ የተሰጣቸውን የቤት ስራ እየሰሩ ባሉበት ወቅት፣ እንዴትና ለምን ብለው ነው፣ አፄ ምኒልክ ራስ መንገሻን ለማገዝ የሚመጡት? ኢጣልያኖች'ኮ በውጫሌ ውል ሰንሰለት ተጐትተው እንዲመጡ የተደረገው የትግራይን ህዝብ ለመቆጣጠርና የእምዬ ምኒልክን ሰሎሞናዊ ዙፋን ለመጠበቅ ነው::

ስለሆነም የትግራይ ህዝብ ሞት፣ የትግራይ ህዝብ ውድመት የትግራይ ህዝብ እልቂት ወዘተ ለአፄ ምኒልክ የመንፈስ እርካታ ነው የሚሰጣቸው:: ምክንያቱም የአፄ ምኒልክ ዋና ዓላማ የትግራይን ህዝብ ማደህየት፣ ማዳከምና መበታተን ነውና:: አፄ ምኒልክና ስርዓታቸው ሊጨነቁና ሊረበሹ የሚችሉት ግን፣ የኢጣልያ ወራሪ ሃይል የትግራይን ህዝብ፣ ሙሉ በሙሉ ከደመሰሰ በኋላ፣ አምባላጌ ተራራ ጫፍ ላይ ሆኖ፣ አንኮበር ላይ የተዘረጋው፣ ዙፋናቸውን ለመናድ እያማተረ መሆኑን ሲገነዘቡ ብቻ ነው:: ይህም በታሪክ ተደጋግሞ የታየና የተረጋጋጠ ሐቅ ነው::

እስቲ የአቶ አስረስ የኔሰው ተጨማሪ ትረካ ደግሞ እንከታተል።

«የራስ መንገሻ ወታደሮችም ባላገሮች ስለሆኑ፣ በዚሁ ጫካ እየተሽለኰለኩ፣ በፍጥነት በግራና በቀኝ፣ በፊትና በኋላ እየፎከሩ እንደ አንበጣ ወረሩዋቸውና፣ ከኢጣልያ ወታደሮች ጋር ተደባልቀው አንገት አንገቱን እየያዙ በሚያስደነግጥ የጭካኔ ስራ፣ በጉራዴ እየጐመዱ ጣሉት። የኢጣልያ ወታደሮችም አለቁ። የራስ መንገሻ ወታደሮችም ደጀኑን ሰንጥቀው ከበቡት።

«ከዚህ በኋላ የኢጣልያ ወታደሮች፣ 1800 ሜትር ርቀው መድፍ ለቀቁባቸው። በዚህ ምክንያትም፣ የራስ መንገሻ ወታደሮች መቀዝቀዝ ጀመሩ። በመሆኑም ድሉ ለመጀመሪያ ጊዜ ለኢጣልያኖች ሆነ። ከዚያ በኋላ ነው እንግዲህ ኢጣልያኖች፣ ደጃዝማች ባህታን ገደልን፣ ራስ መንገሻን ኰዓቲት ላይ ድል አደረግን፣ አባረርን፣ እያሉ ከዓድዋ እስከ ዓዲ ግራት፣ እስከ መቀሌ እስከ አምባላጌ ድረስ ለመምጣት የቻሉት» በማለት ነው አቶ አስረስ የኔሰው የትግራይን ህዝብ አኩሪ የጀግንነት ታሪክ የሚገልፁልን። /ገፅ 42/

የትግራይ ህዝብ በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢጣልያ ጦር የተቸነፈው በኰዓቲት ጦርነት ብቻ ነው። ለምን? የሚል ጥያቄም መነሳት ያለበት ይመስለኛል። መልሱ ግን በጣም ቀላል ነው።

በመጀመሪያ ደረጃ፣ የትግራይ ህዝብ ከአፄ ዮሐንስ ሞት በኋላ «የኔ ህዝብ ነው» የሚለው መንግስት አልነበረውም። መንግስትና መሪ የሌለው ህዝብ ደግሞ፣ አንድነት የለውምና ጠላቶቹን በጋራ ሊመክት አይችልም። ከዚህም ሌላ፣ አፄ

ምኒልክ ትግራይን በወረሩበት ጊዜ ያለትጥቅ አስቀርተውታል። የጦር መሳርያ እገዳም ተደርጎበታል። ይህ ብቻ ግን አይደለም። ወራሪው የኢጣልያ መንግስት፣ የአፄ ምኒልክ ሽርክ ነበርና፣ የዕለት ተለት መረጃ ስለሚላክለት፣ የትግራይ ህዝብ የተሟላ ትጥቅና ጥይት እንደሌለው፣ ሙሉ በሙሉ ያውቅ ነበር። በመሆኑም ባለ በሌለ ሃይሉ ተዋጋ። በራስ መንገሻ ዮሐንስ የሚመራው የትግራይ ህዝብ ጦርም ድል ሆነ። የኢጣልያ ህዝብም ይሆናል ተብሎ የማይገመት የድል ብስራት ሰማ።

አቶ አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ ደግሞ፣ የኰዓቲትን ጦርነት እንደሚከተለው ይገልፁታል።

«የኢጣልያ መልክተኛ ኮሎኔል ፒአኖ፣ ከአዲስ አበባ ወደገሩ እንደተመለሰ በጥር ወር 1887 ዓ.ም ላይ፣ ያስመራ ገዥ ጄኔራል ባራቴሪ ከራስ መንገሻ ጋር ኰዓቲት ላይ ተዋግቶ ድል አደረገ። እንደኡነቱ ግን፣ የራስ መንገሻ ጦር አሳምሮ ተዋጋ። ነገር ግን ድል በሚያደርግበት ጊዜ ጥይት አለቀበት።

«የኢጣልያ ጦር መቸም፣ ብርቱው ጦሩ ባሸብዙቅ ነበርና፣ ትግሬን ሁሉ እስከ አሸንጌ ድረስ ያዘ። መቀሌ ላይም ብረቱ ምሺግ ሰራና ብዙ ጦር አስቀመጠ። ይሄሁሉ ሲሆን አጤ ምኒልክ ቶሎ ወደ ትግሬ ለመምጣት አልተቻኰሉም ነበረ። ዝግ ብለው ብቻ የጦርነታቸውን ሁሉ ነገር ያሰናዱ ጀመር። ይሄ ዝግታዎ ግን በአውሮጳ ሁሉ የፍርሃት መስሎ ታይቶ ነበር» በማለት ይተርካሉ። /ገፅ 87/

አቶ አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ «አፄ ምኒልክ ወደ ትግሬ ለመምጣት አልተቻኰሉም ነበር» ብለውናል። ለምን ይቻኰላሉ?

ወራሪው የኢጣልያ ጦር የትብብር ጥሪ ቢያቀርብላቸው ኖሮ፣ የቁርጥ ቀን የልብ ወዳጅ ናቸውና፣ ከመቅፅበት ይደርሱለት ነበር:: የትግራይ ህዝብ ግን፣ ምናቸው ሆነና ነው ፈጥነው አልደረሱለትም ተብለው ሊታሙ የሚችሉት?

የትግራይ ህዝብ'ኮ የአፄ ምኒልክና የሁሉም ትምክሕተኞች ቁጥር አንድ ጠላት ነው:: ስለሆነም በትግራይ ህዝብ ላይ የሚደርስ ሞትና እልቂት አፄ ምኒልክን ሊያሳስባቸው ይችላል ተብሎ አይገመትም:: እልቂቱን ለማፋጠን ይቻል ዘንድ ነዳጅ ተባበሩን የሚል ጥያቄ ቢቀርብላቸው ግን፣ የሁሉም ትምክሕተኞች ምላሽ ቅፅበታዊ ይሆናል:: ይህ የሚሆንበት ምክንያትም፣ በአሁኑ ወቅትም እንደምናየው፣ ትምክሕተኞች፣ ከትግራይ ህዝብ በላይ የሚያዩት ጠላት አለን ብለው ስለማያምኑ ነው::

አቶ አስረስ የኔሰው ኰዓቲት ጦር ግንባር ስለተከፈለው መስዋእትም በመጠኑ ያብራራሉ::

«በኰዓቲት ጦርነት፣ ከ1000 በላይ ወታደርና ከ20 በላይ መኳንንት እንደ ሞቱ ይነገራል:: በጦርነቱ ከሞቱት መኳንንት ውስጥም ደጃዝማች ተድላ ዓይባ፣ ደጃዝማች በየነ፣ ደጃዝማች ካሳ፣ ቀኛዝማች አንዳጋርቸው ወዘተ ይገኙበታል» በማለት ነው የሚተርኩልን:: /ገፅ 43/

ከዚህ በኋላ የኰዓቲትና የሰንዓፌን ድል በተመለከተ ለኢጣልያ ወታደሮች አንድ ቴሌግራም ደረሳቸው:: የቴሌግራሙም ይዘት እንዲህ ይላል::

«ለጄኔራል ባራቴሪ፣ የኢጣልያ ወታደሮች፣ በኰዓቲትና በሰንዓፌ የሐበሻ ጨካኝ ወታደሮችን ድል ማድረጋቸው በኢጣልያ አገር ደስታና ትልቅ ስልጣን ሆነ። በትጋት መስራትህን ደስ ብሎኛልና በልቤ አመሰግናለሁ። ለመኳንንቶችም፣ ለወታደሮችም ከነሱ ሶስት እጥፍ የሚበልጡትን ጠላቶቻቸው ያለ ፍርሃት፣ ያለ ድንጋጤ፣ ሶስት ቀን ሙሉ ተዋግተው ድል ማድረጋቸው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነውና፣ የልቤንም ምስጋና አቅርብልኝ።

«እንግዲህ አንተና ላንተ የሚታዘዙ ወታደሮች፣ በኤርትራ እያላችሁ፣ ያች ኮሎኒያችን ልትከበርና ሌላ ድንገተኛ ነገር ያገኛታል ብዬ አልፈራም።

*ሮማ ላይ አንደኛ ኡምበርቶ የኢጣልያ ንጉስ፣ ጥር 18 ቀን 1895 ዓ.ም» /ገፅ 44/*

የኢጣልያ ህዝብና መንግስት ሊታመን የማይችል የድል ብስራት ነው የተነገራቸው። ያ ስሙ ሲነሳ እንደ ርዕደ መሬት የሚያስደነግጣቸው ህዝብ፣ ያ«በዓለም ላይ እንደ ሐበሻ ያለ ጨካኝ አላየንም» የሚሉት ህዝብ፣ እነ አሉላ አባ ነጋ የተወለዱበት ምድር ተቸነፈ፣ የሚል ወሬ ሲሰማ፣ የኢጣልያ መንግስትና ህዝብ እውነት አልመስልህ አለው፣ ለማመንም ተቸገረ።

ነገር ግን አፄ፣ ምኒልክን ይዞ የማይደረግ ነገር የለምና ሆነ። ያ ጠላቶች የማይደፍሩት ኩሩ ህዝብ ተደፈረ። በእምዬ ምኒልክ ሃገራዊ ክሕደትና ሴራ ቅስሙ ተሰበረ።

የትግራይ ህዝብ ለወራሪዎች ምቹ አይደለም። ለዚህም ነው ሁሉም ወራሪዎች ዓይናቸው ወደ አፄ ምኒልክ የሚያዘነብሉት።

ንጉስ ኡምበርቶ፣ ለጄኔራል ባራቴሪ የላኩት ቴሌግራም ከላይ ተመልክተናል። ሌላ ሁለተኛ ቴሌግራምም በዚሁ ቀን ተልኮለታል። እስቲ የመልእክቱን ይዘት ቀጥለን እንየው።

«ለጄኔራል ባራቴሪ፣ ሐበሻን ድል በማድረግህ ካንተና ከኢጣልያ ህዝብ ጋር እጅግ ደስ ብሎኛል። ደግሞ ወታደሮቹን ብቻ አመስግኜ ዝም አልልም። ነገር ግን፣ ዳግማዊ ጋሪባልዴ የሆነ ካፒታኖ ችኮዳኮላ፣ ከጥቂት ወታደሮች ጋር ሆኖ ሃይለኞች ጠላቶቹን ድል ስላደረገ ምስጋና ይድረስለት።

«ዛሬ የትግራይ አገር በር ተከፈተልን። ምንም እንኳ ፈፅመን ባንይዛት ቀኖናችን ናት።

ሮማ ላይ ሚኒስትር ክርስፒ ጥር 18 ቀን ዓ.ም 1895 ዓ.ም።» /እነዚህ ሁለት ቴሌግራሞች «ትቤ አኩሱም መኑ አንተ?» ከተባለ የአቶ አስረስ የኔሰው መፅሐፍ የተወሰዱ ናቸው/

የኢጣልያው ጠቅላይ ሚኒስትር፣ «ዛሬ የትግራይ አገር በር ተከፈተልን» በማለት ልባዊ ደስታውን ገለፀ። የትግራይ በር የተከፈተው ግን፣ በወራሪው የኢጣልያ ጦር ብርታት አልነበረም። የትግራይ በር የተከፈተው አፄ ምኒልክ በፈበረኩት የውጫሌ ውል ቁልፍ ነው።

«ካፒታኖ ችኮዳኮላም» እንዲሁ ሃይለኞቹ ጠላቶቹን ድል ስላደረገ ከፍተኛ ምስጋና ተችሮታል። ምስጋናው መሰጠት የነበረበት ግን፣ ለጠቢቡ ንጉሰ ነገስት ለአፄ ምኒልክ ነው። ምክንያቱም የትግራይ በር የተሰበረው፣ በአፄ ምኒልክ ሃገራዊ ክሕደትና ልዩ ጥበብ እንጂ፣ በወራሪው የኢጣልያ ጦር ሃይል እና ችሎታ አይደለምና።

አቶ ተክለፃድቅ መኩርያ ደግሞ «ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ሃይለስላሴ» በተባለ መፅሐፋቸው፣ ጠቅላይ ሚኒስቴር ፍራንቼስኮ ክርስፒ «የትግሬ ግዛት ለኢጣልያ መንግስት የተከፈተ ነውና ለመያዝ ባንፈልግ የኛ ስንፍና መሆኑን እንዳትዘነጋ» ብሎ ቴሌግራም አስተላለፈለት በማለት ያስቀምጡታል። /ገፅ 100/

የትግራይ በር ለኢጣልያኖች ክፍት ሆኖዋልና ኢጣልያኖች እስከ ሐሸንጌ ድረስ መጡ፣ የትግራይ ህዝብ ግን፣ ከታሕሳስ ወር 1894 ዓ.ም ጀምሮ ከአንድ ዓመት በላይ ከወራሪው የኢጣልያ ጦር ጋር ብቻውን እየተፋለመ ነው ያለው።

የኢጣልያ ጦር ትግራይን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥሮ ሐሸንጌ ላይ ሲደርስ ግን፣ አፄ ምኒልክም ተጨነቁ። ዙፋናቸው ሲነቃነቅ ታያቸው። ኢጣልያ ሐሸንጌ ደረሰ ከተባለበት ቀን ጀምሮ የመንፈስ ዕረፍት አላገኙም። አፄ ምኒልክ ለዳር ድንበር መከበር፣ ለትግራይ ህዝብ ህልውና ደንታ ባይኖራቸውም፣ የስልጣን ጉዳይ ግን፣ እጅግ ነው የሚያስጨንቃቸው።

ስለሆነም፣ ስለዚሁ ጉዳይ ከእቴጌ ጣይቱና ከራስ አሉላ አባ ነጋ ጋር መመካከር ጀመሩ። እቴጌ ጣይቱና ራስ አሉላም ባስቸኳይ ጦርነት መጀመር አለበት የሚል ሐሳብ አቀረቡላቸው። አፄ ምኒልክም አማራጭ አልነበራቸውምና ቢወዱም ባይወዱም የቀረበላቸውን ሐሳብ ተቀበሉት።

ሃጋይ ኤርሊክም፣ ይህን አስመልክቶ ሲፅፍ፣ «በመጨረሻ ላይም አፄ ምኒልክ፣

ሀ. በራስ አሉላ የሚመራ የትግራይ ሐይል፣

ለ. በራስ ወሌ የሚመራ የሸዋ ሐይል፣

ሐ. በራስ ሚካኤል የሚመራ የኦሮሞ ሐይል፣

መ. እንደዚሁም በንጉስ ተክለ ሃይማኖት የሚመራ የጐጃም ሐይል ወደ ሰሜን ለመላክ ወሰኑ» ይለናል::

ነገር ግን አብዛኛዎቹ የሸዋ መኳንንት ይህን ሐሳብ በከፍተኛ ደረጃ ተቃወሙት:: መሆን የለበትም አሉ:: ምክንያታቸውን ሲያቀርቡም ሃጋይ ኤርሊክ እንደሚለው

«ከኢጣልያ ጋር አጠቃላይ ጦርነት ከመደረጉ በፊት የትግሬዎች ሐይል ብቻ ወደ ትግሬ መላክ አለበት ባዮች ነበሩ:: የኢጣልያ ጦር ግን መጋቢት 25 ቀን 1895 ዓ.ም ወደ ዓዲ ግራት ገባ:: ቀጥሎም ዓድዋንና መቀሌን ተቆጣጠረ» እያለ ይተርካል:: /ገፅ 250/ እዚህ ላይ መታየት ያለበት አንድ ነጥብ አለ:: የትግራይ ህዝብ ከላይ እንደተከታተልነው፣ ከ1890 ዓ.ም ጀምሮ በረሃብና በጦርነት ፍጻውን እያየ ነው:: ለስሙ ግን መንግስትም፣ ንጉሰ ነገስትም አለው ይባላል:: ነገር ግን እስከ መጋቢት ወር 1895 ዓ.ም ድረስ አለሁልህ ብሎ ከጐኑ የቆመለት መንግስትም ይሁን ህዝብ አላገኘም::

ይህ ብቻ ግን አይደለም:: የጦር መሳርያ በኤርትራ በኩል ወደ ትግራይ እንዳይገባም አፄ ምኒልክና ኢጣልያ እገዳ አድርገውበታል:: ስለሆነም የትግራይ ህዝብ ትጥቅ የሚያስፈቱና የትጥቅ እገዳ አድርገው የሚወጉት ጠላቶች እንጂ፣ ትጥቅ የሚያስታጥቅና አለሁልህ የሚለው የራሱ መንግስት አልነበረውም::

አፄ ምኒልክና ትምክሕተኛው ስርዓታቸው፣ የትግራይ ትግርኚ ህዝብ አንድነት ከአለት የጠነከረ መሆኑን ይገነዘባሉ::

በራስ መንገሻ ዮሐንስና በደጃዝማች ባህታ ሐጐስ መሃከል የነበረ የጋራ ትብብርንም ያስታውሱታል።

ስለሆነም፣ የሸዋ ትምክሕተኞች ዓላማ «ትግሬ ትግሬን አይወጋም። በመሆኑም ከፈለጉ ተባብረው ኢጣልያን ይግጠሙት፣ ካልፈጉ ደግሞ ባዘጋጀንላቸው ወጥመድ ውስጥ ገብተው፣ እርስ በርሳቸው ይተላለቁ» የሚል ነበር።

በዚያን ጊዜ ራስ አሉላን ጨምሮ፣ የተወሰኑ የትግራይ መኳንንት አዲስ አበባ ውስጥ ነበሩ።

የሸዋ መኳንንትም፣ ከዚህ በመነሳት ነው፣ መጀመርያ አዲስ አበባ ውስጥ ያሉት የትግራይ መኳንንትና ተከታዮቻቸው ወደ ጦርነቱ ግንባር መላክ አለባቸው የሚሉት። አቋማቸውም ግልፅ ነበር።

«ትግሬዎች ሙሉ በሙሉ መመታታቸውን ሳናረጋግጥ ለምን ከኢጣልያ ጋር እንዋጋለን? እኛ መዋጋት ያለብን ኢጣልያ ትግሬን መቶ በመቶ እንደ ደመሰሰና ሐሸንጌን አልፎ ወደ ሸዋ ለመምጣት እየተዘጋጀ መሆኑን ስንረጋግጥ ብቻ ነው» የሚል አመለካከት ነበራቸው። በሌላ አነጋገር የሸዋ መኳንንት «ትግሬና ነብር አይታመንም» የሚል ፍልስፍና ስለነበራቸው፣ መጀመርያ የትግራይ ህዝብ ተጨፍጭፎ ማለቅ አለበት ብለው ሞት ወሰኑበት።

ቀደም ብለን እንዳየነው፣ ደጃዝማች ባህታ ሐጐስ /ባህታ ሰገነይቲ/ እና ራስ መንገሻ ዮሐንስ ኰዓቲት ላይ የተቸነፉት፣ በኢትዮጵያ አቆጣጠር በ1887 ዓ.ም ነበር። በተከታታይም